በውጭ ምንዛሬና ጥሬ እቃ እጥረት የፈተነው የሕክምና ግብዓቶች ምርት

ገጽ 8

በትዳር አጋር የተነጠቀች ሕይወት

ገጽ 10

**የለመለመው ተስፋ ...** የተሁለደሬዋ ወይዘሮ ...

ገጽ 16


# አዲስ ዘመን

እፎይ

83ኛ ዓመት ቁጥር 026 መስከረም 26 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!











# ኢሬቻ

## መልከብዙው የምስጋና በዓል

ገጽ 4





## በአማራ ክልል

### የሰላም ሁኔታው እየተሻሻለ መምጣቱን ርዕሰ መስተዳድሩ አስታወቁ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ቀደም ሲል ከነበረው ግጭት አንጻር የክልሉ ሰላም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ ገለጹ።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አረጋ ከበደ የክልሉን ወቅታዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግ ከአሚኮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለጹት፤ በክልሉ የተከሰተው

በአማራ ክልል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## «በእሴቶቻችን ዙሪያ ተሰባስበን፤ የሚያደናቅፉንን እንቅፋቶች በመንቀል ነገን የበለጠ ብሩህ ለማድረግ ጠንክረን እንሥራ»

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በእሴቶቻችንና በባህላችን ዙሪያ ተሰባስበን፤ እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ የሚያደናቅፉንን እንቅፋቶች ሁሉ በመንቀል ዛሬ ላይ ሆነን ነገን የበለጠ ብሩህ ለማድረግ ጠንክረን ልንሠራ ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ለኢሬቻ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ትናንት

«በእሴቶቻችን ዙሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











## ኢሬቻ ለአብሮነትና ለማሕበራዊ መስተጋብር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

**መዓዛ ማሞ**

ኢሬቻ የአብሮነትና የምስጋና በዓል ሆኖ በኦሮሞ ህዝቦች ዘንድ በየዓመቱ ሲከበር የኖረ በዓል ነው። በዓሉ የክረምቱ ወቅት ተጠናቆ ምድር በአረንጓዴ ስታጌጥ የኦሮሞ ሕዝብ እርጥብ ሳር ይዞ ወደ ወንዝ በመውረድ ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት ታላቅ የምስጋና በዓል ነው።

በዓሉ በብዙዎች ዘንድ በጨለማ የሚገለጸው ክረምት በሰላም ተጠናቆና የወንዞች ሙላት ቀንሶ ሰዎች በሰላም ከጨለማ ወደ ብርሃን በመሸጋገራቸው ፈጣሪያቸውን የሚያመሰግኑበት የአዲስ ዓመት ማብሰሪያ መሆኑንም ብዙዎች ይናገራሉ።

ኢሬቻ ለአብሮነትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







ዜና

# በጥቅምት ወር በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ አካባቢዎች ከባድ ዝናብ ይኖራል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በጥቅምት ወር በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በመጪው ወር በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይጥላል።

በጸሐይ በመታገዝ ከሚፈጠር ከባድ ደመና ጋር ተያይዞ በምዕራብና በደቡብ አጋማሽ የሚፈጠረው ከባድ ዝናብ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የአፈር መሸርሸርና በእርሻ ማሳዎች ላይ ውሃ መተኛት ሊያጋጥም ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ኢንስቲትዩቱ አሳስቧል።

የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት ሁኔታው እንደሚጠናከር ያመላከተው ኢንስቲትዩቱ፤ በተጨማሪም የመካከለኛው አዋሽ፣ የደቡባዊ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖር አስታውቋል።

የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያን ጨምሮ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት ያለው የዝናብ ሁኔታ እንደሚኖር የገለጸው ኢንስቲትዩት፤ በሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቃማ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ፀባይ ጎልቶ እንደሚታይ አመላክቷል።

በሚቀጥለው ወር በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት እንደሚኖራቸው በመጥቀስ፤ በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖር ገልጿል።

በተለያዩ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ጠንካራ ደመናዎች እንደሚፈጠሩ የተመላከተ ሲሆን፤ በሰሜንና በደቡብ ወሎ፣ እንዲሁም አንዳንድ የትግራይ አካባቢዎችን ጨምሮ በደቡብ አፋር ዞን ሶስት፣ ዞን አራትና ዞን አምስት፣ እንዲሁም የምዕራብ አርሲ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ በመግለጫው ተመላክቷል።

ወቅታዊ ዝናብ ማግኘት በሚጀምሩትና የደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች በደጋማ አካባቢዎች ቀደም ብሎ የማሳ ዝግጅት ለማድረግና ዘር ለመዝራት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ኢንስቲትዩቱ በመግለጫው አስታውቋል።

በተጨማሪም የአየር ሁኔታው በደቡብና ደቡብ ምስራቅ፣ በምዕራብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ለሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲሁም ቀደም ብለውና ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት ለማሟላት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ተገልጿል።

# ኢሬቻ አብሮነትን ለማጠናከር የጎላ ሚና አለው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አሳታፊነትን ማዕከል ያደረገው ኢሬቻ አብሮነትና አንድነትን ለማጠናከር ያለው ሚና የጎላ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ገለጹ።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ፎክሎርና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህር ደረጄ ፉፋ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ብዝሃ ብሔሮችን አሳታፊነት ያደረገው የኢሬቻ ቱባ ባህል እንደሀገር አብሮነትን ለማጠናከር የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ነው።

የኢሬቻ በዓል አከባበር ሕዝብን ለማቀራረብና የተቋረጡ ግንኙነቶችን ለማደስ ይረዳል ያሉት ዶክተር ደረጄ፤ በዓሉ ማህበራዊ መስተጋብሮች እንዲዳብሩና ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚወገዱበትን መንገድ ለመፍጠር አይነተኛ መንገድ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የኢሬቻ በዓል የሕዝቦች አንድነት የሚጠናከርበት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር መቀራረብ የሚችልበት ዕድል አለው፤ በዓሉ ፍቅርን፣ ሰላምን የሚሰብክና በውሃ በተከበበ አካል በቄጠማ ታጅቦ የሚከበር ቱባ ባህል ነው ብለዋል።

በኢሬቻ በዓል ሕጉንና ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ከተከበረ ለአብሮነት ያለው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ያሉት ዶክተር ደረጄ፤ ስለበዓሉ ምንነት በመገንዘብ የወንድማማችነት ዓርማ አንግቦ ቀኑን ማክበር ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በኦሮሞ የጥናትና ምርምር ማዕከል የታሪክ ቡድን መሪና የታሪክ ባለሙያ አቶ ግርማ ነመራ በበኩላቸው፤ ኢሬቻ የእርቀ ሰላም ማውረጃና በአራቱም አቅጣጫ የሚኖር ሕዝብ የሚገናኝበት በመሆኑ ለእርስ በእርስ ግንኙነት መጠናከር ጉልህ ሚና እንዳለው አስረድተዋል።

በኢሬቻ የሚከወነው ቱባ ባህል አብዛኛው ብሔረሰብ የሚጋራው የሰላምና የፍቅር እሴት አለው ያሉት አቶ ግርማ፤ በበዓሉ ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የተውጣጡ ዜጎች የሚታደሙበት በመሆኑ ለሀገር አንድነት የማይተካ ድርሻ አለው ብለዋል።

እንደ አቶ ግርማ ገለጻ፤ በዓሉን በአንድነትና በአብሮነት ስሜት ማክበር ከማህበራዊ ጠቀሜታው ባለፈ ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃትና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት አወንታዊ ሚና አለው።

በዓሉ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንደሚያግዝ በተደጋጋሚ ታይቷል ያሉት ደግሞ የገዳ ሥርዓት አስተማሪና አማካሪ የሆኑት አቶ ጫላ ሶሪ ናቸው።

እንደ አቶ ጫላ ገለጻ፤ በዓሉ የሀገር ውስጥ ቱሪዝምን ለማነቃቃትና ከታዳሚዎች መስተንግዶ የንግድ ገቢን ለማሳደግ ያለው ጠቀሜታ የጎላ ነው፤ ከኢኮኖሚ ግብይቱ ጋር ተያይዞ ዜጎች የሚተዋወቁበትና የሚግባቡበት ዕድልም አለ ሲሉ አስረድተዋል።



ደረጄ ፉፋ(ዶ/ር)



አቶ ጫላ ሶሪ

በመሆኑም አንድነት ሲባል ማህበራዊ ክንውኖችን ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮችንም ያካተተ ነው ያሉት አቶ ጫላ፤ የበዓሉን ውጤታማነት ለማሳደግ ሰላማዊ እንቅስቃሴዎችን ብቻ መከተል እንደሚገባ አመላክተዋል።

በዓሉ በሚከበርብት ቦታ ከባህሉ ያፈነገጡና ለፖለቲካ አሻጥር የሚነሱ እኩይ ተግባራት መቃወምና ጥፋተኞችን ማጋለጥ ይገባል፤ ከዚህ ባለፈ አንድነትን በማጠናከር የጥፋት ዓላማዎችን በጋራ መከላከል ያስፈልጋል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ከግንዛቤ እጥረት አንጻር የሚከሰቱ አንዳንድ ችግሮችን በማስወገድ ትክክለኛ ባህላዊ እሴቱን የተከተለ በዓል ማክበር እንደሚያስፈልግ አመላክተው፤ በዓሉ ለህዝቦች አንድነትና አብሮነት መጠናከር የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ይበልጥ ማሳደግ እንደሚገባ አስገንዝበዋል።



# ኢሬቻ ኢትዮጵያን ለዓለም ማህበረሰብ በበጎ ጎኗ ለማስተዋወቅ የሚያስችል በዓል ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል ኢትዮጵያን ለዓለም ማህበረሰብ በበጎ ጎኗ የሚያስተዋውቅ ትልቅ በዓል ከመሆኑም ባለፈ ገቢን በማመንጨት ሰፊ ዕድል ያለው መሆኑን የአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አበራ ብሩ ዶ/ር ገለጹ።

አበራ ዶ/ር ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ ኢሬቻ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገርን ሊገልጽ የሚችል አንድ እሴት ነው። በዓሉ እንደ ሀገር ሕዝቦችን ያስተሳስራል፣ ያገናኛል፣ አንዱ ለሌላው አጋሩ፣ ወገኑ መሆኑን ያስገነዝባል።

ኢሬቻ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች የሚሳተፉበትና ከኦሮሞ ማሕበረሰብ ባለፈም እያደገ የመጣ ነው ያሉት አበራ ዶ/ር፤ በዓሉ ለኢትዮጵያውያን ሰፊ ዕድል ይዞልን መጥቷል ብለዋል። የአብሮነት፣ የፍቅር፣ የሰላም በዓል የሆነው የኢሬቻ በዓል ኢትዮጵያን መሰል ዓይነት እሴቶች እንዳሏት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ አድርጎ በማስተዋወቅ የራሱ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

በሀገር ደረጃም በርካታ የማሕበረሰብ ክፍል የሚንቀሳቀስበት እንደመሆኑ የሀገር ኢኮኖሚን ሊያጎለብት እና ሊያሳድግ የሚችል ዕድል መሆኑንም ተናግረዋል።

አበራ ዶ/ር እንደተናገሩት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪም በዓሉ ገቢ የሚያመነጭ መሆኑን በመገንዘብ እንደ ዕድል መውሰድ ይኖርበታል። የበዓል አልባሳት ሽያጭ፣ ከማደሪያ ቦታዎች ኪራይና ከተለያዩ ሽያጮች የሚገኝ ገቢ ሰፊ ጠቀሜታ እንዳለውም ጠቁመዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ በዓሉ በዋናነት ባለፈው ክረምት የተራራቁ ሰዎች ክረምቱ አልፎ ወንዝ ሲቀንስላቸው በሰላም ቆይተው በመገናኘታቸው ለአምላካቸው ምስጋና የሚያቀርቡበት በዓል ነው። ከመከራ ወደ ጥሩ መሸጋገሪያ ተምሳሌት ተደርጎ ይቀርብበታል።

በማህበራዊ ሚዲያ የሚተላለፉ እና እንደስጋት የሚነሱ ነገሮች ትክክል አይደሉም ያሉት አበራ ዶ/ር፤ ኢሬቻ የሚያቀራርብ፣ የሚያፋቅር፣ ሰላም የሚሰጥ እንጂ የሚያጨቃጭቅ፣ የሚያጋጭ፣ የሚያጠራጥር በዓል አይደለም፤ ሁሉም ሰው የግሉን እና የአካባቢውን ሰላም እየጠበቀ በዓሉን ማሳለፍ አለበት ብለዋል።

“ኦሮሞ ፍቅር ነው፣ አስታራቂ ነው፣ በልቡ ተንኮል የለውም” ያሉት ሀደ ሲንቄ ዘይቱን አደም፤ ኦሮሞ አቃፊ፣ አስታራቂ፣ ፍቅር እና ሰላም የሆነው መነሻው እና መድረሻው የኢሬቻ በዓልን ተመስርቶ መሆኑንም አመልክተዋል።

ኦሮሞ ጉዲፈቻ ወስዶ ሲያሳድግ ብሔሩን አይጠይቅም፣ የሚያምነው ሰው መሆኑን ብቻ ነው። ባህሉም እንግዳ ተቀባይ ነው። ኢሬቻ ብሄር ቋንቋ አይለይም፣ አንድነትን የሚሰጥ የሰላም በዓል ነው ብለዋል።

ከእንዶዴ ወረዳ በሆረ ፊንፊኔ በዓል ላይ ለመታደም የተገኘው ፍቃዱ በንቲ፤ ኢሬቻ በዓል አንድነት የሚቀነቀንበት፣ ሰላም የሚነገርበት፣ የተጣሉና የተኮራረፉ የሚታረቁበት፣ ሙሉ ክረምት በሰላም አሳልፈናል፤ በጋውንም ሰላም እንዲያሰፍን ፈጣሪን የምንለምንበት በዓል ነው ብሏል።

በዓሉ ከመላው ኢትዮጵያውያን አልፎም ለዓለም ማህበረሰብ አስፈላጊ ነው። አንድነትና ሰላም የሚጠራበት በዓል እንደመሆኑም ሰላም የሆነውን በዓል መውደድ ያስፈልጋል። ሰላም፣ ፍቅር፣ ደስታ እንዲሆን በንጹህ ልቦና እግዚአብሄርን ለመለመን ነው የሚኬደው። ቂም ቋጥሮ አይከበርም። ኢሬቻ በዓል ላይ የሚታደም ሰው የተጣላውን ታርቆ መታደም አለበት ሲልም አስተያየቱን ሰጥቷል።

# ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም ክብረበዓል ነው

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ ፡- ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የመላው ዓለም ክብረበዓል ሆኗል ሲሉ የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ተናገሩ። በኢሬቻ ላይ ያተኮረ ፎረም በትናትናው እለት ተካሂዷል።

በፎረሙ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ እንደገለጹት፤ አሁን ላይ ኢሬቻ በኦሮሞ ህዝብ ብቻ የሚከበር ሳይሆን የዓለም ጭምር ክብረ በዓል ሆኗል።

አቶ ሽመልስ እንዳሉት፤ ኢሬቻ የሰላም ፣ የይቅርታ፣ ሰው ከፈጣሪው ጋር የሚታረቅበትና ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት የምስጋና በዓል ነው።

ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ተፈጥሮን ውብ አድርጎ የፈጠረውን ፈጣሪ የሚያመሰግንበትና የሚያከብርበት በዓል መሆኑን የጠቀሱት አቶ ሽመልስ፣ የተጣላ ጸቡን በይቅርታ የሚሽርበት፣ የሰላም፣ የአብሮነት እና የአንድነት መገለጫ ነው ብለዋል። እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ ፤ በኢትዮጵያ ብዙ ባህሎች አሉ ፤ አንድነትን በብዝሃነት ውስጥ በተጠናከረ መልኩ ለማምጣት እየሠራንም እንገኛለን።

በአሁኑ ወቅት የኢሬቻን በዓል ከጫፍ እስከ ጫፍ ሁሉም ኢትዮጵያውያን እያከበሩት ይገኛሉ ሲሉም ጠቅሰዋል ።

ሀገራችን ከድህነትና ኋላ ቀርነት እንድትላቀቅ ሁላችንም ራሳችንን በራሳችን ሆነን የጋራ የሆነውን ኢትዮጵያዊነት ከፍ ለማድረግ ልንሠራ ይገባል ያሉት ፕሬዝዳንቱ ለዚህ በጎ ተግባር ደግሞ ኢሬቻ ትልቅ ሚና አለው ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና የከተማው ነዋሪ የኢሬቻ በዓል በደመቀ ሁኔታ እንዲከበር እያደረጉ ስላሉት አስተዋጽኦም ከፍተኛ ምስጋና አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በሕብረ ብሄራዊ ማንነት የደመቀች ልዩ ልዩ ባህሎችና ማንነቶች ያቀፈች ሀገር መሆኗን ጠቁመው፤ ከእነዚህም መካከል በኦሮሞ ማህበረሰብ ዘንድ የሚከበረው የኢሬቻ በዓል አንዱ ነው ብለዋል።

በዓሉ በዋናነት የኦሮሞ ማህበረሰብ ለፈጣሪ ምስጋና የሚያቀርብበት ሲሆን ፍቅር፣ ሰላም፣ ይቅርታና አንድነት የበዓሉ መገለጫ እሴቶች ናቸው ብለዋል።

ኢሬቻ የኢትዮጵያውያን ህብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትና የአንድነት መገለጫ በዓል ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ኢሬቻ ያለምንም ልዩነት የሚከበር የሁሉም በዓል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ስለሆነም የኦሮሞ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ብሄር ብሄረሰቦች በጋራ የሚያከብሩት የጋራ እሴት መሆን ችሏል ሲሉ ተናግረዋል።



ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ



ፎቶ፦ ገባቦ ገብሬ

አቶ ሽመልስ አብዲሳ

# ኢትዮጵያ ለስደተኞችና ተመላሾች ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች ነው

## - ስደተኞች ብሔራዊ መታወቂያ እንዲያገኙ የሚያስችል ስምምነት ተፈርሟል

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለስደተኞችና ተመላሾች ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሠራች መሆኑ ተገለጸ። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን ስደተኞች ብሄራዊ መታወቂያ እንዲያገኙ የሚያስችል ስምምነት በትናንትናው እለት ተፈርመዋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ጠይባ ሀሰን በስምምነቱ ላይ እንደገለጹት፣ የመግባቢያ ስምምነቱ እንደ አፍሪካ የመጀመሪያ ሲሆን ይህም ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው።

እንደ ወይዘሮ ጠይባ ገለጻ፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያ ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የምትሰጠውን ትኩረት የሚያሣይ ነው።

በዚህም በሀገሪቱ የሚገኙ ስደተኞች ከዜጎች እኩል በሀገሪቱ ማንኛውም አይነት የተሟላ አገልግሎት በየትኛውም ቦታ ሆነው በጥራትና በፍጥነት እንዲያገኙ የሚያስችል ነው። ይህም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

ወይዘሮ ጠይባ እንደገለጹት፤ ስምምነቱ ኢትዮጵያ ለስደተኞች ያላትን በጎ አመለካከትና ተቀባይነት የሚያሳይ ብሎም ትልቅ የዲፕሎማሲ ምእራፍ መሆኑን ተናግረዋል።

በብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ዮዳሄ ዘሚካኤል በበኩላቸው ፤



ስምምነቱ በሀገሪቱ የሚገኙ ስደተኞች የዲጂታል ብሄራዊ መታወቂያ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው።

ስምምነቱን የተስማሙት ተቋማት የጋራ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋሉ። ይህም ለታወቁ ስደተኞች የሚያፈልጋቸውን አገልግሎቶችን እንዲያገኙ እና ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ መሆኑም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ስደተኞችን ተቀብላ የምታስተናግድ ሀገር ስትሆን ለነዚህ ስደተኞች የብሄራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፋይዳ ቁጥር በመስጠት በተሰጣቸው የፋይዳ ቁጥር መሠረት የባንክ ደብተር ማውጣት፣ የመንጃ ፍቃድ ማውጣት እና የመሳሰሉትን የተለያዩ አገልግሎቶችን መጠቀም ያስችላል ሲሉ ተናግረዋል።

ይህም የስደተኞችን ሙሉ መረጃ ዲጂታል በሆነ መንገድ እንዲኖር በማድረግ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ስደተኞች ከዜጎች እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ይፈጥራል ብለዋል።

አቶ ዮዳሄ የብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራም ጽህፈት ቤት በ2015 ዓ.ም የዲጂታል መታወቂያ አዋጅ ጸድቆ ወደ ሥራ መግባቱን አስታውሰው ፤በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት 90 ሚሊዮን ዜጎችን የብሔራዊ መታወቂያ ባለቤት ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽን የኢትዮጵያ ተጠሪ አንድሪው ቦጎሪ በስምምነቱ ወቅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከ900 ሺህ በላይ ስደተኞችን ተቀብላ እያስተናገደች የምትገኝ ሀገር ስትሆን ይህ ስምምነት ስደተኞች ትክክለኛ ሰነድ በመያዝ የሚያፈልጋቸውን ማንኛያውም አገልግሎቶች እንዲያገኙ ይረዳል።

ለስደተኞች ሰብአዊ መብቶቻቸው ተከብሮ ተስማሚ ሁኔታ እንዲፈጠር የማድረግ ተግባር ቀጣይነት እንዲኖረው በጋራ እንደሚሰሩም አስታውቀዋል።

# የኢሬቻ በዓል የቱሪዝም ዘርፉን በማነቃቃት ዜጎችን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ያደርጋል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የኢሬቻ በዓል የቱሪዝም ዘርፍ በማነቃቃት በተለያዩ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንደሚያደርግ የኦሮሚያ ቱሪዝም ኮሚሽን አስታወቀ።

የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል "ኢሬቻ የአንድነትና የወንድማማችነት አርማ ነው" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ ሆረ ፊንፊኔና በቢሾፍቱ ሆረ ሀርሰዴ ይከበራል።


የኮሚሽኑ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኢፈባስ አብዱልዋሃብ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የዘንድሮው የኢሬቻ በዓል በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች የሚሳተፉበት በመሆኑ የቱሪዝሙን ዘርፍ በማነቃቃት በተለያዩ ዘርፍ የተሰማሩ ዜጎችን ተጠቃሚ ያደርጋል።

ክብረ በዓሉን ለማክበር ወደ ቢሾፍቱና አዲስ አበባ የሚመጡ ዜጎች የተለያዩ የምግብ፣ የመጠጥና የሆቴል አገልግሎቶችን ይጠቀማሉ ያሉት አቶ ኢፈባስ፤ በአገልግሎቱ ከ10 ቢሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ዝውውር ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

ኮሚሽኑ የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በበዓሉ እንዲታደሙ ኢሬቻን የማስተዋወቅ ሥራዎች ማከናወኑን ጠቁመው፤ በተለይም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በመሆን በቅንጅት ሥራዎች መከናወናቸውን ተናግረዋል።

የኢሬቻ በዓል በርካታ ዜጎች የሚሳተፉበት በዓል መሆኑን የገለጹት አቶ ኢፈባስ፤ በግል ከሚመጡ ቱሪስቶች በተጨማሪ በክብረ በዓሉ እንዲሳተፉ ከተለያዩ ሀገራት ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እንደሚሳተፉ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ለኢሬቻ ሳምንት ስያሜ በመስጠት



በሳምንቱ ውስጥ በዓሉ በተለያዩ መርሃግብሮች እንዲከበር መደረጉን ገልጸው፤ በበዓሉ የሚታደሙ ቱሪስቶችን ቁጥር እንዲጨምር የሚያስችል ሥራ መከናወኑን አስረድተዋል።

መስከረም ወር እንደሀገር የቱሪዝም ወር በመሆኑ የበዓሉ መከበር በራሱ በርካታ ቱሪስቶች እንዲታደሙበት የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

# ኢሬቻ- መልከብዙው የምስጋና በዓል

**ዳግማዊት ግርማ**

ወቅቱ መስከረም ነው። ምድር በተፈጥሮ አረንጓዴ ልባስ ተሸፍናለች። ክረምት ጨለማውን ትቶ ለፀሐይ እጅ ሰጥቷል። የተስፋ ነፋስ በከተማው ይነፍሳል። ወሩ የበዓላት ሀብታም ነው። ከሃይማኖታዊ እስከ ባህላዊነት ይዘልቃሉ። ከመስቀል እስከ መውሊድ ተከብሮበታል። በየስፍራው እንደ ባህሉ ዘመን ተለውጧል።

በገዳ ሥርዓት ተዳዳሪዎቹ ቤት ዛሬ ኢሬቻ ነው። በሆረ ፊንፊኔ ይከበራል። ነገ ደግሞ ቢሾፍቱ ላይ በሆረ ሀርሰዴ። በዓሉ ሚልዮኖችን ያሳትፋል። ፍቅር ጥላቻን ይረታል። ቂምና ቁርሾ ስፍራ የላቸውም። እርቅና ይቅርታ ይሆናል። ወንድማማችነት ይጸናል። የአንዱ ህመም ሌላውንም ያመዋል። ያለ እርቅ በዓል የለም። ቀኑ ጥል ይጣላበታል። ጠላት ለጠላው ልቡ ይራራል። ፍቅር እርቅ መዋደድ ይነግሳሉ። በእለተ ኢሬቻ ነገር ይቀናል።

የምስጋና ቀን ነው። ከሰው እስከ ፈጣሪ ይመሰገንበታል። በቀኑ ዋቃ ጉራቻ ምስጋና ይቸረዋል። ህዝቡ በባህሉ ደምቆ ተውቦ ይውላል። መልካሙ ሁሉ ይነግሳል። አረንጓዴ ሳር ይዞ ስለልምላሜው ምስጋና ይቸራል። በሳሩ ለምለምነት ላይ ተስፋውን ይኩላል። ስላለፈው በማመስገን ለመጪው መልካምነት ፈጣሪ ይለመንበታል። ደግነት ይዘመርበታል።

አባ ገዳ ጎበና ሆላ ይናገራሉ። የኦሮሞ አባ ገዳዎች ህብረት ፀሐፊ ናቸው። ለእርሳቸው በዓሉ ባለ ብዙ መልክ ነው። እርቅና ሰላም ይገለጥበታል። ውብ ሆኖ ስለተፈጠረው ተፈጥሮ ይመሰገንበታል። በረሃው ለተሞላው ውሃ ተርቦ ስለጠገበው ደስታ ይሆናል። በምስጋናው ሂደት ማንም አይዘነጋም። ጋራ ሸንተረሩ ዳገት ቁልቁለቱ ሁሉ ይታወሳል። ከቤት እስከ ዱር እንስሳው አይረሳም። ስለተመገበው ምግብ ምስጋና ይቸራል።

በበዓሉ ራስ ወዳድነት ስፍራ የለውም። መልካምነት መንገድ አለው። ወንድም ወንድሙን ያስባል። መተሳሰብ ይሆናል። አንዱ ያለ አንዱ ባዶነቱን ያውቃል። በወዳጅ እምባ ላይ የሚመሠረት ደስታ አይኖረውም። በወንድም ርሃብ የተጣደ ደስታ የለም። ህዝቡ ትልቅነቱን በሚመጥን መልኩ ይንቀሳቀሳል። በባህልና በራስ መኩራት ይነግሳል ብለዋል።

በዓሉ ወግና ሥርዓት አለው። በባህሉ መሠረት በገዳና በመልካ አባቶች በመመራት ይከበራል። አባቶች፣ ቄሮዎችና ቀሬዎች ተከባብረው ያከብሩታል። ኢሬቻ የኦሮሞ ህዝብ ከሌሎች ወንድም ህዝቦች ጋር በጋራ የሚያከብርበት ነው። ከፖለቲካ በጸዳ መንፈስ ይከበራል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳም ይናገራሉ። በእለቱ መቀያየም ቦታ የለውም ይላሉ። የተጣሉ ይቅርታ ይጠያየቃሉ። በዓሉ ሕዝቦችን ያስተሳስራል። አንድነትን ይፈጥራል። ኢኮኖሚን ለማጠናከርም ያግዛልም።

ኢሬቻ በቱሪዝም ዘርፍም ያለው ሚና ይህ ነው ተብሎ የሚገለፅ አይደለም። ግጭትን ማስወገጃ ዘዴም ጭምር ነው። ማኅበራዊ ትስስርን ይፈጥራል። ባህላዊ እሴቱን ይጠብቃል። ፈጣሪ ይመሰገንበታል። በማመስገን የሚከበር በዓል ነው። በዓሉ ማኅበራዊ እሴቱ የጎላ ነው። ሰዎች እርስ በእርስ ይዛመዳሉ። በበዓሉ ተገናኝተው የተዳዳሩም አይጠፉም። አብሮነት ይጎላል። አንድነት ያብብበታል። ያለፈ በደል ይተዋል። ስለመጪው ሰላም ይጸለያል።

በዓሉ ከኦሮሞ ሕዝቦች ባሻገር ሌሎችን ያሳትፋል። መሰል በዓላትን ማክበር ትርፉ የትዬሌሌ ነው። ሥርዓታቸውን ማጎልበትም ማኅበራዊ መስተጋብርን ያጠናክራል። ሀገርን በቱሪዝምና በኢኮኖሚ አቅም ለማጎልበት ስለመጥቀሙም አውግተዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሌላ አዋቂም ጋር አውግቷል። የኦሮሞ ባህልና ታሪክ ተመራማሪ ናቸው። አቶ አለማየሁ ኃይሌ ይባላሉ። በዓሉ በገዳ ሥርዓት ስር ተዳዳሪ መሆኑን ይገልጻሉ። የምስጋና ቀን ነው። ፈጣሪ በጋራ ይመሰገንበታል። ኦሮሞ በጋራ ወደ አደባባይ ወጥቶ አምላኩን ያመሰግናል። የክረምቱን ጨለማ አሳልፈህ የበጋውን ፀሀይ ስላሳየኸኝ ተመስገን እያለ።

አባ ገዳዎች ንግግር እና ምርቃት አላቸው። ይህ ንግግር ከማንም በላይ ተደማጭነት አለው። ህዝቡ የተነገረውን ሳይታክት ተግባር ላይ ያውላል። ሚሊዮኖች የሚሳተፉበት ትልቅ ፌስቲቫል ነው። በበዓሉ የኦሮሞ ሕዝብ የአንድነት ተምሳሌት ይሆናል። ባህሉን አክብሮ ያስከብራል። ደምቆ ይታያል። ታዳሚው ለሠላሙ ስኬት አሻራውን ያሳርፋል ብለዋል ተመራማሪው።

# «በእሴቶቻችን ዙሪያ ተሰባስበን፤ የሚያደናቅፉንን እንቅፋቶች በመንቀል ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ለመላ የኢትዮጵያ ህዝብ ባስተላለፉት የኢሬቻ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት፤ “ኢሬቻ የሰላምና የዕርቅ በዓል ነው! መላው የሀገራችን ህዝብ አስቸጋሪውን የክረምት ወቅት አልፋችሁ ውብ ወደሆነው የብራ ወቅት በመሻገራችሁ፤ እንኳን አደረሳችሁ” ብለዋል።

በማግኘት እና በማጣት፣ በጥጋብና በረሃብ፣ በስኬትና በውድቀት እንዲሁም በሙላትና በጉድለት ውስጥ ከእኛ ጋር የሆነውን ፈጣሪያችንን ማመስገን ባህላችን አድርገነዋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ ከሁሉም በፊት ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ችግሮችን ተቋቁመን፣ ትንሽ ትልቁን እንቅፋቶች አሸንፈን ብርሃናማውን ብራ እንድናይ ያስቻለን ፈጣሪ ይክበር፤ ይመስገን ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ለኢሬቻ ወደ መልካ ከመውጣት በፊት “ሰው ከፈጣሪው ጋር ሰላም ነው? ሰው እርስ በእርሱ ሰላም ነው?” የሚሉ ጥያቄዎች የተለመዱ ናቸው ። የተጣላና እላፊ የተነጋገረ፣ የተቃቃረ ሰው ለኢሬቻ ወደ መልካ ከመሄዱ በፊት እርስ በእርስ ይቅር ሊባባል ይገባል። ፈጣሪን ከማመስገን በፊት ከፈጣሪና ከፍጡራን ጋር መታረቅ የተለመደ መልካም እሴት ነው። በኢሬቻ በዓል ርጥብ ሳር በእጅ ይዞ፣ በጀማው ውበት ታጅቦ “መሬሆ መሬሆ ...” እያሉ ለፈጣሪ በሚቀርብ የውዳሴ ዜማ ወደ መልካ መትመሙ ኢሬቻ የኦሮሞ የአንድነቱ ተምሳሌትና የሰላም በዓል ነው።

በመሆኑም ኢሬቻን የሚያውቅ ሰው ቂምን ተጸይፎ ሰላምን ይሰብካል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ሰላምና አንድነት፣ ኅብረትና ወንድማማችነት መርሁ ነው፤ ከፈጣሪ ለተቀበለው ክቡር ስጦታ እውቅና ይሰጣል፤ የፍጡራንን ኅብርና አብሮነት እያደነቀ ለፈጣሪ ምስጋና ያቀርባል ብለዋል።

“ድሃውን በመስጠት ይደግፋል፤ የታረዘውን ያለብሳል፤ ማዕዱን በማጋራት አብሮ ደስታን ይጋራል። በኢሬቻ ውስጥ ያለው የሰላም ትርጉም በራስ ድንበር ዙሪያ ሰላም ከመሆንና በሰላም ከመኖር ባሻገር አርስ በእርስ መደጋገፍን በውስጡ ያካትታል” ሲሉም አብራርተዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ገለጻ፤ ኢሬቻ የፍትሕና የእኩልነት፣ የፍቅርና የአንድነት በዓል ነው። ኢሬቻ ታላቅ ጀማን የሚሰበስብ የገዳ ጥላ ፣ ወንድማማችነትንና አብሮነትን እንዲሁም የወንድማማች ሕዝቦችን ወዳጅነት ከፍ አድርጎ የሚያሳይ በዓል ነው። በእሴቶቻችንና በባህላችን ዙሪያ ተሰባስበን፤ እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ የሚያደናቅፉንን እንቅፋቶችን ሁሉ በመንቀል ዛሬ ላይ ሆነን ነገን የበለጠ ብሩህ ለማድረግ ጠንክረን ልንሠራ ይገባል።

ዘመኑ የበረከትና ጥጋብ፣ የሰላምና የእርቅ፣ ሠርተን ስኬትን የምንጎናፀፍበት፣ ዘርተን በሙቶ እጥፍ የምናጭድበት እንዲሆንልን እመኛለሁ፤ በስኬት አንገታችንን ቀና የምናደርግበት ዘመን፣ ቂምና ጉስቁልናን አሸንፈን የሕዝባችንን ዕውቀትና ታላቅነት ለዓለም የምናሳይበት ዘመን ይሁንልን ሲሉም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ፤ “እንደ ኢሬቻ በዓል ያለውን ታላቅ ሥርዓት አንድነታችንን የሚያጠናክር መሣሪያ አድርገን በመያዝ፣ ከቅርብም ከሩቅም በብልጽግና ጉዟችን ላይ የሚቃጣውን ወጥመድ ሁሉ ሰባብረን የያዝነውን ዓላማና ራዕይ የምናሳካበት የታሪካዊ ጉዞ ዘመን ይሁንልን” ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ኢሬቻ ስአብሮነትና ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ኢሬቻ አባገዳዎች፣ ወጣቶች፣ አባቶች፣ ሴቶችና ህጻናት ያለ ልዩነት በጋራ በአደባባይ የሚያከብሩት በዓል ነው። በዓሉ ከመላው ኢትዮጵያ ከሚመጡ ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በጋራ የሚከበር በመሆኑ የሕዝቦች ትስስርን በማጠናከር የራሱ የሆነ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው እሙን ነው።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ የኦሮሞ ፎክሎርና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዶክተር ደረጀ ፉፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ኢሬቻ ቱባ ባህሉ ብሔር ብሔረሰቦችን የሚያሳትፍ በመሆኑ ለአብሮነት መጠናከር ጉልህ ሚና አለው።

የኢሬቻ በዓል አከባበር መሠረታዊ ዓላማው ህዝብን ለማቀራረብና የተቋረጡ ግንኙነቶችን ለማደስ ነው የሚሉት ዶክተር ደረጄ፤ በዓሉ ማህበራዊ መስተጋብሮች የሚዳብሩበትና ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚወገዱበት እንደሆነ ጠቁመዋል።

የኢሬቻ በዓል ሕጉንና ባህላዊ እሴቱን ጠብቆ ከተከበረ ለአብሮነት ያለው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ እንዳልሆነ የሚናገሩት ዶክተር ደረጄ ስለበዓሉ ምንነት በመገንዘብ በዓሉን የወንድማማችነት ዓርማ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል። ዶክተር ደረጄ አክለውም የኢሬቻ በዓል የህዝቦች አንድነት የሚጠናከርበት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር መቀራረብ የሚችልበት እንደሆነም ተናግረዋል።

በኦሮሚያ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የባህል እሴት ቡድን መሪው አቶ አላና ተሾመ በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የኢሬቻ በዓል ከፈጣሪ ጋር ግንኙነት መፍጠርና የሰው ልጅና ተፈጥሮ የሚገናኙበት ነው። በዓሉ የሚከበረው በጋራ መሆኑን ጠቁመው በዓሉን የኦሮሞ ሕዝቦች በጋራ እንዲሁም ከአጎራባች ክልል ሕዝቦች ጋር በአንድነት የሚከበር መሆኑን አመላክተዋል።

ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት በሆራ ሀርሰዴ በነበረው የኢሬቻ በዓል አከባበር ከሀላባ፣ ከሲዳማ፣ ከወላይታ፣ ከስልጤና ከጉራጌ በዓሉን ለማክበር ሲመጡ እንደነበር መመልከታቸውን አስታውሰው አሁን ላይ ይሄ በበለጠ አድጎ የተለያዩ ብሔር በሔረሰቦችና ክልሎች በዓሉን ከኦሮሞ ሕዝብ ጋር በጋራ ለማክበር እንደሚመጡና ይህም አብሮነትን በማጠናከር ትልቅ ድርሻ እንዳለው ተናግረዋል።

በዘንድሮ ዓመት ከጎረቤት ሀገራት ከኬንያ፣ ከታንዛንያ፣ ከኡጋንዳና ጅቡቲ ጭምር ኢሬቻን በጋራ ለማክበር እንግዶች እየመጡ መሆኑን የሚናገሩት አቶ አላና ይህ የሕዝብ ለሕዝብ አብሮነትና መተሳሰብን ለማጠናከር የሚደረግ ክንውን ነው ብለዋል።

በዓሉን በጋራ ማክበር ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ማስቆጠሩን የሚናገሩት አቶ አላና ከኦሮሞ ሕዝቦች አልፎ የኩሽ ሕዝቦች በጋራ አባያ ወንዝ ዳርቻ ሲያከብሩ እንደነበር ታሪካዊ ቁሳቁሶች እንደሚያመላክቱ አስረድተዋል።

በኦሮሞ የጥናትና ምርምር ማዕከል የታሪክ ቡድን መሪና የታሪክ ባለሙያው አቶ ግርማ ነመራ በበኩላቸው እንደሚገልጹት ኢሬቻ የእርቀ ሰላም ማውረጃና በአራቱም አቅጣጫ የሚኖር የኦሮሞ ህዝብ የሚገናኝበት በመሆኑ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጠናከር ያለው ሚና ታላቅ ነው።

በኢሬቻ የሚከወነው ቱባ ባህል አብዛኛው ብሔረሰብ የሚጋራው መሆኑን ጠቁመው በበዓሉ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ሥርዓቱን የሚታደሙ በመሆኑ በዓሉ ለሀገር አንድነት የማይተካ ድርሻ እንዳለው አብራርተዋል። እንደ አቶ ግርማ ገለጻ በዓሉ በአንድነትና በአብሮነት ስሜት ማክበር ከማህበራዊ ጠቀሜታው ባለፈ ለቱሪዝም ዘርፉ መነቃቃትና ለኢኮኖሚያዊ እድገት የማይተካ ሚና አለው።

በኦሮሞ ባህልና ቱሪዝም የኦሮሞ ባህል ማዕከል የባህልና ታሪክ ዘርፍ ዳይሬክተር አቶ አለማየሁ ኃይሌ እንደሚሉት ደግሞ እንደ ኢሬቻ ዓይነቱን መልካም እሴት በመጠቀም የተጎዳው እንዲካስ፣ የበደለውም እንዲክስ ማድረግ፣ የተከፋውንም ማስታረቅ ይቻላል። አንዱ ለሌላው የሚያስብ፣ የሚጠነቀቅ፣ የሚሳሳ እንዲሆን በማድረግ የተሳሳተውን ነገር ለመመለስም ይቻላል።

ኢሬቻ የእርቅ፣ ምልጃ እና የሠላም ቀን መሆኑን የሚገልጹት አቶ አለማየሁ እርቅ መውረድ ያለበት ከፈጣሪ ጋር ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ እርስ በእርስ መተራረም እና ወደሠላም ስምምነት መምጣት ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢሬቻ ማሕበራዊ መስተጋብርን እና የሕዝብ ለህዝብ ትስስርን በማጠናከር ረገድ የራሱ የሆነ ትልቅ ድርሻ አለው። ሕዝቦች የቋንቋና የእምነት ድንበር ሳይለያቸው ኢሬቻን ባሕሉንና እሴቱን እንደጠበቀ ለዘመናት ሲያከብሩ ቆይተዋል። ይህንን የሀገር እና የሕዝብ ሀብት የሆነውን ታላቅ በዓል እሴቱን ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ እየተሰራ ያለው ሥራ መቀጠል አለበት።



አቶ አረጋ ከበደ

# በአማራ ክልል ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ግጭት በቁጥጥር ሥር እየዋለ በመሆኑ የክልሉ ሰላም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል።

በክልሉ በርካታ አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም መስፈኑን ተከትሎ ሕዝቡ የሰላሙ ባለቤትና ደጋፊ ሆኗል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ የተፈጠረው ግጭት በንጹሃን ዜጎች ላይ ጉዳትን፤ በክልሉ ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴ ላይም ችግር እንዳስከተለ ተናግረዋል።

በክልሉ በርካታ አካባቢዎች የተፈጠረው የሰላም እጦት ሰብዓዊ ጉዳት፣ ምጣኔ ሀብታዊ ድቀትን እና ቁሳዊ ውድመትን አስከትሏል ያሉት አቶ አረጋ፤ የሕዝቡ አስተዋይነትና የጸጥታ ኃይሉ ትጋት ባይጨመርበት ኖሮ አደጋው የከፋ ሊሆን ይችል እንደነበር አመላክተዋል።

በክልሉ ተፈጥሮ የነበረው ግጭት በትምህርት፣ በጤናና በግብርና ሥራዎች ላይ የፈጠረው አሉታዊ ተፅእኖ ከባድ ነበር ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ አዝማሚያው የአማራን ሕዝብ መሠረታዊ ፍላጎትና ዕውነታ ከግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም ብለዋል።

የፌዴራል መንግሥት ከክልሉ መንግሥት ጋር በመተባበር ችግር በተፈጠረባቸው በሁሉም አካባቢዎች ላይ ሕግ በማስከበሩ ረገድ አይነተኛ ሚና ተጫውቷል ያሉት አቶ አረጋ፤ በዚህም በርካቶቹ አካባቢዎች ወደአንጻራዊ ሰላም መመለሳቸውና ይህም ለክልሉ ህዝብ የተከፈለ መስዋዕትነት መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አረጋ ገለጻ፤ በምርጫ የመጣን መንግሥት በኃይል ማንበርከክ እንደማይቻል ያረጋገጠ የሕግ ማስከበር ሥራም ተከናውኗል።

አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ይሄ የክልሉን ከተሞች በኃይል ለመቆጣጠር የሚደረግ ጥረት መኖሩን ጠቁመው፤ በሽምቅ ጥቃት በየደረጃው የመንግሥት የጸጥታ አካላትንና የፖለቲካ አመራሮች ላይ ጉዳት ለማድረስ ጫና የሚያሳድሩበት መንገድ አግባብ እንዳልሆነ ተናግረዋል።

አሁንም ቢሆን ይህ ኃይል ከድርጊቱ እስካልተቆጠበ ድረስ ሕግ የማስከበር ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ያነሱት አቶ አረጋ፤ የሕግ የበላይነት በማስከበር ሕዝቡም ሆነ መንግሥት ወደመደበኛ ሥራ እንዲመለስ ጠንካራ እንቅስቃሴዎች በመደረግ ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

የተለየ ሃሳብ እና ሰላማዊ የሆነ አማራጭ ያለው ሁሉ ሃሳቡንና አመለካከቱን የሚያራምድበት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገዶች ዝግ አለመሆናቸውንም አንስተው፤ ሕጋዊ የሆነ የመንግሥትን ሥልጣን በኃይል ለመቆጣጠር ማሰብ ግን ሕዝብን ለስቃይና ክልሉን ወደ ኋላ ከመመለስ ያለፈ ፋይዳ እንደሌለው አስረድተዋል።

ከሕግ ማስከበሩ ጎን ለጎን ሕዝብን በማሳተፍ በታችኛው የመንግሥት አስተዳደር የሚገኘውን የፖለቲካ አመራር መልሶ የማደራጀት ሥራ እንደሚቀጥልም አስታውቀዋል።

በተለያዩ አደናጋሪ የፖለቲካ እሳቤዎች በመሳሳት ወደ አላስፈላጊ ግጭት የሚገቡ ወንድሞች አርቀው ማሰብና ከድርጊታቸው መቆጠብ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

ስለዚህ ሁሉም የክልሉ ሕዝቦች በተለይም ወጣቶች የሰከነ እና ብስለት የተሞላበት አካሄድን በመከተል በአንድነት ለሰላም መቆም አለባቸው ሲሉ ርዕሰ መስተዳድሩ አሳስበዋል።

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ





# ‹‹የኢሬቻ በዓል አካታችነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ መጥቷል››

- አቶ አለማየሁ ኃይሌ
በኦሮሞ ባህል ማዕከል የባህልና ታሪክ ዘርፍ ዳይሬክተር

አስቴር ኤልያስ

የቀድሞው ሸዋ ክፍለ አገር፣ ኤጀሬ ወረዳ፣ አዲስ ዓለም ከተማ የትውልድ ስፍራቸው ነው። ከአንደኛ እስከ ዘጠነኛ ክፍል ያለውን ትምህርታቸውን የተከታተሉትም በዚሁ በአዲስ ዓለም ከተማ በአሁኑ መጠሪያው ኤጀሬ ጨንገሬ ትምህርት ቤት ነው። ከ9ኛ በኋላ ግን ከትውልድ አካባቢያቸው በቅርብ ርቀት ላይ ወደምትገኘው አዲስ አበባ በመምጣት እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርት በምስራቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሩ።

የዛሬው የዘመን እንግዳችን ከአንደኛ እስከ ዘጠነኛ ባሉ ክፍሎች ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ የሚታወቁ ሲሆን፤ ከየደረሱበት የክፍል ደረጃ ሁሉ የአንደኛነትን ቦታ ሳይለቁ እስከ ዘጠነኛ ድረስ መዝቀል የቻሉ ናቸው። በተለይም የ6ኛ እና የ8ኛ ክፍል ሚኒስትሪ ውጤታቸው ከመቶ 99 ነጥብ በመሆኑ በወላጆቻቸውም ሆነ በመምህራን ዘንድ ተወዳጅነት ያተረፉበት ጊዜ ነበር።

እንግዳችን አቶ አለማየሁ ኃይሌ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በከፍተኛ ደረጃ አጠናቀው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በቴክኖሎጂ ሳይንስ የተማሩ ሲሆን፣ በተማሩበት ዘርፍም ለአምስት ዓመት ያህል ማገልገል ችለዋል። ከአምስት ዓመት የሥራ አገልግሎት በኋላ ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር የማቅናት እድል አግኝተዋል።

በመሆኑም እንግዳችን ከዛሬ ሶስት አስርት ዓመታት በፊት በሌላ የትምህርት ዘርፍ በዩክሬን ተከታትለው በሶሽዮ ፖለቲካል ሳይንስ መመረቅ ችለዋል። እንደተመረቁም የመጀመሪያውን የሳይንስ ትምህርታቸው ሙሉ በሙሉ ወደማኅበራዊ ሳይንስ በመቀየር የሥራ ዓለሙን እንደገና ለመቀላቀል በታማኝነት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል።

እንግዳችን ማኅበራዊ ሳይንሱ ውስጣቸው ገብቶ ስለነበር የኦሮሞን እንዲሁም የኢትዮጵያንም ባሕል ማጥናቱን ተያያዙት። ምንም እንኳ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ባያሳትሙለትም የኢትዮጵያን ባህል ከኦሮሞ ጋር አያይዘው አጥንተዋል። የኦሮሞን ባህል በተመለከተ ግን ወደ ሰባት ያህል መጻሕፍት ለንባብ አብቅተዋል። ከሰባቱ አንዱ ደግሞ በሶስት ቋንቋዎች የተተረጎመ ጭምር ነው። በመረጃ አሰባሰብ ላይ ጓደኞቻቸውም የተሳተፉበት ሥራ ነው።

አዲስ ዘመን ከእኚህ ከአራት አስርት ዓመታት በላይ የካበተ የሥራ ልምድ ካላቸው እንግዳችን ጋር ቆይታ ማድረግን ወድዷል።

እንግዳችን አቶ አለማየሁ ኃይሌ፣ በኦሮሞ ባህልና ቱሪዝም የኦሮሞ ባህል ማዕከል የባህልና ታሪክ ዘርፍ ዳይሬክተር ሲሆኑ በተለይም በኦሮሞ ባህል ታሪክ ላይ ሰፊ ጥናትና በዘርፉም በተለያየ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመመስረት መጻሕፍትን ለአንባቢያን እነሆ ብለዋል። ከእርሳቸው ጋር የኢሬቻን በዓል በማስመልከት ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- ሶቬዬት ኅብረት ዩክሬን ለትምህርት በሔዱ ጊዜ ወደኢትዮጵያ የተመለሱት ትምርትዎን እንዳጠናቀቁ ነው?**

**አቶ አለማየሁ፡-** አዎ! ወቅቱ የደርግ ዘመን ስለነበር ብዙዎቹ ተማሪዎች ወደሀገራቸው መመለስን እምብዛም አይፈልጉም ነበር። እኔ ግን በዚያ ሀገር በፍጹም የመቅረት ፍላጎቱ አልነበረኝም። እውነት ለመናገር ሀገሬን እወዳታለሁ። ስለዚህም ትምህርቴን እንዳጠናቀቅሁ ወደኢትዮጵያ ልመለስ ችያለሁ።

በወቅቱ ‹‹እናታችሁ ትጠራችኋለች፤ ልጆቼ ድረሱልኝ እያለች›› የሚል መልዕክት ያዘለ አንድ የኦሮሚኛ ዘፋኝ ያቀነቅን የነበረው ሙዚቃ ውስጤ ይመላለስ ነበር። ይህ የመዝሙር ያህል ውስጥን የሚኮረኩር ሙዚቃ እንኳን ሀገር አስከድቶ ሊያስቀር ቀርቶ ልብን የሚያባባ በመሆኑ መቅረት ይሉት ነገር የማይታሰብ እንደነበር አስታውሳለሁ።

በመሆኑም ወደሀገሬ የተመለስኩት ያለአንዳች ማቅማማት ነው። በተለይም ‹‹እናታችሁ ትጠራችኋለች›› የሚለው የዘፈኑ ስንኝ ከአዕምሮዬ ያልጠፋ በመሆኑ ትምህርቴን ጨርሼ ያጠፋሁት ጊዜ የለም። እውነት ለመናገር በወቅቱ ሲሰማኝ የነበረው የምትጠራኝ ወላጅ እናቴ እንደሆነች ነበር። ከዚህ የተነሳ ወደ ሀገሬ ኢትዮጵያ የመጣሁትም በታላቅ ጉጉት ነው። መጥቼም ሀገሬን በታማኝነት ማገልገሉን ተያያዝኩት።

**አዲስ ዘመን፡- በተለይ የኦሮሞ ባህልና ታሪክን በመጻፍ ለተደራሲያን ማድረስ ችለዋል፤ የመጀመሪያ ስራዎም የሆነው እስከ 16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ያለው የኦሮሞ ታሪክ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው፤ ጅማሬውን በዚህ መልኩ ለመጻፍ የተነሳሱበት ዋና ምክንያትና ስለሌሎቹም መጻሕፍዎ ይንገሩን?**

**አቶ አለማየሁ፡-** በእርግጥ መጀመሪያ የጻፍኩት የኦሮሞ ታሪክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚል ነው፤ ሁለተኛው ሥራ ደግሞ የኦሮሞ ታሪክ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚል ነው። የኦሮሞ ታሪክ እስከ 16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሚለው የጻፍኩበት ዋናው ምክንያት አንዳንዶች ኦሮሞ ከ16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ እንደሌለ የሚናገሩ ስለነበሩ ነው። የእነርሱ አባባል እንዲህ እንዲህ ነው በሚል የማሳመን (Justify) የሚያደርግ ሳይሆን ሐሰት (Falsify) ስለመሆኑ የሚገልጽ ሥራ መሥራት ስለፈልኩ ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ የኩሽ ሕዝብ ነው። የኦሮሞ ሕዝብ በኢትዮጵያም በአፍሪካም ውስጥ ያለ ሕዝብ ነው እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት ከሌላ ዓለም የመጣ አይደለም። ይህ አባባላቸው ምናልባት ያለመረዳትና ታሪክ ያለማወቅ



ሊሆን ስለሚችል ግንዛቤው እንዲኖር በማሰብ ጭምር ነው ስራዬን መስራት የቻልኩት። እዚሁ ኢትዮጵያ እንዲሁም ምስራቅ አፍሪካ ያለ ሕዝብ ስለመሆኑ በመረጃ የተደገፈ ታሪክ ለንባብ ማብቃት ችያለሁ።

ከዚህ ሌላ የገዳ ሥርዓትን በመጽሐፍ አሳትሜያለሁ። ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በሶስት ቋንቋ ማለትም በኦሮሚኛ፣ በአማርኛ እና በእንግሊዝኛ ነው። በተጨማሪም የአዲስ አበባ (ፊንፊኔ) አመሰራረት እና የኦሮሞ ታሪክን የሚገልጽ መጽሐፍም ለንባብ አብቅቻለሁ። እንዲሁም የጨፌ ገዳ ሥርዓት በገላን ከተማ የሚል እና የኦሮሞ ወርጂዎች ታሪክ ከኦሮሞ ጋር ያላቸው ታሪካዊ አንድነትን የሚገልጽም እንዲሁ ከጻፍኳቸው ውስጥ የሚካተቱ ሥራዎቼ ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ለሕትመት በዝግጅት ላይ የሚገኝ ‹‹የገዳ ሥርዓት እና የኦሮሞ ወታደራዊ አወቃቀር›› በሚል ርዕስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው። ይህም መጽሐፍ በዚህ ዓመት ለንባብ ይበቃል ብዬ አስባለሁ። ይህን ጨምሮ ወደ ስምንት መጽሐፍት አሉኝ ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ዋና ርዕሳችን ወደሆነው የኢሬቻ በዓል እንምጣ፤ በመጀመሪያ ኢሬቻ ምንድን? መከበር የተጀመረውስ መቼ ነው?**

**አቶ አለማየሁ፡-** በገዳ ሥርዓት ውስጥ በርካታ ተቋማት (Institutions) አሉ። ኢሬቻ ደግሞ በገዳ ሥርዓት ውስጥ ካሉት አንኳር ማኅበራዊ ተቋማት (Institutions) መካከል አንዱ እና ትልቁ ነው። ኢሬቻ የጋራ የምስጋና ቀን ነው። ኦሮሞ በጋራ ወደአደባባይ ወጥቶ አምላኩ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት በዓል ነው። ፈጣሪ አምላክ ከዝናባማው፣ ከጭጋጋማውና ከጨለማው ወቅት ወደ ብራው ወቅት ስላሸጋገረ ምስጋና የሚቀርብበት ነው። ወቅቱ የኦሮሞ ሕዝብ ተሰባስቦ ምስጋና የሚያቅርብበት እንዲሁም ስለበደለው ነገር እርቅ የሚጠይቅበት እና እጅ የሚነሳበት በዓል ነው።

ኦሮሞ በባህሉ ውስጥ ባሉት የክረምቱ ወራት የዘራው በቅሎ የሚያፈራበት፣ ያረባው ውጤታማ የሚሆንበት ወቅት በመሆኑ በዚያ ጊዜ ዝናብ ሊበዛ ይችላል፤ እንደዛ ከሆነ እግዚአብሔርን የሚጠይቀው ዝናቡን አቁምልን ብሎ ሳይሆን እርቅን አውርድልን በሚል ነው። ምንም እንኳ ወቅቱ ብራ የሚሆንበት ጊዜ ቢሆንም ከዚያም በኋላ ከመጠን በላይ የሆነ ዝናብ ሲጥል የተዘራውን ያበላሻል፤ ከብቱን መውጫ ያሳጣል፤ መሻገሪያ ድልድዮችን ይሰብራልና ይህ እንዳይሆን ‹‹አምላክ ሆይ ታገሰን›› ሲል ኦሮሞ ፈጣሪውን የሚለምንበት በዓል ነው። ከዚህም የተነሳ ኢሬቻ በጋራ በመሆን ፈጣሪ የሚመሰገንበትና

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ

## ‹‹የኢሬቻ በዓል አካታችነት ከጊዜ ወደ ጊዜ...



ከገጽ 6 የዞረ

ምልጃ የሚጠየቅበት ቀን ነው ማለት ይቻላል።

በኢሬቻ በዓል ላይ የሚከወነው ሥርዓት ከሃይማኖታዊው ይልቅ ሚዛኑ የሚደፋው ባህላዊው ላይ ነው። ይህን ያልኩበት ምክንያት ከአለባበስ ጀምሮ በቡድን በቡድን በመሆን የሚደረገው ባህላዊ ዘፈን ሁሉ ስላለበት ጭምር ነው። በበዓሉ ላይ የተለያየ ኃይማኖት ተከታይ ስለሚታደምበት ባህላዊ ገጽታው ላቅ ብሎ ይስተዋላል። ከዚህ የተነሳ የምስጋናም የባህልም ቀን ነው ማለት ይቻላል።

መቼ ነው የተጀመረው ላልሽው በጥንት ዘመን የነበሩ ከኩሽ አባቶቻችንና እናቶቻችን ጊዜ ጀምሮ የነበረ ክዋኔ ነው። አንድ ምሳሌ ላንሳልሽ፤ በኦሮሞ ዘንድ ‹ወድቃ በተነሳችው ዘር አምላክ› የሚባል ጽንሰ ሃሳብ አለ። አንዷት ፍሬ መሬት ላይ ወድቃ ስትነሳ ብዙ ፍሬ እንደምታፈራው ሁሉ የሰው ልጅም እንዲሁ ነው። ምክንያቱም የሰው ልጅም ከእግዚአብሔር የተሰጠው ፍሬ እናት ከወንድ ተቀብላ በማኅጸኗ ይዛ ሰው ወደምድር ይመጣል። ልክ ወድቃ በተነሳች ዘር አይነት እሳቤ እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ዘር በዚህ መልክ እየቀጠለ ያለበት ምስጢር ነው። ከዚህ ምስጢር የተነሳ ኦሮሞ ‹ወድቃ በተነሳች ፍሬ አምላክ› ይላል። የሰው ልጅም የሚገኘው በዚህ የትውልድ መቀጠል ምስጢር ውስጥ ነውና። ይህ ፍልስፍና የኦሮሞ ብቻ ሳይሆን የኩሽ ሕዝቦች ፍልስፍናም ጭምር ነው።

በጥቅሉ ግን ኢሬቻ የተጀመረው በዚህ ጊዜ ነው የሚል ድምዳሜ መስጠት ባይቻልም ለረጅም ጊዜ የቆየና ከጥንትም ጀምሮ ያለ ባህላዊ ክዋኔ እና ኃይማኖታዊ አተገባበር የሚታይበት በዓል ነው ማለት ይቻላል። በዚያን ወቅት ሁሉም ሕዝብና ጎሳ በየወንዝ ዳር፣ በየተራራ እና በየአካባቢው ኢሬቻንም እምነቱንም ያካሂዳል። የኦሮሞም ኢሬቻ የወጣው ከዚሁ ውስጥ ነው። ይህ ማለት ከብዙ ሺ ዘመናት በፊት ነው። እንዲያውም በገዳ አቆጣጠር መሰረት ኢሬቻ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ጀምሮ እንደሚከወን ይነገራል። ከዚህ የተነሳ ኢሬቻ ቀደም ብሎም እንደነበር መረዳት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ ከገዳ ሥርዓት ጋር ያለው መስተጋብር ምን ይመስላል?**

**አቶ አለማየሁ፡-** እንደጠቀስኩት ኢሬቻ ገዳ ውስጥ ያለ አንድ ተቋም ነው። ገዳ ደግሞ ሥርዓት ነው። ኢሬቻ ደግሞ በገዳ ውስጥ ያለ ማኅበራዊ እና በጋራ ፈጣሪ የሚመሰገንበት ክዋኔ ነው። ይህ ክዋኔ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሔድ ነው። ይኸውም በመልካና በኢሬቻ ቱሉ የሚካሄድ ማለት ነው። ማለትም በተራራ (ቱሉ) ላይ የሚካሄድ ኢሬቻ እና በጅረት (መልካ) አካባቢ የሚካሔድ የጋራ የምስጋና ቀን ማለት ነው። በተራራ (ቱሉ) ላይ የሚከናወነው በመጋቢት መጨረሻ ወር ነው። በዚያን ወቅት ፈጣሪ አምላክንን ‹ታረቀን!› የሚባልበት ጊዜ ነው። ‹በጋው በቅቷል፤ ከዚህ የተነሳ ሰውም ከብቱም እየተጎዳ ነውና ዝናብ ስጠን፤ እርዳን!› የሚባልበት ወር ነው።

መስከረም ወር መገባደጃ ላይ የሚካሄደው ምስጋና ደግሞ ከከባዱ ክረምት የወጣንበት ጊዜ በመሆኑ ‹ምስጋና ይገባሃል› ተብሎ አበባ ተይዞ ምስጋና የሚቀርብበት ወቅት ነው። በዚህ ወቅት የጨለማውን ወቅት አሳልፎ ፍሬ የሚያብብበት ጊዜ በማድረሱ ‹‹አምላካችን ታርቆናልና ምስጋና ይድረሰው›› በሚል የሚከበር በዓል ነው።

በገዳ ሥርዓት ውስጥ እንዳልኩሽ በርካታ ተቋማት አሉ። ልክ በመንግስት ስርዓት ውስጥ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ተቋማት እንዳሉ ሁሉ በገዳ ስርዓት ውስጥ ያለው የዚያ አይነት ነው ማለት ይቻላል። በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ተቋማት ሁሉ የሚያገለግሉት ማኅበረሰቡን ነው። አስቀድሜ እንደጠቀስኩት ከዚያ ውስጥ አንዱ ኢሬቻ ነው። ከዚህ ሌላ የቃሉ ተቋም፤ የጋብቻ ተቋም እና ሌሎች ተቋማትም አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ኢሬቻ በሰዎች መካከል ሰላም እንዲኖር ትልቁን ሚና የሚጫወት እንደሆነ ይነገራል፤ ከዚህ አንጻር ኢሬቻ ለሀገራችን ሰላም የሚጫወተው ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ አለማየሁ፡-** እንደሚታወቀው ኢሬቻ የጋራ ነው። የጋራ ኢሬቻ በሚካሄድበት ጊዜ በድቅድሚያ በአካባቢው የተቀያየመ ሰው ካለ እንዲታረቅ ይደረጋል። በአባ ገዳዎች፣ በአገር ሽማግሌዎች፣ በአረጋውያን ሴቶች ምክር ይሰጣል። ቁርሾ እና ቂም ይዞ ወደፈጣሪ የሚደረግ ነገር የለም። በመጀመሪያ ፈጣሪን ይቅርታ ከመጠየቃችን በፊት አጠገባችን ያለውን ሰው ይቅርታ መጠየቅና መታረቅን የግድ የሚል ሥርዓት ነው።

ከዚህ የተነሳ በመጀመሪያ የሚካሔደው የእርቅ ሥነሥርዓት ነው። ወደፈጣሪ መቅረብ እንዲያስችል በመታረቅ እጅ ለእጅ መያያዝ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በኢሬቻ በዓል ላይ የሚካሄደው እንዳልኩሽ የጋራ ምስጋና እና የጋራ ጸሎት ነው። በዚያን ሰዓት የሚካሄደውም ልመና፣ ‹ፈጣሪ ሆይ ታረቀን› የሚል ነው። ስለዚህ ቂም እና ቁርሾ ይዞ ወደፈጣሪ መቅረብ ስለማይቻል መታረቅ ነው።

ይህ አካሔድ ደግሞ አብሮ ለመኖር በጋራ የሚካሄድ እሴት በመሆኑ ትልቅ ትርጉም የሚሰጠው ነው። ከዚህ የተነሳ ለመታረቅና በአካባቢው ካለ ሰው ሁሉ ጋር ለመስማማት የኢሬቻ በዓል ትልቅ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን የሚወጣ እሴት ነው። በመሆኑም ጥል እንደማይፈልግ ይልቁኑ የተጣለ ካለ የሚታረቅበት መድረክ መሆኑ አንድ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል። ከዚህ የተነሳ ኢሬቻ ማኅበራዊ ፋይዳው የጎላ ነው። ሰላምንና አንድነትን ለመፍጠር የራሱን ላቅ ያለ ሚና መጫወት የሚችል ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢሬቻ በዓል ሲከበር የራሱ የሆኑ ፋይዳዎች እንዳሉት ይታወቃል፤ በተለይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**አቶ አለማየሁ፡-** በሁለቱም ዘርፍ የየራሱ ጥቅም አለው። ማኅበራዊውን ስንመለከት በጋራ የመኖር ዓላማ የሰነቀ ስለሆነ አብሮነትን የበለጠ የሚያጎለብት ነው። ወንድማማችነትንና እህትማማችነትንም ያጠናክራል።

በተለይ ሕዝብን በማቀራረቡ ረገድ ሚናው የጎላ ነው። በበዓሉ የሚታደሙት የተለያዩ እምነት ተከታዮች ናቸው። የሚመጡትም የኢሬቻ በዓል አከባበርን በቅርብ ለማየትም አብሮ ለማክበር እንደመሆኑ የመቀራረቡ ሁኔታ ይፈጠራል። አብዛኞቹ ጥንታዊ የኦሮሞ ባህል አከባበር ምን ይመስላል፤ ሥርዓቱስ እንዴት ይከወናል የሚለውን ለማየት እንደመምጣታቸው ከብዙዎች ጋር ኅብረትና ወንድማማችነትን ፈጥረው ይመለሳሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ በበዓሉ ስፍራ በመገኘት በጋራ በመሆን ፈጣሪውን ለማመስገን፣ ማንነቱንና ኦሮሞነቱን ለመግለጽ በሚደረገው ሁነት ትስስሩን ይበልጥ የሚያጠናክር ይሆናልና ማኅበራዊ ፋይዳው ከፍ ያለ ይሆናል። ከዚህ ባለፈም በቅርበት የመተዋወቅና የመጠያየቁ ነገርም የሚሰፋበት መድረክ እንደመሆኑ ቅርርቦሹ የሚጎለብትበት ነው። ወዳጅነት እና ፍቅርም የሚጠናከርበት ስፍራ ነው። ከዚህ የተነሳ ማኅበራዊ ጠቀሜታው ላቅ ያለ ነው ማለት ይቻላል።

ከዚህ አኳያ ዕለቱን የብሔራዊ ማንነት ቀን ነው ብሎ መውሰድም ይቻላል። ምክያቱም በዓሉ በኢትዮጵያም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ማንነት በስፋት የሚገለጽበት ዕለት እንደመሆኑ ልዩ የሚያደርገው ነው። ከኢትዮጵያ ውጭ በተለያየ እንደ አሜሪካና ሌሎች አገራት የኦሮሞ ልጆች ኢሬቻን ያከብራሉ። በዚያን ጊዜ የሚሰበከው ሰላም ነው። በዕለቱ የሚነገረውም የሚዘፈነውም ሰላምን የተመለከቱ እና ምስጋናን ስለሚገልጹ ጉዳዮች ነው።

ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ደግሞ የመጀመሪያው ወደ ኢሬቻ በዓል ሲኬድ አለባበሱ በራሱ የበዓሉ መገለጫ ቢሆንም ከኢኮኖሚ አኳያ የሚሰጠው ፋይዳ ላቅ ያለ ነው። ምክንቱም የተለያየ ባህል መገለጫ የሆኑ አልባሳት የሚለበስበትም ክብረ በዓል እንደመሆኑ ሁሉም እንደየፍላጎቱ ያንን የባህል ልብስ ይገዛል። በዚህ ጊዜ ያንን የባህል ልብስ ለገበያ የሚያቀርቡ አካላት ደግሞ ይኖራሉ። ከዚህ አንጻር ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን ሸያጩ በአገር ውስጥ የበዓሉ ታዳሚያን ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከውጭ አገር የሚመጡ ቱሪስቶችም በመኖራቸው እነርሱም የሚገበያዩበት እንደመሆኑ ለቱሪዝም ገበያውም ሚናው የጎላ ይሆናል። የኢሬቻ በዓል በሚካሄዱባቸው ከተሞች ሁሉ የግብይት ሥርዓቱና ሰንሰለቱ ከፍ ያለ ይሆናል። በየከተሞቹ ያሉ ሆቴሎችም ገበያቸው ከፍ ያለ የሚሆንበት ወቅት እንደመሆኑ የየከተሞቹ ገቢም የሚጨምርበት ጊዜ ይሆናል። ከዚህ የተነሳ ኢሬቻ በሀገር ውስጥ በሚደረገው ግብይት ላቅ ያለ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ ኢኮኖሚውን ለሚያመነጨው ለቱሪዝም ዘርፉ ትልቅ ሚና የሚጫወት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢሬቻ በዓል አካታችነቱ የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**አቶ አለማየሁ፡-** በጣም የሚያስገርመው አካታችነቱ ከጊዜ ወደጊዜ እየጎለበተ ነው። ከቀድሞው ደቡብ ኢትዮጵያ፣ በኋላ ላይ ራሳቸውን ችለው ከወጡ ክልሎች የኢሬቻን በዓል ለመታደም ይመጣሉ። ለአብነት መጥቀስ ካስፈለገ ከንባታ፣ ሀድያ፣ ሲዳማ እና ሌሎቹም በበዓሉ ለመታደም ከሚመጡት መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። ኢሬቻ ከእነርሱ ጋር የሚተሳሰርበት መገለጫም አለ። ምናልባትም በቋንቋ ካልሆነ በስተቀር በብዙ መንገድ ከኦሮሞ ጋር የመመሳሰል እሴት አለ፤ የእነርሱም የኦሮሞም ሽማግሌዎች ሲናገሩ እንደሚደመጠው ከሆነ ሕዝቡ አንድ እንደሆነና መነሻቸው ተመሳሳይ መሆናቸውን ማጤን ይቻላል።

ልክ ኦሮሞዎች በሲዳማ ፊቼ ጫምባላ ላይ እንደምንገኝ ሁሉ ሲዳማዎችም በኢሬቻ በዓል ላይ ለመገኘት ይመጣሉ። ስልጤውም ጉራጌውም ሌሎቹም የሚመጡ በመሆናቸው አካታችነቱ ላቅ ያለ ነው። በዚህ ብቻ የሚወሰን ሳይሆን ከአማራም ከትግራይም ከሱማሌም ክልል በመምጣት በዓሉን ይታደማሉ። የኢሬቻ በዓል ልክ በአውሮፓና በመሰል አህጉራት እንደሚካሄደው አይነት ካርኒቫል በኢትዮጵያ ሆኗል ማለት የሚያስችል ነው።

በዓሉን ለመታደም አዋሳኝ አገራት ያሉ የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ይመጣሉ። ለምሳሌ ከኬንያ የሚመጡት በየዓመቱ ነው። የእነርሱን ማንነት የሚገልጽ ነገር በበዓሉ ላይ ስለሚያዩም ደስተኞች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ብዙዎች እንደሚሉት የኢሬቻ በዓል ፈጣሪ ለሰው ልጆች ሰላምና ደኅንነትን እንዲሰጥ የሚለመንበትም ጭምር ነው፤ከዚህ አንጻር እንደሀገር ያለው ፋይዳ ምንድን ነው ?**

**አቶ አለማየሁ፡-** በኢሬቻ በዓል ላይ ግን አባ ገዳዎች የሚያደርጉት ንግግር እና ምረቃት አለ። አንድ የፖለቲካ አመራር ከሚናገረው አሊያም አንድ ታዋቂ ዶክተር ለበሽታ ፈዋሽ የሆነውን መድሃኒት ከሚናገረው በላይ የኦሮሞ ሕዝብ በአባ ገዳ የሚናገረውን ነገር ያዳምጣል። የትኛውንም በአባ ገዳ የሚነገርን ጉዳይ በአግባቡ የሚያዳምጥ ነው። ይህ የማዳመጥ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን የተነገረውንም ነገር በአግባቡ ከመፈጸም ጋር የሚያያዝ ነው። ታዳሚው ከሰላም ጋር ተያይዞ በባህላዊ መሪው የሚነገረውን ነጥብ አስተውሎ የሚተገብር ስለመሆኑ ጥርጥር የለውም።

ከዚህ አኳያ እኔ ልል የምችለው የፖለቲካ መሪዎች የተያዘው ታላቅ መርሀግብር ስኬታማ ይሆን ዘንድ አባ ገዳዎችን ቢጠቀሙ መልካም ነው እላለሁ። ሰላም ለማምጣት አባገዳዎች፣ የጎሳ መሪዎች፣ ኢያንቱዎችና ቃሉዎች በሕዝቡ ውስጥ ትልቁን ሥራ መሥራት አለባቸው። ምክንያቱም እኛ መልካም የሆኑ እና ለሰላም ምቹ የሆኑ እሴቶች ያሉን ነን። እነዚህ ትልቅ ተሰሚነት ያላቸው ናቸው። ይህ የኢሬቻ አይነቱ ታላቅ እሴት በሌሎቹም አካባቢዎች ያለ እሴት እንደመሆኑ እንደዚህ አይነቶችን በማቀፍ የተያዘውን ትልቅ እቅድ ስኬታማ ማድረግ አለባቸው።

ስለዚህም በየቦታው ያለውን እንዲህ አይነቱን መልካም እሴት በመጠቀም የተጎዳው እንዲካስ፣ የበደለውም እንዲክስ ማድረግ ይቻላል። የተከፋውንም ማስታረቅ ይቻላል። አንዱ ለሌላው የሚያስብ፣ የሚጠነቀቅ፣ የሚሳሳ እንዲሆን በማድረግ የተሳሳተውን ነገር መመለስ ይቻላል።

ይህንን መልካም ነገር አድራጊ የሆኑት ሁሉ እውነት ብቻ ይዘውና እሱን ብቻ መሰረት አድርገው እንዲሰሩ ለአባገዳዎችም ሆነ ለሌሎች ግንዛቤ መስጠት መልካም ነው። ምክንያቱም እንዳልኩሽ ሕዝቡ አባገዳዎችን ይቀበላል። አባገዳዎች የሚሉትን ሰምቶ በስምምነት ተቀብሎ ካበቃ በኋላ በጎን ሌላ ነገር የሚሰራ ከሆነ ደግሞ ከክህደት የሚቆጠር ነው።

ሰላም መፍጠር ማለት የአንድ ወገን እጣ ፈንታ ብቻ አይደለም፤ ሰላም መፍጠር በበዳይም በተበዳይ መካከል የሚደረግ ቃል ኪዳን እንደመሆኑ የሁለቱን ማለት የበዳይንም የተበዳይንም ስምምነት ግድ የሚል ነው። ብሔራዊ እርቅንም ብሔራዊ ሰላምንም ማካሄድ የሚቻለው በዚህ አይነት መንገድ ነው።

እርቅ በአንድ አካባቢ ብቻ ተፈጥሮ መወሰን ያለበት አይደለም፤ እርቅ ሲባል እንዳልኩሽ ብሄራዊ እርቅ መሆን አለበትና ሌላም ቦታ በተመሳሳይ ያንን የእርስ በእርስ ሰላም ለማውረድ ለዚህ ሥራ ዝግጁ መሆንን የሚጠየቅ ነው። በሁሉም የሀገራችን ክፍል ውይይት ተካሂዶ እና መግባባት ተፈጥሮ ሰላም እንዲወርድ ከሁላችንም ዘንድ የሚጠበቅ መልካምነት እንዳለ መጤን አለበት። በሌላው አካባቢም ሆነ በእኛ አካባቢ የሰላም አቅጣጫ እንዲያዝ አባገዳዎች በኢሬቻ በዓል ላይ የሚያስተላልፉት መልዕክት ትልቅ ዋጋ አለው። እሱ ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ለመታረቅ እንዲዘጋጅ፣ የተጣላም ቢኖር የአባገዳዎችን እና የሀገር ሽማግሌዎችን እንዲሁም የእናቶችን ተማጽዕኖ ወደጎን ሳይል ልቡን ለእርቅ እና ለሰላም ክፍት እንዲያደርግም የሚጠበቅበት ነው።

ሰላም ለሰው ልጅ ሁሉ ወሳኝ እንደመሆኑ ከዚህ ሰላም ላለመጉደል በፈጣሪ ፊት ለሰላም ራስን ዝግጁ ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው። ለዚህ ታላቅ ለሆነው የሰላም አጀንዳ በኢሬቻ በዓል ላይ የሚታደሙትን ሁሉ አባገዳዎች ዝግጁ ማድረግ የሚጠበቅባቸው እንደመሆኑ ምክራቸውንም በዚያው አጋጣሚ ማስተላለፍ አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ የኦሮሞ ባህል እና ታሪክ ተመራማሪ እንደመሆንዎ በቀጣይ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሥራው ስኬታማ እንዲሆን ለሕዝቡ የሚያስተላልፉት መልዕክት ምንድን ነው?**

**አቶ አለማየሁ፡-** ይህ የኢሬቻ ቀን አጋጣሚ ሆኖ የእርቅ፣ ምልጃ እና የሰላም ቀን ነው። እርቅ መውረድ ያለበት ከፈጣሪ ጋር ብቻ ሳይሆን በቅድሚያ እርስ በእርስ መተራረም እና እርቅ ማውረድ ነው። ኢሬቻ ይህን ማድረግ እንደሚገባ የሚያስቀምጥ ነው።

ይህ በመሆኑ ሕዝባችን ከተቀያየመ እርቅን ያውርድ፤ ቂም እና ቁርሾ ይዞ ረጅም መንገድ መጓዝ አይቻልምና ያንን ከጫንቃው ላይ አውርዶ ይጣል። ሁሉም ለሰላም መረጋገጥ ራሱን አዘጋጅቶ ለሕዝባችን እና ለሀገራችን ሰላም መስፈን የበኩሉን ሚና መጫወት አለበት።

በምድራችን የፈሰሰው የሰው ደም አለ፤ ያ ደም ደግሞ ወደፈጣሪ መጮሁ አይቀርም። ከዚህ የበለጠ የከፋ ነገር እንዳይኖር እና አንዱ ሌላውን የማይገድልበት ጊዜ እንዲሆን ሁሉ የኅብረተሰብ ክፍል ለእርቅና ሰላም መምጣት ራሱን ዝግጁ ማድረግ አለበት እላለሁ። አገራችን ለዜጎቿ የምትበቃ ናት፤ ከዚህ የተነሳ መገፋፋቱ ቀርቶ ወደ ሰላሙ እንምጣ። ለዚህ ደግሞ ለምክክሩና ለውይይቱ ራሳችንን ከወዲሁ እናዘጋጅ። ሰላም ሊመጣ የሚችለው በውይይት ውስጥ ነው። በደልን በመቁጠር ለብቻ በመገለል ሰላምን ማምጣት አያስችልም። ባለን መልካም እሴት ተነሳስተን የሀገር ሽማግሌዎች የሚሉንን ሰምተን ለተዘጋጀው የውይይት መድረክ ተሳትፏችንን በንቃት እናሳይ። ወደሰላም እንድንመጣ ዓይነልቦናችንን ያብራልን እላለሁ።

ፊታችንን ወደተዘረጋው የሰላም ተማጽዕኖ በማዞር የመተላለቅን ሂደት እንግታ፤ ደም መፋሰሱ እንዲቆም እንበርታ፤ እርስበእርስ መገዳደሉ ይቅር። ልጆቻችንን በሰላም ወደትምህርት ቤት ሄደው ይመለሱ፣ ማሳዎቻችን በዘር ይሸፈኑ። ከብቶቻችን በመስኩ ላይ ቦርቀው ይመለሱ። አስተማሪው ትውልድን ያለስጋት ይቅረጽ። ተመራማሪዎቻችን ወደምርመምር ይመለሱ። ሀገራችን ሰላም ትሁን። ሰላም ካለ ሁሉ ይኖራልና የማስተላልፈው መልዕክት ይህንን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡኝ ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ?**

**አቶ አለማየሁ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# በውጭ ምንዛሬና ጥሬ እቃ እጥረት

## የፈተነው የሕክምና ግብዓቶች ምርት

**እዮሩስ ተስፋዬ**

የኢትዮጵያ የሕክምና ግብዓት ፍላጎት ከ83 በመቶ በላይ በኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት በኩል እንደሚቀርብና 92 በመቶ የሚሆነው መድኃኒት ደግሞ ከውጭ ሀገራት እንደሚመጣ መረጃዎች ያሳያሉ። የተቀረው ስምንት በመቶ የሚሆነው መድኃኒት ከሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች የሚገዛ መሆኑንም ከኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት የተገኘ መረጃ ያመለክታል። ይህም በመድኃኒት እና በሕክምና ግብዓቶች በኩል እጥረትና የዋጋ አለመረጋጋት በስፋት እንዳለ ይጠቁማል።

አቶ ዮሴፍ አርጋው በሂዩማን ዌል ፋርማሲውቲካል ኢትዮጵያ ሊሚትድ የሥራ አስኪያጁ ረዳት ሆነው ይሰራሉ። እርሳቸው እንደሚሉት፣ ኩባንያው በመድኃኒት ዘርፍ ከፍተኛ መዋዕለ ነዋይ በማፍሰስ በአማራ ክልል ቱለፋ ከተማ እ.ኤ.አ በ2017 ተቋቁሟል። ኩባንያው ለሕይወት አድን፤ ለሚጥል ሕመም እና ሌሎችንም መድኃኒቶች ያመርታል። በአሁኑ ጊዜ 77 ዓይነት መድኃኒቶችን የማምረት ፈቃድና አቅም አለው። ይሁንና በጥሬ ዕቃ ግብዓት ችግር ምክንያት ሁሉንም መድኃኒቶች ማምረት አቅቶታል። በአሁኑ ጊዜ እያመረተ የሚገኘውም ሃያ አምስቱን ብቻ ነው። የውጭ ምንዛሬ እጥረቱም ፈተና ሆኖበታል። ለዚህም ከኢትዮጵያ ፋርማሲዩቲካል አገልግሎት ጋር በጋራ እየሰራ ይገኛል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ብሎም የዘርፉ ተዋናዮች ለሚገጥማቸው ፈተና መፍትሔ ለማስቀመጥ «ግንኙነትን መፍጠር፤ የአቅርቦትን ድልድይ በጋራ ለመገንባት» በሚል መሪ ቃል ሦስተኛው ዓለም አቀፍ የፋርማሲውቲካል አቅራቢዎች ጉባኤ በቅርቡ መካሄዱ ይታወሳል። የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለቱ ምቹ፣ ጠንካራና ጽኑ ግንኙነት የሚታይበት እንዲሆን እየተሰራ መሆኑንም የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አስታወቋል።

በዚሁ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአገልግሎቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ጥራታቸውና ፈዋሽነታቸው የተረጋገጡ መድኃኒቶችን ለ75 ዓመታት ሲያቀርብ እንደቆየ አስታውሰዋል። ከዚህ አንፃር የዜጎችን ጤና ለመጠበቅ የመድኃኒት አቅርቦት ሰንሰለቱ ምቹ፣ ጠንካራና ጽኑ ግንኙነት ያለው ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል። የአቅርቦት ሰንሰለቱ የተሳለጠ እንዲሆን ዓለም አቀፍ የመድኃኒት አቅራቢዎች ኮንፈረንስ እና ሌሎች የውይይት መድረኮች ጉልህ ሚና እንዳላቸውም አስምረዋል።

የአንድን ሀገር የብልጽግና ጉዞ እውን ከሚያደርጉ ጉዳዮች መካከል የጤና አገልግሎት ሥርዓቱን ማዘመን አንዱ መሆኑንም ጠቁመው፤ ዓለም አቀፍ የመድኃኒት አቅራቢዎች ኮንፈረንስም የውጭ ኢንቨስተሮችን ወደ ሀገር ውስጥ በመሳብ የሀገር ውስጥ አምራቾችና አቅራቢዎችን አቀራርቦ የመድኃኒት አቅርቦት ሥርዓቱ የተሳለጠ እንዲሆን እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፣ በዘመናዊ የአቅርቦት ሰንሰለት መስተጋብር ውስጥ ገዢ እና ሻጭ ያላቸው ግንኙነት በመርህ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ብለዋል። የግንኙነቱ መሠረት እንዳይዋዥቅና የጸና እንዲሆን በግዢ ውስጥ፤ ከቁሳቁሶች ልውውጥ በሻገር በመርህ ላይ ያተኮረ እና ዘላቂ መሆን ይኖርበታል ሲሉም ገልጸዋል።

የአገልግሎቱ የግዢ አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ንጉሴም የሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾች የሚጠቀሙትን ጥሬ እቃ ከውጭ ለማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንደሚያስፈልጋቸው ጠቁመዋል። አገልግሎቱም ወደ ሀገር ውስጥ መድኃኒት ለማስገባት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንደሚፈልግም ጠቅሰዋል። አገልግሎቱ ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሀገር ውስጥ መድኃኒት አምራቾችን የውጭ ምንዛሬ ችግር የሚፈታ መመሪያ ማዘጋጀቱንም ተናግረዋል።

አቶ ዳንኤል ዋቅቶላ የኢትዮጵያ የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ አምራቾች ማህበር ፕሬዚዳንትና የክሌጀስትሮ መድኃኒት ፋብሪካ መሥራች እና ባለቤት ናቸው። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ ከአምስት ዓመት በፊት የዓለም የጤና ድርጅት ያወጣውን ደረጃ የሚያሟሉ ፋብሪካዎች በሀገር ውስጥ አልነበሩም። አሁን ላይ ግን አምስት ደርሰዋል። ይህም ትልቅ ስኬት ነው። መድኃኒትና ለሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን ማምረት ከፍተኛ እውቀት፣ ቴክኖሎጂ እና ገንዘብን ይጠይቃል። ይህንን ወደ ሀገር ውስጥ ለማምጣት ከፍተኛ ጥረትና ትብብር ይጠይቃል። በመንግሥት በኩል ፖሊሲዎች ተቀርጸዋል። ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር ግን ወደኋላ የመቅረት ነገር ይታያል።

አቶ ዮሴፍ አርጋው በበኩላቸው ከ95 ከመቶ በላይ ጥሬ ዕቃዎች የሚገቡት ከውጭ መሆኑን ጠቁመው፣ የዶላር እጥረት ቢያጋጥም ከእናት ኩባንያ ድጋፍ በማግኘት በፍራንኮ ቫሉታ (ሕጋዊ ከሆነ ምንጭ የሚገኝ የውጭ ምንዛሬ) በማስገባት እና በመቀየር ሥራው እየሄደ ይገኛል። የትራንስፖርት ዋጋ ጭማሪ፣የዶላር ዋጋ በየጊዜው መጨመር፤ የዓለም አቀፍ ገበያው ላይ የሚያደርሰው አስተዋጽኦም ቀላል የሚባል አይደለም። በዚህም ብዙዎች ድርጅቶቻቸውን ዘግተዋል። አገልግሎቱ የሚያወጣውን ጨረታ በማሸነፍ ከሚገኘው 55 በመቶ ዶላር ጥሬ እቃ አምጥቶ በገበያ ላይ ለመቀጠል ጥረት እየተደረገ ነው።

እንደ እርሳቸው ማብራሪያ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ ጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት አዲስ መመሪያ በማውረዳቸው ችግሮች በተወሰነ መልኩ ቀለዋል። ጨረታውን ለሚያሸንፍ አካል 55 በመቶን ከመንግሥት ማግኘት የሚቻልበት አሠራር መዘርጋቱም መንግሥትን ያስመሰግነዋል። ይሁን እንጂ አብዛኛው ጥሬ ዕቃ ከውጭ የሚገባ መሆኑን በማጤን፤ ሌሎችም መዋለ ነዋያቸውን በማፍሰስ ወደ ሀገር እንዲመጡ ሲጋበዝ፤ ፈዋሽ የሆኑ መድኃኒቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ቢደረግ፣ መድኃኒት ከሚያመርቱ ድርጅቶች በተጨማሪም ጥሬ ዕቃውን ማምረት የሚችሉ ድርጅቶች ወደ ሀገር ውስጥ ቢገቡ ችግሮችን በሚገባ ያቃልላሉ።

የአገልግሎቱ የግዢ አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ንጉሴ እንደሚናገሩት፣ የሀገር ውስጥ አምራቾች ሀገር ውስጥ ያምርቱ እንጂ ጥሬ ዕቃዎቹ ከውጭ የሚመጡ በመሆናቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ይገጥማል። የጥሬ ዕቃውን ለማምጣት የሚወጣውን ዶላር ለማስታረቅ ከአምራቾች፣ ከማህበራት፣ ከግዢ ኤጀንሲ ከጤና ሚኒስቴር እና ከፋይናንስ ሚኒስቴር ጋር በጋራ በመሆን ለመድኃኒት አቅራቢዎች የጥሬ ዕቃ ችግራቸውን የሚፈታ መመሪያ ተዘጋጅቷል። ስለዚህ እንደሚያመጡት እሴት እስከ 55 በመቶ የዶላር አቅርቦት በጤና ሚኒስቴር በኩል እንዲመቻች ተደርጓል። ይህ በመሆኑ በቀጣይ ዓመታት ትልቅ እመርታ የሚያሳይ እና ብዙ መድኃኒቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ይረዳል።

የመድኃኒት እና የሕክምና መገልገያ አምራቾች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ዳንኤል በበኩላቸው፣ በአሁን ወቅት ለአገልግሎቱ እስከ 40 በመቶ የሚደርስ መድኃኒት ድርጅቱ እያቀረበ ነው። ይህም ለድርጅቱ ትልቅ አቅም አለው። ትንሽ ማስተካከያ ከተደረገ ደግሞ ወደ ውጭ የመላክ አቅም ይኖራል። ለዚህም የሚረዳ ምቹ ሁኔታ እና የሰው ኃይል እንዲሁም የመጓጓዣ አማራጮች አሉ።

አቶ ዳንኤል እንደሚገልጹት የውጭ ምንዛሬው እጥረት ከተቀረፈ ራስን ለመቻል ትልቅ ዕድል ይፈጥራል። ምሥራቅ አፍሪካ ውስጥ የሌሉ የመድኃኒት ፋብሪካዎች በሀገሪቱ እየተገነቡ ነው። ይህ ትልቅ አቅም ሲሆን ራስን ለመቻል ጠንክሮ መሥራት ይገባል።




**የኢትዮጵያ መድኃኒት አቅራቢ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አብዱልቃድር ገልገሎ፣**

የሕክምና እና የመድኃኒት ምርት ላይ ከሚታዩ ችግሮች የግንዛቤ እጥረት፣ የትብብር እና የቅንጅት ማነስ እንዲሁም ውሳኔዎችን በፍጥነት ያለመወሰን ችግር ይስተዋላል። በመሆኑም ፖሊሲዎች ወደ ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ከመንግሥት ጋር በጋራ መሥራት ይጠይቃል።

ሽሮፕ እና መሰል ምርቶች በጭራሽ ከውጭ ሀገር መምጣት የለባቸውም። ይልቁንም ከአስር ዓመት በኋላ ሀገሪቱ ከ60 እስከ 70 በመቶ በመድኃኒት ምርት እና በአቅርቦት ራሷን እንድትችል ተስፋ ማድረግ ያስፈልጋል። ምንም እንኳን አሁን ያለው የመድኃኒት እጥረት አሳሳቢ ደረጃ ላይ ቢደርስም በመንግሥት በኩል የሚታየው ቁርጠኝነት ይበል የሚያሰኝ ነው።

በየጊዜው የሚጨምሩ መድኃኒቶችም ይሁን የሕክምና ግብዓት ዋጋ ለመቀነስ ጥሬ ዕቃዎች፣ በሀገር ውስጥ ወደ ማምረት ሂደት መግባት ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ዘመናዊ መድኃኒት ማምረት ከጀመሩ ሀገራት አንዷ ነች። ሀገር ውስጥ የሚመረቱ እንደ ፓራሲታሞል እና የጸረ ተህዋስያን መድኃኒት በማምረት ልምድ አላት። አሁንም በመድኃኒት ምርት በስፋት መቀጠል ይኖርባታል።

አቶ ዮሴፍ እንደሚሉት፣ ከዚህ ቀደም ከነበረው ጋር ሲነጻጸር አሁን ላይ የሚያበረታቱ ብዙ ነገሮች አሉ። ለምሳሌ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ከግብር ነጻ (እፎይታ) መኖሩ እና ከውጭ የሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ከታክስ ነጻ እንዲሆኑ መደረጋቸውም ዘርፉን ለማበረታታት ከሚደረጉት መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

የአገልግሎቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን እንደሚሉት፣ የሀገር ውስጥ ምርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣት ከውጭ ሀገር የሚገባውን ይቀንሰዋል። የሀገር ውስጥ አምራቾች ቁጥር ለመጨመር ፖሊሲዎቹ እና አበረታች ነገሮች አሉት። ለአብነትም ጥሩ የኢንቨስትመንት ትኩረት እንዳለው ለማሳየት የኢትዮጵያ ፋርማሲውቲካል ኢንዱስትሪ ውስጥ ዝግጁ የሆነ የፋርማ ኢንዱስትሪ ፓርክ አለ። ከታክስ ጋር በተያያዘም ተያያዥ አበረታች አማራጮች አሉ።

ሌላው የሚነሰው ችግር የአቅርቦት ችግር ሲሆን የንግድ ሰንሰለቱን የጠበቀ አለመሆን በመድኃኒቶች ላይ የዋጋ መውጣት እና መውረድ (መዋዠቅ) እንዲፈጠር ማድረጉ ነው። በጥራት ላይ ግን የሚታይ ችግር የለም። ጥሬ ዕቃን በተመለከተ ግን በአሁን ወቅት መንግሥት ለሚገዛቸው መድኃኒት እስከ 55 በመቶ የውጭ ምንዛሬ እንዲገዛ የገንዘብ ሚኒስቴር አዲስ መመሪያ ማውጣቱ ኢንዱስትሪዎች እንዲነቃቁ እንደሚያግዝ የማህበራቱ ፕሬዚዳንት አቶ ዳንኤል ይገልፃሉ።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ግንኙነት ለማጠናከር እና ለማጎልበት በተሠሩ ሥራዎች ምንም እንኳን ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ ችግሮችን በአቅርቦት ሥርዓቱ ላይ መስተጓጎል የፈጠሩ መሆናቸውን ያስታወሱት ዶክተር ሊያ፤ የገጠሙ ተግዳሮቶችን ያህል የአቅርቦት መቆራረጥ እንዳይፈጠር ማድረግ እንደሚገባ ጉባኤው በተካሄደበት ወቅት አስረድተዋል።

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# ለክብረ በዓላቱ ብቻ ሳይሆን ለእሴቶቻቸውም

### የመጠቅለያው ማብረቅረቅ፤ የስጦታውን ዋጋ እንዳያሳንስ"፤

የስጦታ መጠቅለያ ከዋናው ይዘት ደምቆ የመልእክቱን ዋጋ እንዳያደበዝዝ ወይንም መሠረታዊው ጉዳይ ላይ ማተኮር ሲገባ ማጀቢያው ላይ ብቻ ቀልብንና አመኔታን ሙሉ ለሙሉ መጣል እንደማይገባ ለመግለጽ ሲፈልጉ ብዙ ሀገራት ከላይ የተጠቀሰውን መሰል አነጋገር በየቋንቋቸው አዳብረዋል። በእኛም ቋንቋ ውስጥ ቢሆን "ጋባዧ ዋንዛ፤ የምትወደሰው ብሳና" የሚሉት ዓይነት ተቀራራቢ ብሂላዊ አነጋገር እንዳለን ልብ ይሏል።

በዚህ ፀሐፊ እምነት የሀገራችን በዓላት በሙሉ በአግባቡ ተሰንደው ተደራጅተዋል ለማለት በፍጹም የሚያስደፍር አይደለም። ለምሳሌ፡- ከዓመት ዓመት በካሌንደር ከሚዘጉት አሥራ ሦስት ያህል ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ ብሔራዊ በዓላቶቻችን ውጭ ምን ያህል የማሕበረሰብና የአካባቢ ወይንም መንፈሳዊና ባህላዊ በዓላት እንዳሉን ለመዘርዘር የተመዘገቡ በቂ መረጃዎችን ያለ ድካም ለማግኘት ስለሚያዳግት "በየአካባቢው የሚከበሩት በዓላት ብዛታቸው ይህን ያህል ይሆናል" ብሎ ለመወሰን በእጅጉ ያዳግታል።

በየብሔረሰቡ፣ በማሕበረሰቡ፣ በየጎጡና በየመንደሩ ውስጥ ካሌንደር መዝግቦላቸው እውቅና አለማግኘታቸው እንጂ በርካታ የአካባቢ በዓላት ከብሔራዊ በዓላት ባልተናነሰ ደረጃ (ምናልባትም ባይበልጡ) በልዩ ድምቀትና አጀብ ሲከበሩ ይስተዋላል። ለጊዜው ስለይዘታቸው ለማመስገንም ሆነ ለመኮነን የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስላይደለ በጥልቀት አንተነትናቸውም።

ዋናውና ሊታወስ የተፈለገው መሠረታዊ ጉዳይ በብሔራዊ ደረጃም ይሁን በየአካባቢው ባህልና እምነት መሠረት በተወሰኑ የዐውዳዊ ትእይንቶች ማዕረጋቸው ከፍ ያሉ ሃይማኖታዊ ወይንም ባህላዊ በዓላት የመከበራቸው ፋይዳ ትርጉሙና ግቡ ምንድን ነው የሚለው ይሆናል። በዓላቱ በቁጥር ምን ያህል እንደሆኑ እንገምት ብንል መነሻ የሚሆነን ተቀራራቢ ግምት ለማግኘት ስለምንቸገር የምንግባባው "በመቶዎች ምናልባትም በሺህዎች" ሊገመቱ ይችላሉ በሚል ጥቅል አገላለጽ መደምደም እንችላለን። እነዚህ የሀገራችን ልዩ መገለጫ የሆኑ ባህሎችና በዓላት ምን አበርክተውልን ምን ነሱን? በጥሞና ልናስበብት ይገባል።

በየሃይማኖቶቹ የሚዘከሩና የሚወደሱ በዓላትን እንኳን ብንመለከት እንደ ቀኖናቸው፣ ዶግማና እምነታቸው ብዛታቸው ከዓመት ዓመት ሺህ ምንተ ሺህ ሊባሉ የሚችሉ ዓይነት ናቸው። ያውም በድርብና በድርብርብ በዓልነት።

በየአካባቢው የሚከበሩ ባህላዊ እምነቶችም እንዲሁ በቁጥራቸው ብዛት ብቻ ሳይሆን በይዘታቸውና በአከባበራቸው ሥርዓት ጭምር እንዲህ ነው ብሎ ስለ ብዛታቸውና ዓይነታቸው አፍ ሞልቶ ለመናገር ትናንት ስለምን እንዳልተቻለ፤ ዛሬም ለምን እንደማይሞከር ምክንያት ለመስጠት መጣደፍ በባህር ውስጥ የመዘፈቅ ያህል ሊከብድ የሚችል የተግዳሮት ፈተና ነው።

ባህል፣ በዓላትና እሴት ቤተሰባዊ ዝምድናቸው እስከ ምን ድረስ ይዘልቃል? የሚለው ጥያቄ የዚህ ጽሑፍ ማዕከላዊ የመወያያ ጭብጥ ነው። ቀጥሎ በምልዓትም ባይሆን በመሠረታዊ ደረጃ ሦስቱን ጽንሰ ሃሳቦች ለመነካካት ቢሞከርም በተለየ ምልከታ ግን "እሴት" የሚለው ዋና ሃሳብ ከባህልና ከበዓላት ጋር ያለውን መስተጋብር ዘርዘር አድርገን ለማሳየት እንሞክራለን።

### ባህልና በዓላት ምንና ምን ናቸው?

ባህል አንድ ሕዝብ ወይንም ወገን ለረዥም ዘመናት የእኔ ብሎ አክብሮ የያዘው ማሕበረሰባዊ ሀብቱና መገለጫው ነው። የሰውን ልጅ ሰብዓዊና ምክንያታዊ ፍጡር እንዲሆን ካስቻሉት ዋና ባህርያቱ መካከልም አንዱና ቀዳሚው ባለ ባህል የመሆን ብቃቱ ነው። ባህል በጥቅሉ ቁሳዊና መንፈሳዊ፣ የሚጨበጥና የማይጨበጥ ተብሎ ሊመደብ ይችላል።

የዘርፉ ባለሙያዎች የሰው ልጅ ከባህሉ ጋር ያለው ትስስርና ቁርኝት እጅግ የጠበቀ እንደሆነ አስረግጠው የሚናገሩት በበቂ ማስረጃ እየተነተኑ ነው። ሰው ያለ ባህል ልኑር ቢል ከሰብዕና ደረጃ ዝቅ ሊል እንደሚችልም ይከራከራሉ። ባህል በማሕበረሰቡ የእምነት፣ የአምልኮና ሌሎች ክንውኖች ጎልቶ ይንጸባረቃል። ከፉና ደግ፣ ቸርና ንፉግ፣ ቆንጆና አስቀያሚ፣ ርሁሩህ እና ጨካኝ ወዘተ. የመሳሰሉ ብያኔዎች የሚሰጡት አብዛኛውን ጊዜ በባህሉ መስፈርት መሠረት ነው።

ባህል በዕድሜ ማነስና ከፍታ፣ በጀግንነትና በፍርሃት፣ በአዋቂነትና ባለማወቅ ወዘተ. ሊገለጽና ሊንጸባረቅ ይችላል። ለምሳሌ፡- የሃይማኖት መሪዎች፣ የዕድሜ አንጋፋ አባቶችና እናቶች፣ ጀግኖች አርበኞች፣ የኪነ ጥበባት ባለሙያዎች፣ በሥነ ምግባር የተመሰገኑና አንቱታ ያተረፉ አርአያ ሰብ ግለሰቦች፣ በታሪክ የሚወሱ ተጠቃሾች፣ የመልካም ሥነ ምግባር አስተማሪ በሆኑ የተረት ገጸ ባሕርያት ሳይቀር ባህል ጎልቶ ሊንጸባረቅ ይችላል።

ባህል ከቤተሰብ፣ ከማሕበረሰብ፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ልምምዶች፣ ተምሳሌትነት ካላቸው ምልክቶች፣ ከትምህርት ሥርዓትና ከሀገረ መንግሥት የፖለቲካ አስተዳደር ወዘተ. ጋር ተሸርቦና ተጋምዶ ህልውና የሚሆን መንፈሳዊና ቁሳዊ የኅብረተረሰብ ሀብት ነው። ቁሳዊ ባህል በአመጋገብ፣ በመጠለያ አገነባብና በአኗኗር ዘይቤ፣ ለውበት ማድመቂያነት በሚውሉ ማጌጫዎች፣ ለግብርና በሚውሉ ቁሳቁሶች፣ እጀ ጠቢባን በሚገለገሉባቸው መሳሪያዎችም ወዘተ. ሊገለጽ ይችላል።

ማሕበራዊ ባህል በሰው ለሰው ግንኙነት ይወከላል። ለምሳሌ፡- ጓደኝነት፣ ቤተሰባዊና የእርስ በእርስ ግንኙነቶች በአብነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ፍልስፍናዊ ባህልም እንዲሁ ከአእምሯችን፣ ከስሜታችን፣ ከመንፈሳዊ ሕይወት አቋማችን ጋር የተያያዙና በሌሎች ላይ ተጽእኖ የምናሳድርበትን የግል መንፈሳዊ አቋምና ፍልስፍና አካቶ የያዘ ነው።

በዓላት በአንጻሩ ከባህል ውስጥ የሚያዘመሩ "ምርቶች" ናቸው። ባህልና በዓላት ብዙ ጊዜያት መስመራቸው እየደበዘዘ አንድም ሁለትም ሆነው በተለዋጭነት ሲገለጹና ሲተዋወቁ ይስተዋላል። በቀላል ማሳያ ለማመልከት ያህል ባህል በአጥር በተከበበ ሰፊ የመኖሪያ ግቢና ቤት ሲመሰል በዓላት ደግሞ የቤቱ አንድ ክፍል ወይንም ክፍሎች እንደሆኑ ቢታሰብ ጥቂትም ቢሆን ውስብስቡን ጽንሰ ሃሳባቸውን ለመረዳት ያግዝ ይመስለናል።

### ያልጠለሰው "የእሴት" ድንጋጌ፤

ትርጉሙ ተዛብቶ አገልግሎት ላይ ከሚውሉ የቋንቋችን "ድፍርስ" ጽንሰ ሃሳቦች መካከል አንዱ እሴት በቀዳሚነትና ያለማስተዋል ተደጋግሞ ሲንገላታ እንመለከታለን። በብዙ መንግሥታዊ ተቋማት ውስጥ "የመሥሪያ ቤታችን እሴቶች" ተብለው የሚዘረዘሩ እጅግ አማላይና አስጎምጂ ቃላትን በየግድግዳው ላይ በወርቃማ ቀለም ታትመው ማንበብ የተለመደ ነው። "ግልጽነት፣ ቁርጠኝነት፣ አጋርነት፣ ጥራት፣ ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣ ቅንነት፣ ታማኝነት፣ ባለጉዳይን ማክበር፣ የሙያ ሥነ ምግባር ወዘተ." የሚሉት እነዚህን መሰል የቃላት ድርድሮች በሙስናና ባለጉዳይን በማንገላታት ተለይተው በሚታወቁ መንግሥታዊና ሕዝባዊ ተቋማት ሳይቀር በተቋማቱ ሰሌዳ ላይ በጉልህ ፊደላት ተቀርጸው ማንበብ የባህል ያህል ተቆራኝቶናል።

የእሴት ትርጉም ከላይ ከጠቃቀስናቸው እውነታዎች በእጅጉ የተለየ ነው። እሴት ከባህል ውስጠኛው ክፍል ተፈልቅቆ የሚወጣና በጣዝማ ማር የሚመሰል የተፈተነ ተግባር ነው። ጣዝማ ማር አገልግሎቱ አንድም ለጥፍጥና አንድም ለመድኃኒትነት እንደሚውል ትንሽ ትልቁ ያውቀዋል። ይህንን ጠንንና ጠንከር ያለ ገለጻ ፈታ አድርጎ ማብራራቱ አስፈላጊ ስለሆነ በጥቂቱ እናፍታታው።

የባህል ተመራማሪዎች ባህልን የሚመስሉት ከቀይ ሽንኩርት ጋር እያመሳሰሉ ነው። ቀይ ሽንኩርት ቢልጡት የሚወጣው ልጣጭ እንጂ "ሥጋና አጥንት" የሚባል ባህርይ የለውም። አንዱ ልጣጭ ሲገፈፍ የሚከተለው ሌላ ልጣጭ ነው። ሽንኩርቱን እስከ መጨረሻው ልጠን እንጨርሰው ብንል ልጣጭ ከመግፈፍ ውጭ ምንም የተለየ አካል ማግኘት አይቻልም።

ባህል በሽንኩርት የተመሰለበት ዋና ምክንያት አንድን ግለሰብ ወይንም ማሕበረሰብ ዘልቀን ውስጡን "እየላጥን" እንፈትሽ ብንል በንብርብሩ ውስጥ የምናገኘው የቤተሰብን ተጽእኖ፣ የአካባቢ ወግና ሥርዓትን፣ የእምነት ተቋማት ያሳደሩትን የሕይወት ፍልስፍናና መርህ፣ በትምህርት ሥርዓቱ የተቀረጸን የአኗኗር ሥርዓት፣ የሀገረ መንግሥቱ ፖለቲካና መንግሥታዊ ሥርዓት ያሰመራቸውን መስመሮች፣ ከፍ ሲልም የዓለም አቀፍ ዋና ዋና ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት ያተሙትን አሻራ ነው። እነዚህ ሁሉ ተጽእኖ ፈጣሪ አካላት አሻራቸው ደምቆ የሚታየው የማሕበረሰቡ አባላት ልብ ተቀልብ ሆነው ተምረው ሕይወታቸውን ሊመሩበት በይሁንታ ስለተቀበሏቸው ነው።

እሴት ግን ከእነዚህ ንብርብር እውነታዎች የተለየ ነው። በንብርብር ከተመሰለው ከባህሉ ጠሊቅ ክፍል ስለሚቀዳም እውቀቱ የሚገኘው እየተለማመዱት ሳይሆን ሳይታወቅና በረቀቀ መንገድ ስሜትና መንፈሳችንን ገዝቶ ስለሚያስገብረን ነው። ይህንንም ረቀቅ ያለ ገለጻ በቀላል ምሳሌ ለማስረዳት እንሞክር።

በብሔራዊ ደረጃ የሚከበሩት ሕዝባዊና ሃይማኖታዊ በዓላቶቻችን የራሳቸው የአከባበር ባህልና ወግ አላቸው። መስቀልም ሆነ መውሊድ፣ ፋሲካም ሆነ አረፋ ወይንም ሌሎቹ ሲከበሩ በልዩ ሁኔታ የሚታወቁባቸው መለያ አላቸው። የምዕመናን አመጋገብ፣ አለባበስ፣ የግብዣው ዓይነትና የአደባባይ ትዕይንቶች ሁሉ እንደ በዓላቱ ባህል ሊለያይም ሊመሳሰልም ይችላል። ነገር ግን ከአልባሳቱና ከአመጋገቡ፣ ከአደባባይ ትዕይነቱና ከድምቀቱ ባሻጋር አክባሪው ምዕመን ተነፋፍቆ ሲገናኝና ማዕድ አብሮ ሲቆርስ የሚታየው አርቴፊሻል ያልሆነ ፍቅርና መከባበር፣ አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብስ መተሳሰብ፣ የተጣለው እንዲታረቅ ሁኔታው ሲያስገድድ፣ የተቸገር ሲረዳና ነፍሱና ስሜቱ ሲረሰርስ የሚስተዋለው ያ መልከ ብዙ መገለጫ ሌላ ሳይሆን በበዓላቱና በባህሉ ውስጥ ያለው እሴት ጎልቶ የመውጣቱ ምልክት ነው።

በአዳዲስ አልባሳት ከመዋብ ባሻገር፣ ለድግስ ፋታ ከማጣት በበለጠ ሕያው ሆኖ በማሕበረሰቡ ውስጥ የሚስተዋለው መቀባበል፣ መከባበርና መደናነቅ፣ መረዳዳትና መደጋገፍ፣ ለታላላቆች የሚሰጠው አክብሮትና ምክራቸውንና ምርቃታቸውን ለመቀበል የሚደረገው እሽቅድምድም እርሱ ነው "እሴት" የሚባለው። ስለዚህም ነው እሴትን በጣዝማ ማር የመሰልነው። አንድም ለጥፍጥና አንድም ለመድኃኒት ይሆናል ብለን። እሴት የባህልና የበዓላት አስኳል ረቂቅ የአብሮነት ሀብት እንጂ እንደ ሌላው በአጀብ ብዛት የሚገለጽ የግል ጉዳይ ብቻ አይደለም።

ወደ ማጠቃለያ ሃሳባችን እናዝግም። ምናልባትም በበዓላት ብዛትና በኅብረ ባህሎች ፀጋ ኢትዮጵያችን ከበርካታ ሀገራት ቀድማ የምትጠቀስ ሳትሆን እንደማትቀር ብንገምት ላንሳሳት እንችላለን። ሌላው ቀርቶ በየሃይማኖታችን ውስጥ ያሉትን የየቀኑን ድርብርብ መንፈሳዊ በዓላት እንቁጠር እንኳን ብንል ቁጥራቸው የትዬለሌ ሆኖ እንደምንቸገር ከላይ በሰጠናቸው ትንታኔዎቻችን ውስጥ ጠቃቅሰን አልፈናል።

አብዛኞቹ የሀገራችን ባህሎችና በዓላት ህልውና የሆኑት በሃይማኖቶች ዙሪያ እንደሆነ ይታወቃል። የአብዛኞቹ ሀገራዊ እሴቶቻችን የሚዘመሩትም ሃይማኖቶቹ ባጎናጸፉን ፀጋዎች አማካይነት ነው። የትኛውም ሃይማኖት ደግሞ በምድርም ይሁን በሰማይ ከሰላምና በአብሮነት ከመኖር ውጭ ሌላ መልእክት የለውም። የአብዛኞቹ ሃይማኖቶች ማዕከላዊ መልእክት "ለአንተ/ቺ እንዲደረግልህ/ሽ የምትፈልገውን/የምትፈልጊውን እንዲሁ ለሌላው አድርግ/ጊ" የሚል መሆኑን ወርቃማ ሕግጋት የሚባሉት የየሃይማኖቶቹ ትምህርቶች በግልጽ ያስረዳሉ።

እንደዚህ በሃይማኖቶችና በበዓላት እሴቶች ደምቃለች በሚባል ሀገር መገዳደል፣ አንዱ አንዱን ማፈናቀል፣ ወንድም በወንድሙ ላይ ሰይፍ እየሳለ ለመጠፋፋት የደም ሽማ መጣጣል ከየትና እንዴት ሥር ሰዶ ሊያጨካክነን ቻለ? ይሉኝታ በሌለው ዘረፋ መበልጸግን ያስተማረን የየትኛው ባህላችንና በዓላቶቻችን "ክፉ እሴት" ነው። በዓላትን ስናከብር ተነፋፍቀን፣ ስንገዳደል ተጨካክነን፤ ምን ይሉት ክፉ ብሔራዊ ልክፍት ነው? ወደ ቀልባችን ተመልሰን ባህሎቻችንንም ሆኑ በዓላቶቻችን ልንፈትሽ ግድ ሊለን ይገባል። ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም በጎ ፈቃድ።

## ተናጋሪው ዶሴ

# በትዳር አጋር የተነጠቀች ሕይወት



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሀገር የማንነታችን መገለጫና የህልውናችን መሰረት ናት። እናት ደግሞ የሀገር ተምሳሌት ናት። እናት መኖሪያችን ፣እናት ፍቅራችን፣እናት የህይወታችን ትርጉም ናት። ብቻ እናትና ሀገር የማይነጣጠሉ የህይወታችን ክፋዮች ናቸው።

ወ/ሮ ሀረገወይን አሰፋ የ36 ዓመት ጎልማሳ ስትሆን በትዳር ውስጥ ለ13 ዓመታት ያህል አሳልፋለች። በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁለት ልጆችንም አፍርታለች። የትዳር አጋሯ ኑሮውን በውጭ ሀገር ካደረገ ረዥም ጊዜያትን አሳልፏል። ከአንድ ዓመት በፊት ግን ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት ኑሮውን አዲስ አበባ አድርጓል ።ሆኖም በጥንዶቹ ቤት ዘወትር አለመግባባቶች ይፈጠራሉ። ሁልጊዜም ሽማግሌ ገብቶ ያስታርቃቸዋል ።ወ/ሮ ሀረገወይንም ትዳሬ ችግር ውስጥ ነው በማለት ለሚቀርቧት ሰዎችም ትናገር ነበር።

ህዳር 29/2015ዓ.ም ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ሆኗል። በወ/ሮ ሀረገወይንና በባለቤቷ መካከል ጭቅጭቅ ተፈጥሯል። በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ልዩ ቦታው አርሴማ አደባባይ ገባ ብሎ ካለው መኖሪያ ቤት ውስጥ ፍቺ መፈጸም አለብን በሚል በተፈጠረ አለመግባባትና ከሌላ ወንድ ጋር እጠረጥርሻለሁ፤ እምነት አጉድለሻል በሚል ከፍያለ ጭቅጭቅ ተፈጥሯል።

### የከረረው ጭቅጭቅና ያስከተለው መዘዝ

በሁለቱ ጥንዶች መካከል ያለው ጭቅጭቅ ገላጋይ ባለማግኘቱ ተባብሷል። ጭቅጭቁ ተባብሶ ወደ ድብድብና የኃይል እርምጃ ተሸጋግሯል።አባወራ እጀታው የእንጨት በሆነ የአጥንት መከትከቻ መጥረቢያ አንገቷ ላይ ደጋግሞ ይመታል። በዚህ ጊዜ ወ/ሮ ሀረገወይን ዱላውን መቋቋም ሲያቅታት ተዝለፍልፋ ትወድቃለች። በዚያውም ህይወቷ ያልፋል።

### የፖሊስ ማስረጃ

መረጃው የደረሰው ፖሊስ ወንጀሉ በተፈጠረበት ቦታ ይደርሳል። የሰውና የቴክኒክ ማስረጃም ይወስዳል። እጀታው የእንጨት በሆነ የአጥንት መከትከቻ መጥረቢያ አንገቷ ላይ ደጋግሞ በመምታት ጉዳት አድርሶ ህይወቷ እንዲያልፍ ያደረገ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ ባደረገው ምርመራ ማጣራት ችሏል።

በሟች ሀረገወይን አሰፋና በባለቤቷ መካከል የተፈጠረ አለመግባባት የትዳር አጋሩንና የልጆቹን እናት ህይወት እንዲያጠፊ አድርጎታል። ተጠርጣሪና ሟች በትዳር አብረው ሲኖሩ በተደጋጋሚ አለመግባባት ተከስቶ በሽማግሌ ሲታረቁ እንደቆዩ ለፍቺም ፍርድ ቤት ከደረሱ በኋላ በሽማግሌ ጥረት አብረው እንደቆዩ የፖሊስ መረጃ ያሳያል።

### የቤተሰብ ምስክርነት

የዘወትር ጭቅጭቅና ፀብ መነሻ የሆነው ከሌላ ወንድ ጋር እጠረጥርሻለሁ አላምንሽም በሚል ምክንያት በሚጣሉበት ወቅት በመካከላቸው በተደጋጋሚ ጊዜ ሽማግሌ ሆነው ሲያስታርቁ የቆዩት አገላጋይ አክሊሉ ላንቀ ለአዲስ አበባ ፖሊስ ገልጻዋል። እሳቸው እንደተናገሩት፤ በተደጋጋሚ አለመግባባቶች እንዳለ ሟች በተደጋጋሚ እየመጣች እንደምትነግራቸውና ትዳሬ ችግር ውስጥ ነው ፀልዩልኝ እያለች እንደምትማጸናቸው አስረድተዋል።

ሽማግሌውም በፀሎት፣ በምክር ትዳር እንዳይፈርስ ብዙ ጥረት እንዳደረጉ ባለቤቷን በማግኘት ‹‹በዓይንህ ያላየኸውን ነገር አትመን ተው›› በማለት ‹‹ከአንተ የተወለዱ ልጆችን ማሳደግ፤ ከሚስትህ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ፤ሚስትህን መንከባከብ የአንተ ኃላፊነት ነው›› በሚል ብዙ እንደነገሩት ተናግረዋል።

ሟች ሀረገወይን አሰፋ ባለቤቷ ሀገር ውስጥ ባለመኖሩ ለረዥም ዓመታት ልጆቿን ለብቻዋ አሳድጋለች። ባለቤቷ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ ልጆቻቸውን በጋራ ለማሳደግና አብረው ወደ ውጭ ሀገር ለመሄድ አስበው ነበር ። ነገር ግን ሳይሆን ቀርቷል።

የሟች እህት ወሰን አሰፋ እንደምትናገረው፤ ባለቤቷ ከውጭ ሀገር ከመጣ ከአንድ ዓመት በላይ እንደሆነውና የመጣውም ከሟች ጋር የመኖሪያ ቤታቸውን ሠርተው አንድ ላይ ለመኖር እንደነበርና ሟች የውጭ ፕሮሰስ ጨርሳ እንደነበር። ሆኖም ቤተሰብ ለሽኝት እንጂ ይህ ይመጣል ብሎ እንዳላሰበ ትናገራለች።

የሟች ሀረገወይን አሰፋ ቤተሰቦች በሰላም ያሳደርከን፤ በሰላም አውለን ብለው ወደ ስራቸው ሄደዋል። ስልክ ተደውሎ የሰሙትን ነገር ግን ማመን አቅቷቸዋል። የሟች እህት በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ ስትናገር ‹‹በድንገት ቶሎ ድረሺ ›› ተብሎ እንደተደወለላትና በቦታው ስትደርስ ፖሊስና ሕዝብ ተሰብስቦ እንደደረሰች ትናገራለች። ከመኪና ስትወርድ ክፉኛ መደናገጧን ‹‹እህቴ በህይወት ካለች ህይወቷን እናትርፍ፤ ከሞተችም ንገሩኝ›› ስትል እንደጠየቀችና ሆኖም አስደንጋጭ በሆነ መልኩ በሰው እጅ እንደተገደለች እንደተነገራት ትገልጻለች።

የሟች ወንድም ቶማስ አሰፋ እንደሚናገረው፤ ችግሩ እንደተፈጠረ እህቱ ደውላ እንደነገረችው እና በዛው ሰዓት ወደ ሟች መኖሪያ ቤት ያመራል። በቦታው ሲደርስ ፖሊስ በአካባቢው በብዛት እንደነበር እርሱም ወደ ውስጥ መግባት እንዳልቻለ ይናገራል። በኋላም ፖሊሶች ፈቅደውለት ወደ ውስጥ እንደገባ ያየው ነገር ልብ ሰባሪ እንደነበር ገልጿል።

ሌላኛው የሟች ቤተሰብ የሆነው ሰለሞን ታደሰ ስለጉዳዩ ሲናገር፤ በግል ጉዳይ ለረዥም ሰዓት በስልክ እያወራ እንደቆየ፤ በዚህም ምክንያት ከቤተሰብ ስልክ ደውለው እርሱን ማግኘት ስላልቻሉ ሰው ተልኮ ስለ ጉዳዩ እንደሰማ ይገልጻል። ቤት ሁሉም እራሳቸውን እንደሳቱ እንደተነገረው፤ ምንድነው ብሎ ወደ ቤት ሲሄድ የተፈጠረውን ነገር እንደተመለከተ ይናገራል። ‹‹ተነጋግሮና ተግባብቶ መኖር በሚቻልበት በዚህ ዘመን በአጉል ጥርጣሬ ተነስቶ በአሰቃቂ ሁኔታ የትዳር አጋሩን ህይወት ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ ማጥፋት የከፋ ወንጀል መሆኑን ይናገራል።

መርማሪ ሳጅን ሀብታሙ ገብሬ እንደሚናገሩት፤ ተጠርጣሪው ወንጀሉን ከፈፀመ በኋላ ከዚህ በፊት ሽማግሌ ሆኖ ያስታርቃቸው የነበረ ጓደኛው ጋር ደውሎ ጉዳዩን እንደነገረ ጓደኛው በስልክ መረጃውን ለፖሊስ እንዳደረሰ ተናግረዋል። የተጠርጣሪው ጓደኛ በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታ ሲናገር ተጠርጣሪው ለእርሱ ደውሎ የግድያ ወንጀል እንደፈፀመ እንደነገረው ተናግሯል።

ይህንን የሰማው ጓደኛው ወደ ተጠርጣሪው ሰው ቤት ያመራል። በቦታው እንደደረሱም ተጠርጣሪ ወንጀለኛም በሩን ይከፍትላቸዋል። ሁኔታውንም ለፖሊስ ደውሎ እንዳሳወቀ ይነግራቸዋል። መኖሪያ ቤቱ ወደ ውስጥ ገባ ያለ በመሆኑ ፖሊሶች ለማግኘት የተወሰነ ስለተቸገሩ እርሱ እየመራቸው ወደ ሟች መኖሪያ ቤት እንደደረሱ ያስረዳል።

አንዳንድ ጊዜ በመፍራት ፣ ቻይ በመሆን ፍቅራችንንና ትዳራችንን ያቆየን የሚመስለን ሰዎች አንጠፋም። ይህም ሟች ከባለቤቷ ጋር ያለው አለመግባባት በቤተሰብ እየተፈታ ወደ ቤቷ ትመለስ ነበር። ልጆቿን ይዛ ሁለት ቀን ቤተሰብ ጋር ቆይታ በመጣች ማግስት ነው ይህ የወንጀል ድርጊት የተፈፀመው።

የሟች እህት እንደምትናገረው እንደማንኛውም ሰው በመካከላቸው አልፎ አልፎ ፀብ እንዳለ ቤተሰብ ገብቶ እንደሚያስታርቅ ትናገራለች። ህይወቷ ከማለፉ ጥቅት ቀናት በፊት ሟች ልጆቿን ይዛ ወደ ቤተሰብ እንደመጣችና ለተወሰኑ ቀናት እዛው ትቆያለች። ሟች በቆይታዋም ደስተኛ ነበረች። ተጨዋውተው ተሳስቀው ወደ ቤቷ እንደተመለሰችም ገልጻለች።

የሟች ወንድም በበኩሉ እንደሚናገረው፤ ባለቤቷ ውጭ ሀገር እንደመሆኑ መጠን ሟችና ልጆቿ ብዙ ጊዜ ቤተሰብ ጋር እንደሚያሳልፉ ተናግሮ፤ በሟችና በተጠርጣሪው መካከል አልፎ አልፎ ግጭት እንደነበር እና ሆኖም እስከ ሞት የሚያደርስ ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ እንደማይታሰብ ተናግሯል።

የወይዘሮዋ ሞት ከራሷ አልፎ የወለደቻቸው ልጆቻቸው ላይም ትልቅ ጠበሳ አሳድሯል። የሟች ወንድም ሲናገር ልጆቹ ትመጣለች ብለው በር በር ሲያዩ ያለው ስሜት የሚያም እንደሆነ ይገልፃል። እንደ ቤተሰብ ከባድ ጊዜ እያሳለፉ እንደሆነ ተናግሮ ከዚህ በኋላ ልጆቹን ስለሁኔታው ማስረዳት ሌላ ፈተና እንደሆነባቸው ገልጿል።

የሟች እህት ስለሁኔታው በእንባ ታጅባ ስትናገር፤ ተለያይቶ እህትና ወንድም ሆኖ መኖር እየተቻለ እርሱ ውጭ ሀገር እየኖረ የአብራኩ ክፋይ ልጆቹን በሥነ ሥርዓት ለብቻዋ እናትም አባትም ሆና ያሳደገችን ሴት እንዲህ በጭካኔ መግደል አዕምሯቸው ያልተቀበለው ነገር እንደሆነ ገልፃለች።

ሌላኛው የሟች ቤተሰብ ሲናገር፤ በዚህ በረቀቀ ዘመን ካልተግባቡ መለያየት እያለ ለወንጀልና ሰው ለመግደል መቸኮል በእጅጉ ከባድ እንደሆነ ያስረዳል።

አለመግባባት ሲከሰት በኃይልና በጉልበት ለመጠቀም ከማሰብ ይልቅ በመነጋገር መፍታት ብልህነት ነው። መርማሪ ሳጅን ሀብታሙ ገብሬ እንደሚናገሩት፤ በባልና በሚስት መካከል የማያግባቡ ብዙ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ። እንዲህ አይነት ነገር ሲከሰት በንግግር የሚፈታ ከሆነ በንግግር መፍታት ይገባል፤ ይህ የማይቻል ከሆነ በህጋዊ መንገድ መለያየት ሲቻል ወደ መጠፋፋት መሄድ አግባብ እንዳልሆነ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ሳጅን ሀብታሙ ሲናገሩ፤ እነዚህ ግለሰቦች በመካከላቸው ሁለት ልጆችን አፍርተዋል። ልጆች ደግሞ ከወላጆቻቸው ጋር ማደግ አለባቸው። አሁን እነዚህ ልጆች ሁለቱንም ወላጆች ነው ያጡት። እናትን በሞት አባትን ደግሞ በእስር። ይሄ ሁሉ መሆን ያልነበረበት እንደሆነ ተናግረዋል።

የሟችና የተጠርጣሪ የጋራ ወዳጅ የሆነው አገልጋይ አክሊሉ ላንቃ እንደሚናገረው፤ በመካከላቸው ብዙ ጊዜ አለመተማመን አለ፤ጥርጣሬ አለ፤ እርሱ እርሷን፤ እርሷ ደግሞ እርሱን፤ ያለማመን ችግር ነበር።ያለመተማመን ደግሞ መጨረሻው አያምርም። አንድ ሰው ከአንድ ሰው ጋር በአንድ ቤት እስከ ኖረ ድረስ መተማመን መኖር እንዳለበትና ይህ መሆን ካልቻለ ግን በሰላም መለያየት አማራጭ መሆኑን ያስረዳሉ።

የሟች እህት በበኩሏ ‹‹በዚህ ዘመን ማንኛውንም ነገር በመነጋገር መፍታት ይቻላል፤ ካልተስማሙ ደግሞ በሰላም መለያየት አማራጭ ነው። ህይወት ይቀጥላል ፤ተለያይቶ ልጆችን ማሳደግ ይቻላል።ነገር ግን ይህ ሁሉ አማራጭ እያለ የሰውን ነፍስ ማጥፋት ለምን›› ስትል ትጠይቃለች።

መርማሪ ሳጅን ሀብታሙ እንደሚናገሩት፤ አለመግባባት ሲከሰት ልጆችን ወደ ሌላ ቦታ በመውሰድ ሁለቱ ሰዎች በንግግር ችግሮችን ለመፍታት መሞከር አለባቸው። ቁጭ ብለው የእኔ ችግር ምንድነው፤ የአንተ ወይም የአንቺ ችግር ምንድነው የሚለውን መነጋገር መቻል አለባቸው። ዘመድ አዝማድ አሰባስበውም ችግሮችን ለመፍታት ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። በዚህ ካልሆነ በሰላም መለያየት መቻል አለባቸው እንጂ ወደዚህ አይነት መጥፎ ውሳኔ ለመድረስ መጣደፍ የለባቸውም ብለዋል።

የሁለቱም የጋራ ጓደኛ የሆነው አገልጋይ አክሊሉ በበኩሉ፤ እግር ከእግር ጋር እንኳ ይጋጫል፣ ሲኒ ከሲኒ ጋር ይጋጫል፣ አለመግባባት ሲፈጠር ማንኛውም ሰው እራሱን መግዛት እንዳለበት ተናግሯል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## በቴሌቪዥን መስኮቶች

መልካምሥራ አፈወርቅ

አዕምሮ በሥራ ሲጨናነቅ አልያም በሃሳብ ሲወጠር ለአፍታ ዘና የሚያደርገውን ቢያገኝ አይጠላም። እንዲህ በሆነ ጊዜ የምርጫው ጉዳይ እንደየ ሰው ፍላጎትና አቅም ሊለያይ ይችላል። አንዳንዱ ከከተማ ወጣ ብሎ ከባህር ዳርቻው አሸዋ ጋደም ማለት ፍላጎቱ ነው። ለእሱ መዝናናት ማለት ንጹህ አየር እየሳቡ ተፈጥሮን ማድነቅ ሊሆን ይችላል።

ሌላው ደግሞ አውሮፓ አሜሪካ ወጣ ብሎ፤ ከሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎች ፣ ከታዋቂ የገበያ ማዕከላት መገኘቱን እንደ መዝናናት ይቆጥረዋል። ራስን ከስፖርት ማዘውተሪያዎች አስተዋውቆ ጤና እየጠበቁ መንፈስን ማርካትም አንዱ የመዝናናት መገለጫ ነው ሊባል ይችላል።

መዝናናት እንግዲህ ሰፊና መልከ ብዙ ነው። እንደየሰው አቅምና ፍላጎት ቢለያይም ከሰው ልጆች የዕለት እንቅስቃሴዎች ጋር በእኩል ይራመዳል። ወደ እኛ ማህበረሰብ መለስ ስንል ግን የመዝናናት ሁኔታ ሊዥጎረጎር ይችላል። ይህ እንግዲህ እንደየሰው አቅምና ፍላጎት ብለን ከለየነው ነው።

አብዛኛው ግን ከቤቱ ተቀምጦ የሚዝናናበት ሬዲዮና ቴሌቪዥን ሊኖረው እንደሚችል ያስማማናል። አይነት ደረጃው ይለያይ እንጂ አሁን ላይ በየቤቱ ቴሌቪዥን የሌለው ሰው ይኖራል ለማለት አያስደፍርም።

የዛሬን አያድርገውና ቴሌቪዥን ብርቅ ሆኖ በጥቂት ሰዎች ቤት በነበረ ጊዜ ራስን ለማዝናናት ወደጎረቤት ጎራ የሚለው ተመልካች ጥቂት አልነበረም። እንዲህ ሲሆን ግን ሁሉም እንዳሻው የፈለገውን መርጦ ያያል ማለት አልነበረም። ምንጊዜም ይህ አይነቱ ፍላጎት የሚወሰነው በቴሌቪዥን ባለቤቶች ምርጫ ብቻ ይሆናል። በተለይ በዘመኑ የነበሩ ህጻናት ቴሌቪዥን ለማየት ነጻነታቸው በገደብ እንደነበር የሚያውቅ ያውቀዋል።

የዛኔ በእነሱ ዕድሜ ተመራጭ የነበረው ፕሮግራም በልጆች ክፍለ ጊዜ የሚተላለፈው የ«አባባ ተስፋዬ የተረት ወግ ነበር። ከዚህ በዘለለ ከወላጆቻቸው ጋ ብለው የሚያዩት የ «ሕብረትርዒት» የሙዚቃ ምርጫ ሊሆን ይችላል። እነዚህን ተወዳጅ ፕሮግራሞች ታዲያ ከሰው ቤት ገብቶ ደልቀቅ ብሎ ማየት ክልክል ነበር።

የዛን ዘመን ህጻናት ቴሌቪዥን ከማየታቸው አስድቀሞ በአቅማቸው ለቤቱ ባለቤቶች የጉልበት ግብር ሊከፍሉ ግድ ነው። በትንሹ በእነሱ አቅም የሚጸዳ ቤት፣ አልያም የሚታጠብ ዕቃ ካለ እንደሚሆን ማድረግ ግዴታቸው ይሆናል ። ይህ ሁሉ ዋጋ የሚከፈለው ታዲያ ራስን ለማዝናናትና ደስታን ለመፍጠር ሲባል ነው ።

በወቅቱ ዘመኑ የሚፈቅደው የመዝናኛ አማራጭ ከዚህ የዘለለ አልነበረም። ሁሉም አካባቢውን ተጠቅሞ አእምሮውን ዘና ፈታ ለማድረግ የቴሌቪዥን መስኮት ላይ ማተኮር ነበረበት ። ይህ ዘመን ጥቂት ፈቀቅ ብሎ አንድ ርምጃ እንዳለፈ ፣ የቪዲዮ ፊልሞች ለመዝናኛነት ይመረጡ ያዙ።

በዘመኑ ሁሉም ዘንድ ይህ አማራጭ ነበር ባይባልም ቪዲዮ ይሉት ማጫወቻ በየቤቱ መዘውተሩ በርካታ ተመልካቾችን አላሳጣም። በጊዜው በየቦታው በገንዘብ የሚከራዩ ምርጥ የውጭ ሀገራት ፊልሞች ተወዳጅነት ነበራቸው ።

ወቅትና ጊዜ ሲለወጥ ደግሞ ቀን ቆጥሮ አሮጌው በአዲስ ተተካ። የቴክኖሎጂው ጫፍ ከብዙዎች ሲደርስም ትናንት ያልነበሩ መገልገያዎች ከብዙዎች ዘንድ ተገኙ ። የሲዲ ፊልሞች ፣ሙዚቃዎችና አልበሞች ለብዙኃኑ ተደራሽ መሆን ያዙ።

ውሎ አድሮ ደግሞ ዓለምን በአንድ የሚያገናኘው የማህበራዊ ሚዲያ መረብ በሁሉም ሰው መዳፍ አረፈ። የቴክኖሎጂው መፍጠን ጥቅም ጉዳቱ፣ ትርፍ ኪሳራው ከትውልድ ተጠጋ። ይህን ተከትሎ መዝናናት ፣ መደሰት ይሏቸው እውነታዎች በቀላል ዘዴና መንገድ ተተግብረው ለብዙዎች ዕውን ሆኑ ።

ወዳጆቼ መነሻዬን አልዘነጋሁም። አስቀድሜ እንዳልኳችሁ ለማውሳት የፈለግሁት የመዝናኛውን ነገር ነው ። «ነገርን ነገር ያነሳዋል» ሆኖብኝ እኛንና የቴሌቪዥንን ነገር መለስ ብዬ አስታወስኩ። ይህ አጋጣሚ የዘመንኛውን የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችና የአስተዋዋቂዎቹን ጉዳይ እንድታዘበው አስገደደኝ።

ለጊዜ ምስጋና ይግባወና ዛሬ ላይ ሁሉም ቤት በሚያስብል ሁኔታ ቴሌቪዥን ይሉት ነገር አይጠፋም። የምልከታው ጉዳይ እንደየፍላጎት ቢሆንም በተለያዩ ጣቢያዎች የመዝናኛ ዝግጅቶች ይተላለፋሉ። «መዝናኛ» የሚለው ሃሳብ በብዙዎች ዘንድ የሚኖረውን ትርጉም መለየት ባይቻልም ተመልካቹ ግን ይህን ቃል በሚሸከም አግባብ ለዓይኑ የሚጠብቀው ነገር መመኘቱ ዕሙን ነው ።

ብዙዎቻችን እንደምንታዘበው ግን በየቴሌቪዥን መስኮቶች የሚተላለፉ ፕሮግራሞች የልብ አድራሽ የሚባሉ አልሆኑም። በአንድ ትዕዛዝ አንድ አይነት ጉዳይ አስተላልፉ የተባሉ ይመስል አብዛኞቹ በተመሳሳይ ይዘት መገለጥ ልምዳቸው ሆኗል ። በርካቶች በእረፍት ሰአታቸው ቤት በተገኙ ጊዜ ከቴሌቪዥን መስኮት ማተኮራቸው አይቀሬ ነው።

በእነዚህ ቀናት ከሚተላለፉ ፕሮግራሞች ሰአት ለይተው ፣ ጣቢያ መርጠው እንዳያተኩሩ ግን ምርጫው ጠባብ ይሆናል ። ብዙዎች እንደሚሉት አንዱ ጣቢያ ሲታይ ወንድና ሴት አስተዋዋቂዎች ከስቱዲዮ ተቀምጠው ያለመታከት የሚያወሩት የተለመደ ወሬ ያሰለቻል።

እሱን ለውጠው ወደሌላው ሲሻገሩም ጉዳዩ ተመሳሳይ ነው። የሰዎቹ መቀየር እንጂ የሚነሳው ርዕሰ ጉዳይ እምብዛም ለውጥ የለውም። አሁንም ጥቂት አየት አድርገው ሪሞቱን ወደሌላ ያዞሩታል። በዚህም ጣቢያ በሌሎቹ አይተው ካለፉት አይነት ይዘት ጋር ይፋጠጣሉ። ይህ የሚሆነው በእረፍት ቀናት በተመሳሳይ ሰአትና ጊዜ በሚተላለፉ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ላይ ነው።

በጣም አስገራሚው ጉዳይ በቴሌቪዥን የመዝናኛ ፕሮግራሞች የሚታዩ አቅራቢዎች ተመሳስሎ ነው። አሁን ላይ ሁሉም በሚባል መልኩ በተጋነነ የሜካፕ ገጽታ ብቅ የሚሉ የስቱዲዮ ጋዜጠኞች በእጅጉ በርክተዋል። ሁሉም የአንድ እናት ልጆች እስኪመስሉ የሚጠቀሙት ሜካፕም ኢትዮጵያዊ ማንነትን እያስረሳ ነው። ይህ እውነታ ደግሞ በእንግድነት የሚቀርቡት ላይ ጭምር ከማን አንሼነትን እያሳየ መሆኑን ልብ ይሏል። እርግጥ ነው ራስን አሳምሮና በተገቢው ተውቦ መታየት የግድ ይላል። አሁን ላይ ግን ይህ አይቱ ሀገርኛ ምግባር ሙሉ ለሙሉ እየጠፋ ነው ለማለት ያስደፍራል ።

በዘመኑ ደጋግመን እንደምናስተውለው በቴሌቪዥን የመዝናኛ ጣቢያዎች የሚቀርቡ በርካታ እንግዶች የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች እየሆኑ ነው። ኩሽና መግባቱ ግድ የሆነ ይመስል በአንዱ ጣቢያ የታየው ጥቂት ለወጥ ብሎ በሌላው መደገሙ ተለምዷል። ይህ ደግሞ በትክክል የተመልካቾችን ዓይን ማረፊያ የሚያሳጣ ነው።

አንዳንዴ ደግሞ እንግዶች ሆነው የሚቀርቡ ሰዎች የመናገር ፍላጎት በግልጽ ሲገደብ ይስተዋላል። ምናአልባትም የጠያቂዎቹ ፍላጎት ብቻ በሚመስል አቅጣጫ ቃላቸው ሲገራ ማየት ያስተዛዝባል። ከዚሁ ተያይዞ በቡድን ጨዋታ ለመዝናኛ ተብለው የሚቀርቡ አንዳንድ ጥያቄዎች የሚያሸማቅቁ ናቸው። በተለይ የጥንዶችን ግንኙነት በሚመለከት የሚጠየቁ ከሆነ ከማስፈገግ ባለፈ አስደንጋጭና ያልታረሙ መሆናቸውን ማስተዋል ይቻላል።

ማዝናናት ሲባል ማሳቅ ብቻ ሊሆን አይገባም። በዋዘኛ ንግግሮች መሀል የሚያስተምሩ፣ ቁምነገር የሚያስጨብጡ ይዘቶች ቢቀርቡ ነውርነት የለውም ። የእኛዎቹ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ግን ማዝናናትን በሳቅና ፈንጠዝያ ብቻ ከበው አሰልቺ የሚባል ይዘቶችን «እንካችሁ» ይላሉ።

አንዳንዶቹን በጥልቅ ካስተዋልናቸው ፕሮግራሞቻቸው በቀጥታ የተቀዱት ከውጭው ዓለም የመዝናኛ ፕሮግራም ነው። ይህ ሲደረግ ግን በሁለቱ መሀል የሚኖረውን የባህል፣ የኑሮና የአስተሳሰብ ግጭቶችን ልብ ያሏቸው አይመስልም ። ይዘቶቹ እንደወረዱ መተግበራቸው ቀለማቱ በአንድ ሳይዋሀዱ የባዕድነት ስሜት እንዲንጸባረቅ አስገድዷል። መዝናናት አሰልቺ ሆኖም ሪሞት ያስወረውራል።

# ዓለም አቀፍ

## በእስር ላይ የምትገኘው ኢራናዊት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች የዘንድሮውን የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸነፈች

በጋዜጣው ሪፖርተር



ናርጅስ ሞሃማዲ

በእስር ላይ የምትገኘው ኢራናዊቷ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ናርጅስ ሞሃማዲ የዘንድሮው የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ ሆናለች።

ናርጅስ የሽልማቱ አሸናፊ የሆነችው በኢራን በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ጭቆና በመታገል እንዲሁም ሁሉም ዜጎች ሰብዓዊ መብቶቻቸው ተከብሮ እና ነጻነት የሚያገኙበትን ዓለም ለመፍጠር ባደረገችው ትግል እንደሆነም ኮሚቴው አስታውቋል።

ናርጅስ በምታደርገው ትግልም በርካታ ጊዜ በቁጥጥር ስር ውላለች። በኢራን መንግሥት 13 ጊዜ በቁጥጥር ስር ውላ አምስት ጊዜ ጥፋተኛ የተባለች ሲሆን፤ በአጠቃላይም የ31 ዓመታት እስራት እንዲሁም 154 የጅራፍ ግርፋት ተፈርዶባታል።

ናርጅስ ያለፉትን አብዛኛውን ሁለት አስርት አመታት በእስር ነው ያሳለፈችው። በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ብሄራዊ ደህንነት ተቃራኒ በሆነ ተግባር እና በኢራን መንግሥት ላይ ፕሮፓጋንዳ በማሰራጨት ክስ 12 ዓመት ተፈርዶባት ኢቪን ማረሚያ በእስር ትገኛለች።

የኖቤል ኮሚቴውም ሽልማቱን ባበረከተበት ወቅት “የናርጅስ የጀግንነት ትግል ከፍተኛ ዋጋ አስከፍሏታል” ብሏል።

“እኔ አሁን እየተናገርኩ ባለሁበት ወቅት እሷ በእስር እየማቀቀች ትገኛለች” ሲሉም በኦስሎ የሚገኘው የኖቤል የሰላም ሽልማት ኮሚቴ ኃላፊ የሆኑት ቤሪት ሪስ አንደርሰን ተናግረዋል።

ናርጅስ ቢቢሲ ዓለምን የተሻለች ለማድረግ የሚጥሩ 100 ሴቶችን በሚመርጥበት ፕሮግራሙም በዘንድሮው ዝርዝር ውስጥ ተካታለች።

ባለፈው ዓመት የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ የነበሩት ሜሞሪያል የተባለ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ቡድን፣ ዩክሬናዊ የሰብዓዊ ተሟጋች ማዕከል ‘ሴንተር ፎር ሊበርቲስ ’ እንዲሁም በእስር ላይ የሚገኘው የመብት ተሟጋች አሌስ ቢያሊያትስኪ ነበሩ።

ሩስያ በዩክሬን ላይ ወረራ ፈጽማ ጦርነቱ በተፋፋመበት ወቅት ሰላም እንዲሰፍን ላደረጉት ትግልም እውቅና ተሰጥቷቸዋል።

የዘንድሮው የኖቤል የሰላም ሽልማት አሸናፊ ናርጅስ 11 ሚሊዮን የስዊድን ክሮነር (አንድ ሚሊዮን የአሜሪካ) ዶላር ታገኛለች። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲወዳደር 10 በመቶ ብልጫ አለው ተብሏል። በተጨማሪም ተሸላሚዎች ዲፕሎማ እና የኖቤል ኮሚቴው 18 ካራት ወርቅ ሜዳሊያም ይሸለማሉ።

የኖቤል የሰላም ሽልማት ከተቋቋመበት ከአውሮፓውያኑ 1901 ጀምሮ 110 ግለሰቦች እና 30 ድርጅቶች አሸናፊ ሆነዋል።

ከዚህ ቀደም ፓኪስታናዊቷ የትምህርት ተሟጋች ማላላ ዩሳፋዚ እንዲሁም የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሽልማቱ አሸናፊ ሆነዋል።

## በሱዳን የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ እየተሰማ ያለው አነጋጋሪው “የአልበሽር ድምጽ”

በጋዜጣው ሪፖርተር



ኦማር ሐሰን አል በሽር

ሱዳንን ከሦስት አስርት ዓመታት በላይ በፈላጭ ቆራጭነት የገዙት ኦማር ሐሰን አል በሽር በቅርቡ “ድምጻቸው” ተሰምቷል።

የቀድሞው የሱዳን መሪ አልበሽርን አስመስሎ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን (አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ) በመጠቀም የተላለፈው መልዕክት ቲክቶክ ላይ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ዕይታ ነበረው።

ይህ በእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ለምትገኘው ሱዳን ሌላ የኢንተርኔት ውዥንብር ምክንያት ሆኗል።

ማንነቱ ባልታወቀ የቲክቶክ ገጽ ከነሐሴ መገባደጃ ወዲህ “በድብቅ ተቀርጸው የወጡ” የቀድሞው ፕሬዚዳንት ናቸው ያላቸውን ድምጾች እየለጠፈ ነው። ገጹ የአልበሽርን በርካታ ድምጾችን ቢለቅም ድምጾቹ ግን ትክክለኛ አይደሉም።

የጦር ወንጀሎችን በመፈጸም የተከሰሱት እና በ2019 በወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣን የተገረሰሱት አልበሽር ለአንድ ዓመት ያህል በአደባባይ አልታዩም።

በጠና እንደታመሙም ይታመናል። አልበሽር የቀረቡባቸውን የጦር ወንጀሎች አይቀበሏቸውም።

ያሉበት ቦታ እንቆቅልሽ በሆነበት በዚህ ወቅት ሀገሪቱ በጦር ሠራዊቱ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መካከል በሚደረገው ጦርነት እየተናጠች ትገኛለች።

አዳዲስ ዘዴዎችን በመጠቀም የሐሰተኛ መረጃዎችን በፍጥነት እና ርካሽ በሆነ መንገድ በማኅበራዊ ትስስር መድረኮች እንዴት እንደሚያሰራጩ ስለሚያሳዩ እንደዚህ አይነት ዘመቻዎች ጠቃሚ ናቸው ይላሉ ባለሙያዎች።

በካሊፎርኒያ በርክሌይ ዩኒቨርሲቲ የዲጂታል ፎረንሲክ ጥናት ያደረጉት ሃኒ ፋሪድ “የተራቀቀ የድምጽ እና የተንቀሳቃሽ ምስሎች ማጭበርበር ቴክኖሎጂ ለሁሉም ተደራሽ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያስጨንቀኛል” ይላሉ።

“የተራቀቁ ጥቂቶች ለብዙ አሥርት ዓመታት እውነታውን በማጣመም ይጠበቡበት ነበር። አሁን ግን ትንሽ የቴክኒክ ዕውቀት ያለው ማንኛውም ሰው በፍጥነት እና በቀላሉ ሐሰተኛ ይዘት መፍጠር ይችላል” ብለዋል።

ቅጂዎቹ “ዘ ቮይስ ኦፍ ሱዳን” በሚባል ገጽ ላይ ተለጥፈዋል። ልጥፎቹ በመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ወቅት ከተሰጡ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የተወሰዱ የቆዩ ቅጂዎች፣ የዜና ዘገባዎች እና አልበሽር ተናግረዋቸዋል የተባሉ በርካታ “በድብቅ ተቀርጸው የተለቀቁ ቅጂዎችን” ያሰባጠረ ይመስላል።

አብዛኞቹ የድምጽ ልጥፎች ከስብሰባ ወይም ከስልክ ውይይት የተወሰዱ ይመስላሉ። ድምጾቹም ጥራት የሌላቸው እና ከመጥፎ የስልክ መስመር የተቀረጹ ይመስላሉ።

ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የቢቢሲ ሞኒተሪንግ የሱዳን ባለሙያዎች ተጠይቀው ነበር። በዚህም ኢብራሂም ሃይታር የቅርብ ጊዜ ላይሆኑ እንደሚችሉ ተናግሯል።

የመጀመሪያዎቹ የአልበሽር የድምጽ ቅጂዎች በነሐሴ 2023 ነበር የተለጠፉት። በዚህም የቀድሞው ፕሬዚዳንት የሱዳን ጦር አዛዥ ጄኔራል አብደል ፋታህ አል ቡርሃንን ይተቻሉ።

የአልበሽር ድምጽ አል ኢንሲራፊ ተብሎ የሚጠራው ታዋቂ ሱዳናዊ የፖለቲካ ተንታኝ ከሁለት ቀናት በፊት ካስተላለፈው የፌስቡክ ቀጥታ ስርጭት ጋር ተመሳሳይ ነው። የግለሰቡ መኖሪያ አሜሪካ ነው ይባል እንጂ ፊቱን አሳይቶ አያውቅም።

ማህበራዊ

## መጋቢ አዕምሮ

# ዘመን እና እውነት

**ግርማ መንግሥቴ**

ድሮ ድሮ ውሸት በኢትዮጵያ ውጉዝ ከመ አሪዎስ ነበር አሉ የሚባለው። በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ ዋሽቶ መኖር እንኳን ሊደረግ የሚታሰብ አልነበረም። ጥንት አንድ ሰው ዋሸ ማለት ከሰውም ከፈጣሪውም ተጣላ ማለት ሲሆን፣ ተመልሶ ለመታመን የሕይወት ዘመኑ እንኳን አይበቃውም ሲባል ነበር የሚሰማው። ተጽፎ የሚገኘውም ይሄው እንጂ ሌላ አይደለም።

በድሮዋ ኢትዮጵያ ለእውነት የሚሰጠው ስፍራ ከሁሉም በላይ የላቀ ነው። ስለ እውነት ሲባል ይሞታል እንጂ እውነት ለውሸት ቀብድ መያዣ አትደረግም። የፍትህ ሥርዓቱ መሰረቱ እውነት ነው፤ የአስተዳደር ሥርዓቱ ሞተሩ እውነትና እውነት እንጂ ሌላ ሆኖ አያውቅም። በመሆኑም፤ በአደባባይ የፍትህ ሥርዓት አሰጣጥ (የ"በላ ልበልሃ" ፍርድ ሂደት) የሚጀመረው፣

በላ ልበልሃ

የአፄ ሥርዓቱን፣

የመሰረቱን፤

አልናገርም ሀሰቱን፣

ሁሌ እውነት እውነቱን፤ ("እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደር" ይሏል ይህ ነው)

በሚለው ነበር። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ (በድፍን ዓለም ጭምር) ይሄ የ"ፋራ"ና ያለመሰልጠን ነው።

የዛሬን አያድርገውና፣ በጥንታዊቷ ኢትዮጵያ (እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ) በኢትዮጵያዊያን ልብና ህሊና ውስጥ ፈሪሀ እግዚአብሔር ጠፍቶ አያውቅም ነበር። በውሸት መማል፤ በሀሰት መመስከር፤ አድሏዊነት፣ ሙሰኝነት ... በኢትዮጵዊያን ዘንድ ጥዩፍ ብቻ ሳይሆኑ ሀጢያትም ነበሩ። ("ነበሩ"ስንል በፀፀት ነው።)

በድሮው የሀገራችን ዘመናት ሀሰት ከሰው በታች ያደርጋል። ሀሰተኛ መሆን ቃል አባይነት ነውና "ልጅህን ለልጄ" የሚለው ሰው እንኳ የለም። እንደ አንዳንድ የጽሑፍ መረጃዎች ከሆነ፣ "ዋሾ" መሆን ያስንቃል፤ "ውሸታም" ከመባል መሞት ይሻላል። በኢትዮጵያ ዘመንና እውነት ይህንን ይመስሉ ነበር።

ያ ዘመን ለእውነት ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጥ ትውልድ የነበረበት ዘመን ሲሆን፣ በአሻራነትም "አንገት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" የሚለው ለትውልድ ተሸጋግሮ መገኘቱ ነውና የአሁኑ ዘመን ቢያሳፍር የሚፈረድበት አይደለም።

"እውነት ለዘለዓለም አያረጅም፣ አይደክምም፣ አይቀያይርም፣ አይሸነፍም፣ ህያው ነው፣ እርሱም እየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱን እንኑረው፣ እንማረው፣ እንመነው፣ እናስተምረው፣ እናከብረው፣ እናስበው፣ እንተንብየው፣ እናንብበው፣ መድረካችን ይፈወስ፣ ልብና ህሊናችን ይመለስ፣ አንደበታችን ይቀደስ። አሜን" ይላል አንድ ከወደ ማህበራዊ ድረ-ገፅ አካባቢ አግኝቼ ማስታወሻዬ ላይ ያሰፈርኩት ጽሑፍ። እንዳለ እንቀበለውና እንለፈው።

በታላቁ መጽሐፍ የተገለፀው "እውነት፣ እውነት፣ እላችኋለሁ ..." የብዙኃን የእውነት እና እምነት መሰረት ነው። በትውልዶች ያልተመረዘና ያልተከለሰ የፈጣሪ መርህ ነው። በሌሎችም ሃይማኖቶች የተለየ አይደለም፡፡ በመሆኑም ባለበት ይፀና ዘንድ "ፈቅደን" እንለፈው።

ርእሳችን ሁለት ከበድና ጠጠር ያሉ ጽንሰ ሃሳቦችን ይዟል። "ከበድና ጠጠር" ስንል ጽንሰ ሃሳቦቹ የሰው ልጅ ማሰብ፣ መጠየቅ፣ መመራመር፣ መፈላሰፍ ... ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለ እረፍት የደከመባቸውና ማጠቃለያ፤ ወይም፣ ድምዳሜ ላይ ያልደረሰባቸው በመሆኑ ነው።

ብዙዎች እንደሚስማሙት ስለ አንድ ዘመን ለመነጋገር ወይም ለማጥናት በቅድሚያ የዘመኑን መንፈስ (በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ አድርጎና ጠለቅ ብሎ የሄደ ሰው፣ እኔ እማውቀው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲው ቴዎድሮስ ገብሬ ሲሆን፣ ስራዎቹን (ለምሳሌ፣ "የዘመን መንፈስ በተመረጡ የአማርኛ ሌበ ወለዶች ውስጥ"፤ እንዲሁም "በይነዲሲፒሊናዊ ሥነጽሑፍ"ን ማየት ጠቃሚ ነው) መረዳት የግድ ይሆናል። "የዘመን መንፈስ" (መሰረቱ ከወደ ጀርመን ስለሆነው "Zeitgeist" ማለታችን ነው) አንድ ራሱን የቻለ ጽንሰ ሃሳብ እና የጥናት መስክ ሲሆን፣ በተለይ ታሪክን፣ ትውልድን፣ ጥበብን፣ ማኅበረሰብን ወዘተ በአግባቡ ለመረዳትና የታሪክ ትርክትን በተገቢው ሀዲድ ለማስኬድ በጣም ጠቃሚና ሚዛናዊ የሆነ አተያይ ነው።

የቴድሮስ ገብሬን ብያኔ ስንመለከተው ደግሞ "የዘመን መንፈስ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በዋናነት ነገሮችን ራሳቸውን ሳይሆን ነገሮች በሰው ልቡና ላይ የሚያሳድሩትን ተጽእኖ ይመለከታል፡፡ ለዘመን መንፈስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ አይደለም አቢይ ጉዳዩ፤ አብዮት አይደለም ግዱ፤ ጅሃደ ወይም የመስቀል ጦርነቱ አይደለም ትኩረቱ፡፡ ትኩረቱ እነዚህ ክስተቶች በማህበሩ ልቡና ውስጥ የሚፈጥሩት ወረራ ወይም በባሕል ላይ የሚጥሉት ድባብ ነው፡፡ በብዙዎቹ ሃያሲያንና የማኅበረሰብ አጥኝዎች እምነት ደግሞ ሥነጽሑፍ ለዚህ አይነቱ ዝንቅ መንፈስ የተመቸ ማደሪያ ነው፡፡"

ወደ "እውነት" (Truth) እንምጣ።

እውነትን በተመለከተም ያለው እሰጥ አገባ እንዲህ በቀላሉ "ይሄ ነው" ተብሎ ሊገለፅ የሚችል አይደለም። በሃይማኖት በኩል ያለውን ባለበት ትተን ወደ ዓለማዊውና ፍልስፍናው ስንመጣ የምናገኘው የሃሳብ ዥንጉርጉርነት አንድ ሁለት ተብሎ የሚቆጠር አይደለም። ውስብስብ ነው።

በተለይ ፈላስፎች ትክት እስኪላቸው ድረስ ተከራክረውበታል፤ አላቆሙም። ከአገላለፆች ሁሉ ከፍ ብሎ የሚነገርለትን፣ አልበርት አነስታይንን ("እውነት አንፃራዊ ነው") ጨምሮ የዓለም ሳይንቲስቶች ሁሉ ተራቀውበታል።

እውነትን በተለያዩ አይነቶች (types) ከፍለው የሚተነትኑ ያሉ ሲሆን፣ አንዱም እውነት ግልፅ ያልሆነና ውስብስብ ጽንሰ ሃሳብ መሆኑን የሚገልፀውና እውነትን በአራት (ተጨባጭ/objective፣ ህሊናዊ/subjective፣ የጋራ እምነት/normative፣ እና አዎንታዊ/positive truth) ከፋፍሎ የሚመለከተው Lynch, M.P (2010) ሲሆን፣ እንደዚሁ ተመራማሪ አተያይ "ተጨባጭ እውነት" ማለት እምነት ከእውነት (እውነታ) ጋር በትይዩነት መቆም ሲችል ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው መጽሐፍ ያነባል እንበል። በንባቡ ሂደት ከቃላት ጋር ይነጋገራል፤ አወቃቀራቸውን ያያል፣ መልእክታቸውን ይወስዳል፣ ፕሮሰስ ያደርጋል፣ ይመራመራል፣ አንድምታቸውን ይገነዘባል ...፤ እንደ ጸሐፊው ድምዳሜ ይህ ተጨባጭ እውነት ነው። ተጨባጭ እውነት ለአድሏዊነትና ስሜት አይገዛም፤ ወይም በእነዚህ ኃይሎች አይደፈቅም።

እንደ ሊንች ትንታኔ አንድን ነገር እንደ ፈለግነው የምናደርገው ከሆነ፣ ወደ ፈለግነው የምናመጣው ከሆነና ሰዎች እኛ እንዲረዱት በፈለግነው መንገድ እንዲረዱት ካደረግነው (ልናደርገው የምንችል ከሆነ) ያ ተጨባጭ ያልሆነ ህሊናዊ) እውነት ነው። ይህንንም "We make the truth, we forge it as we see it or as we want people to see it." በማለት ያስቀምጠዋል።

ተመራማሪው "Normative truth"ን በተመለከተ የተለያዩ ማሳያዎችን ያስቀመጡ ሲሆን፣ በአጠቃላይ ግን ይህ አይነቱ እውነት ሙሉ ለሙሉ በእኛ ስሜት ላይ የተመሰረተና ስሜታችን በፈቀደው፣ ባመነውና በወደደው ልክ እውነት ነው ብለን የምንቀበው የእውነት አይነት ነው። ይህ እውነት ወይ ግለሰብ የሰራው፣ የፈጠረው፤ አለያም የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ "እውነት" ነው ብሎ የተቀበለው (በአብዛኛው መካሪና አስተማሪ የሆነ) የእውነት አይነት ነው። ለምሳሌ መግደል መጥፎ ነው፤ መንገድ ስታቋርጥ ግራና ቀኝ ተመልከት ... እና የመሳሰሉት ከዚህ የእውነት ምድብ ስር ናቸው። በአብዛኛው ይህ አይነቱ እውነት የአንድን አካባቢ ማኅበረሰብ እምነት፣ ሥርዓት-ያታ፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ ... መነሻ ያደረገ ይሆናል።

በፍልስፍናእምነትሁላችንምአምነንእስከተቀበልነው ድረስ ሀሰት የሆነው ሁሉ እውነት፤ እውነት የሆነው ሁሉ ሀሰት ነው (በ"Truth and Falsehood" ላይ የተጠበቡ፣ የእንግሊዙን ታላቅ ፈላስፋ በርትራንድ ራስልን ጨምሮ፣ ሥራዎች ስንመረምር የምናገኘው በዚሁ ሃሳብ ዙሪያ የሚሽከረከሩ ሆነው ነው)። ይሁን እንጂ ለጊዜው እውነት የመሰለ ሁሉ በእውነቱ መዝለቅ ሳይቻለው ይቀርና መሀል መንገድ እንኳን ሳይደርስ ይወድቃል፤ ወይም ራሱ ራሱን ሀሰት መሆኑን ያጋልጣል። ለዚህ በምሳሌነት የሚጠቀሱ በርካቶች ቢሆኑም፣ "መሬት ዝርግ ናት" የሚለውን የኖረ እምነትና እውነት በ"አይደለም፣ ክብ ናት" የቀየረው ጋሊሊዮ፤ እንደ የዘርአያዕቆብ ዘመነኛና የ17ኛው ክ/ዘ ፈላስፋ ዴካርት (René Descartes's philosophy) ደግሞ cogito ergo sum (I think, therefore I am)፤ አስባለሁ፣ ስለዚህ አለሁ በሚለው አገላለፁ (1637 የታተመ ስራው) የራሱን እውነት ይዞ የመጣ ሲሆን፤ እነሆ እስካሁንም የጋሊሊዮም ተቀባይነትን አግኝቶ፤ የዴካርትም በሃሳብ የበላይነቱ ከበርካታ ዘመነኞቹ ጎልቶ ሊወጣ ችሏል።

"እውነት" በየፈርጁ መታየትና መመዘኑ ደግሞ ልዩ የእውነት ገፅታ ነው። ከፖለቲካው (Truth in Politics) እንጀምር።

እውነት በፖለቲካው ዘርፍ ልዩ ይዘታን የሚላበስ ሲሆን፤ ለምሳሌ፣ የኒኮሎ ማኪያቬሊ (በተለይ "ከማንኛውም መሪ የኮት የውስጥ ኪስ ውስጥ አትጠፋም" በምትባለው "The Prince") ውስጥ፤

Politics was never about morality; rather, those who gain the most power are those who are able to adapt to the current political situation. (በግርድፉ፣ "ፖለቲካ ፈፅሞ የግብረገብ (ስነምግባር ጉዳይ አይደለም፤ ይልቁንም፣ ስልጣን የተቆጣጠሩ ኃይሎች የፖለቲካውን ሁኔታ በሚመቻቸው መልኩ የሚዘውሩበት ነው።") በማለት የገለፀው ከብዙዎች የተለየ በመሆኑ ይህ አገላለፁ ልክ እንደ ብቻው (የእሱ ብቻ) እውነት ተቆጥሮ በብዙዎች ተደጋግሞ ሲጠቀስና ሲብራራ ይታያል።

በሥነጽሑፉ ዓለምም እንደዚሁ የሥነጽሑፍን ኃያልነት በመገንዘብ የየራሳቸውን እውነት (Truth in Literature) የሚያስተላልፉ ሰዎች መኖራቸው ይነገራል። እውቅና ስመ ጥሩው እንግሊዛዊው ደራሲ ጆርጅ ኦርዌል፣ በተለይም በ"Animal Farm" እና ማእከላዊ ጭብጡን በእውነት፣ ፕሮፓጋንዳና ሳንሱር ላይ ባደረገው፣ በ"Nineteen Eighty Four" (1949) ሥራዎቹ የሚያሳየን ይህንኑ እንደሆነ ነው የዲክስቴን (Dickstein, M. Animal Farm: history as fable.) ጥናት የሚተነትነው። በሀገራችን "የእንስሳት እድር" ተብሎ በተተረጎመውና በዓለማችን እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ተነባቢነትን ባገኘው "Animal Farm" ውስጥ የእነ ስታሊን የጠቅላይነት አገዛዝ (Stalinist totalitarianism) ሁነኛ ስፍራን ይዞ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም በመጽሐፉ ውስጥ ያለው እውነት በእንግሊዝ መንግሥት እንደ ሀሰት ፕሮፓጋንዳ በመቆጠሩ እንዳይታተም ሁሉ ታግዶ የነበረ ዘመን ተሻጋሪ፣ አብዝቶም ተጠቃሽ መጽሐፍ ነው።

ይህንን ወደ ሀገራችን እናምጣው ብንል የበዓሉ ግርማ "ኦሮማይ" ለደራሲው "እውነት" ሲሆን፤ ለደርግ መንግሥት ደግሞ "ሀሰት" ሆነና ደራሲውን አስበላው። ልዩነቱ የእንግሊዝ መንግሥት ኦርዌልን አለመግደሉ ነው።

እውነትን ከታሪክ አኳያም (Truth in History) ከላይ በመጣንባቸው መንገዶች ማየትና ዓለማችን (የሀገራችንን ዝም ነው) ምን ያህል በተዛባ የታሪክ ነገራ (ትርክት)፤ እንደተጥለቀለቀች መገንዘብ፤ እውነትን በነጭ የመሰረዝና ሀሰትን በደማቁ ከስሩ የማስመር ተግባራት ሁሉ በስፋትና በተደጋጋሚነት እየተፈፀሙ እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ሌላው፣ ዘመንና እውነት የሚገለፁበትና በፈረንጆቹ 2016 (https://en.oxforddictionaries.com/word-of-the-year/word-of-the-year-2016 ይጎብኙ) የዓመቱ ምርጥ (ተዘወታሪ) ቃል የሆነው "ድህረ-እውነት" ነው። "post-truth" ማለት የሀሰት ፕሮፓጋንዳ በተጨባጭ እውነት (Objective truth) ላይ የበላይነቱን ይዞ፣ ማኅበረሰብ ላይ ተፅእኖ በመፍጠር የህዝብን አመለካከት በመበረዝ የሀሰት ትርክትን በመንዛት አንድ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ የማድረጊያ ህሊና ቢስ ስልት ነው። በምርጫ ወቅት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚጠቀሙባቸው የቅስቀሳና ምረጡኝ ስልቶችም (post-truth rhetoric) ከዚሁ የሚመደቡ በአብዛኛው በሀሰት፣ ጥላቻና የጥላቻ ንግግር፣ ዘረኝነት፣ ብልግና ላይ የተመሰረቱ (ለዚህ በምሳሌነት የትራምፕ የምረጡኝ ዘመቻ ይጠቀሳል) ናቸው።

ጥናቶቹ እንዳረጋገጡት፣ ይህ "ድህረ-እውነት" የእውነት አይነት፣ ከሀሰት ፕሮፓጋንዳም ሆነ የተዛባ (የሀሰት) ትርክ በላይ የከፋ በመሆኑ፣ ከጊዜያዊ ጥቅም ያለፈ ለማንም ምንም የማያስገኝ የስግብግቦች ፖለቲካ አካሄድና አሰራር ሲሆን፤ በሂደትም ራሳቸውን ጠልፎ የሚጥል አደገኛ የ"እውነት" ባዮቹ የክህደት "እውነት" ነው።

ሌላው የ"ዘመንና እውነት" ማሳያዎች ማኅበራዊ ሚዲያወለድ የሆኑ እውነቶች መኖራቸው ሲሆን፣ እሱም ሆን ተብሎ፣ ታስቦበትና ታቅዶ የሚሰራጭ የሀሰት ትርክት ነው። የአልኮት እና ጌንትዝኮው (Allcott, H, Gentzkow, M. Social Media and Fake News in the 2016 Election. In: Journal of Economic Perspectives.) ጥናት እንደሚያረጋግጠው The Denver Guardian፣ WTOE 5 News እና የመሳሰሉት ስራቸው ይሄ ብቻ ሲሆን፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች "ሼር" እና "ላይክ" በማድረግ ሲያታኩሱና ሲያጋድሉ የሚውሉት እነዚህ ተቋማት የሚፈበርኩትን የሀሰት ወሬ ነው። ዘመኑ በተጨባጭ ይህንን ነው የሚመስለው።

በተለይ በአደጉት ሀገራት፣ በተለይ በተለይ በአሜሪካ ስር እየሰደደ የመጣውን (አሁን አሁን ለእኛም እየተረፈ ነው)፣ የሴራ ንድፈ ሃሳብ (ኮንስፒራሲ ቲየሪ)ን መጠነ ሰፊ አውዳሚነትና ከእውነቱ እጅጉን የራቀ አሰራር እየተነጋገርንበት ካለው ዘመንም ሆነ ትውልድ ጋር አሰናስሎ በማየት ዘመኑ ምን ያህል ለሰው ልጅ አስቸጋሪ እንደሆነና እየሆነም እንደመጣ መረዳት ይቻላል።

ለዚህ አንድ ምሳሌ ወስደን እንመልከት። የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድን ወደ ሥልጣን መምጣት ተከትሎ "ዐቢይ አማራ ነው/አይደለም ኦሮሞ ነው። ዐቢይ ኦሮሞ ነው/አይደለም አማራ ነው" የሚሉ፣ ሀገርንና ሕዝብን ምንም የማይጠቅሙ መጠላለፎች ብቅ ብለው አጀንዳ ሆነውብን ስንነታረክ ነበር። ሀገርና ሕዝብ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚፈልገው በሳል አመራርን ሆኖ እያለ ለግል የፖለቲካ ሸኩቻ ሲባል ብቻ አጀንዳ እየተሰጠን ስንወዛገብ ነበር። ይህ አንዱ የሴራ ፖለቲካ አካል ነው። ሌሎችም ብዙ ብዙ አሉ።

**ማጠቃለያ**

አንዳንዶች እንደሚያምኑበት "ግማሽ እውነት ከውሸት የበለጠ አደገኛ ነው፡፡" አንዳንዶች ደግሞ እንደሚያስተምሩት "እውነት"ም ሆነ "ውሸት" ብሎ ነገር የለም፤ ዝም ብሎ መኖር ነው። "ዘመንን ከመከተል ሌላ ምን አማራጭ አለ?" የሚሉ ደግሞ አሉ። "ዘመኑ ውሸታም ከሆነ ዋሽ። ዘመኑ እምነትና እውነትን ፈላጊ ከሆነ ደግሞ አንገትህን ለእምነትና እውነት ስጥ" ነው የእነዚህኞቹ ጥብቅ መርህ።

እንደ ብፁእ አቡነ ማቲያስ ከሆነ ዘመኑ የሥነምግባር ውድቀት የሚታይበት ነው።

ብፁእነታቸው የ2007 ዓ.ም የትንሳኤ በዓልን አስመልክተው ለምእመናን የ"እንኳን አደረሳችሁ" መልእክት ሲያስተላልፉ እንደተናገሩት፤ "ዓለማችን በመልካም ሥነምግባር ከመበልፀግ ይልቅ በዘቀጠና ለአእምሮ በሚዘገንን ነውረ ኃጢያት ከፉኛ እየተናወጠች ትገኛለች። (ይህ) የሥነ ምግባር ውድቀት ሊመጣ የቻለው የሥነምግባር ትምህርቱ በፈሪሀ እግዚአሔብር ያልተቃኘ ከመሆኑ የተነሳ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።"

ለፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ዘመኑ "ከእውነት የተጣላ" የበዛበት ዘመን ነው። በመሆኑም "የፌስቡክ መንጋ" እውነትን እየሰረዘ ሀሰትን እየተካ ይገኛል። "በሬ ወለደ"ውን ሲነዛ ውሎ ሲነዛ ያድራል። ይነቅላል እንጂ አይተክልም። የዚህ ሁሉ ድምር ደግሞ ሀገርና ሕዝብን ዋጋ እያስከፈለ ይገኛል።

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን አተያይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ነው። ችግሩ ያለው "ለሆዱ ያደረው፣ በሆዱ ተሰንጎ የተያዘው ..." ክፍል ጋ ነው። እሱ ነው ሕዝብን ከሕዝብ እያጣላ፣ እያጋደለ ... የሚገኘው እንጂ ሕዝቡ ጋ ምንም ችግር የለም። ሕዝቡ ጋ እውነት አለ።

ይህ የፕሮፌሰር አስተያየት ወይዘሮ የትነበርሽ ንጉሴ ይመሩት የነበረ የሰላምና እርቅ ኮሚሽን ተቋም የተደገፈ ሆኖ ነው የሚገኘው። ተቋሙ በ85 የሀገሪቱ ከተሞች ተዘዋውሮ ባነጋገረበት ወቅት ከሕዝቡ ያገኘው መልስ "እኛ ጋ ችግር የለም። የሚያጋደሉን ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ናቸው። እነሱን እዛው ሀይ በሉልን" የሚል ነበር። (ጉዳዩ በወቅቱ በኢቴቪ ፕሮግራም ተሰርቶበት ነበር።)

ዘመንና እውነት በዚህ ደረጃ የተፋጠጡበት፤ "እውነቱን ተናግሮ እመሸበት ማደር"ተረት የሆነበት ነው።

በመጨረሻው መጨረሻው "እውነትን መናገር ሰውን ነፃ ለማውጣት ከፈጣሪ መንፈስ ጋር መተባበር ነው፡፡ ውሸት ሰውን ያለ አግባብ ለመቆጣጠር የሚደረግ የስጋ ሥራ ነው፡፡ ውሸት ከራስ ወዳድነት የሚመጣ የሐጢያት ባህሪ ነው፡፡" በማለት ሃሳባቸውን (መንፈሳዊ ቃሉን) ያካፈሉንን በማመስገን፤ የተሻለ ነገን እንመኛለን።

ኢኮኖሚ

## ስኬት

# ሕክምናን ከትምህርት፣ የቡና ንግድን ከቤተሰብ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ሴቶች በማንኛውም የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው መስራት እንደሚችሉ በተለያዩ መስኮች ተሰማርተው ውጤታማ ከሆኑ ሴቶች መረዳት ይቻላል። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ በቤት ውስጥ ኃላፊነት ተጠምደው ውለው እያደሩም ነው። አደባባይ እንዳይወጡ፣ በየትኛውም ሥራ ተሰማርተው እንዳይሰሩ በሚያደርጉ ተጽእኖዎች ሳቢያ የሥራ ተሳትፏቸው እንዲጠብ ተደርጎ የኖረ ቢሆንም፣ ይህን አመለካከት ሰብረው በመውጣት በተሰማሩባቸው መስኮች ውጤታማ የሆኑ በርካታ ሴቶችን በአብነት መጥቀስ ይቻላል።

ሴቶች በራሳቸው በቀጥታ ከሚያበረክቱት ድርሻ በዘለለ በየትኛውም የወንዶች ስኬት ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ አላቸው። ‹‹ከእያንዳንዱ ስኬታማ ወንድ ጀርባ አንዲት ሴት አለች›› የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ ይህ አስተዋጿአቸው በይፋ እውቅና ሲሰጠው አይስተዋልም። ያም ቢሆን ሴቶች በማንኛውም የሥራ መስክ የጀርባ አጥንት ሆነው ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን ለማሳካት የሚቀድማቸው የለም። በተለይም በግብርናው ዘርፍ ሴቶች ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ስለመሆኑ መረጃዎች ያመላክታሉ።

ከግብርና ሥራ አንዱ በሆነው በቡና ሥራ ተሰማርተው የኢትዮጵያን ቡና ከምርት ጀምረው ለዓለም ገበያ በማስተዋወቅ ረገድ ጉልህ አበርክቶ ያላቸው ሴቶች ጥቂት የሚባሉ አይደሉም። ከእነዚህ መካከልም የጡዊ አማሮ ቡና ላኪ ድርጅት መስራችና ባለቤት ወይዘሮ ቅድስት ብሩ አንዷ ናት። ቡና አምራች ከሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ በሆነው ደቡብ ክልል ጌዲኦ ዞን ዲላ ከተማ ተወልዳ ያደገችው ወይዘሮ ቅድስት፣ የሕይወት ጥሪዋ ከሆነው የሕክምና ሙያ ወጥታ ወደ ቡና ሥራ ተሰማርታም ውጤታማ መሆን ችላለች።

ወይዘሮ ቅድስት ከሕክምና ሙያ ወጥታ ወደ ቡና ሥራ የገባችው በቤተሰቦቿ ምክንያት ነው። የዛሬዋ የስኬት ገጽ እንግዳችን ለበርካታ ዓመታት ካገለገለችበት የሕክምና ዘርፍ ወጥታ ከምርት ጀምሮ ባለው ሂደት ቡናን አዘጋጅታ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ እያቀረበች ትገኛለች።

የሕክምና ሙያ ነብሷ አጥብቃ የምትሻው የሙያ ዘርፍ እንደሆነ የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ በነርሲንግ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪዋን በያዘች ማግስት በቅዱስ ጳውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ከስድስት ዓመታት በላይ አገልግላለች። ወላጅ አባቷ ያቀረቡላትን የንግድ ሥራ አሻፈረኝ በማለት ነበር ያኔ በእጅጉ አጥብቃ ትወደው ወደ ነበረው የሕክምና ዘርፍ የገባችው። በሕክምናው ዘርፍ ሕዝቧን ማገልገል በመቻሏ ደስተኛ ነበረች።

ቤተሰቦቿ ቡና አምራችና አቅራቢ እንደመሆናቸው የቡና ሥራን በቅርበት እየተመለከተች ያደገችው ወይዘሮ ቅድስት፣ የሕክምና ሥራዋን እየሠራች የቤተሰቦቿን የቡና ንግድ ታግዝ ነበር። በምርትና አቅራቢነት የተሰማሩት ወላጅ አባቷ ቡናውን ወደ አዲስ አበባ አምጥተው በሚሸጡበት ወቅት ከሕክምና ሥራዋ ጎን ለጎን ቤተሰቦቿን ማገዟ ወደ ቡና ሥራ ውስጥ ቀስ በቀስ እንድትገባ አስገድዷታል።

በቡና ልማትና ኤክስፖርት ዘርፍ የተሰማሩት ወላጅ አባቷ የቡና ሥራውን እንድታግዛቸው ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸው መሆኑን ያስታወሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ በሙሉ አቅሟ ለማገዝ ወስና ከቡና ሽያጭ በተጨማሪ በቡና ዝግጅትና በቡና ቅምሻም እንዲሁ ያላትን ተሳትፎ ከፍ አድርጋለች። በዚህ ጊዜ ‹‹የነብስ ጥሪዬ ነው›› የምትለውን የህክምና ሙያ ገታ በማድረግ የሙሉ ጊዜ ሥራዋ አድርጋ ከምርት እስከ ኤክስፖርት ያለውን የቡና ሥራ ተቀላቅላለች።

ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ሙሉ ጊዜዋን ለሥራው የሰጠችው ወይዘሮ ቅድስት፣ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ በወላጅ አባቷ የቡና እርሻ በልማቱ በስፋት ተሰማርታለች፣ በኤክስፖርት ዘርፍ ላይ እየሰራች ትገኛለች። በአሁኑ ወቅት ግን የእርሻ ሥራው በተለያዩ ምክንያቶች መቋረጡን ጠቅሳለች። ይሁንና በ2012 ዓ.ም የቡና ፈቃድ በማውጣት ‹‹ጡዊ አማሮ ቡና ላኪ›› የተሰኘውን ኤክስፖርት ኩባንያ አቋቁማ እየሰራች ትገኛለች። ዘርፉ የምታውቀው በመሆኑ ብዙ እንዳልከበዳት የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ መነሻዋን በደቡብ ክልል አማሮ በማድረግ ምርቱን አዘጋጅታ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ተሰናዳች።

በወቅቱ ቢሮ ከፍታ ሁለት ሠራተኞችን በመያዝ ወደ ሥራው የገባች ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት ለ12 ሴቶችና ለአምስት ወንዶች በድምሩ ለ17 ሰዎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር ችላለች። በአማሮና ይርጋጨፌ አካባቢ የሚመረተው ቡና ታጥቦ፣ ደርቆና ተለቅሞ የሚዘጋጅበት ማጠቢያ ማሽን በመትከል የተዘጋጀ ቡና ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ ታቀርባለች።

“የቡና ሥራን ከታች ከእርሻው ጀምሮ አውቀዋለሁ” የምትለው ወይዘሮ ቅድስት፣ የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ መሆን እንዲችል በጥራት መመረትና መዘጋጀት እንዳለበት ታስገነዝባለች። ለዚህም መንግሥትን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ኃላፊነት እንዳለበት ገልጻለች። በተለይም የቡና ዋጋ በዓለም ገበያ እየወረደ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ተወዳዳሪ ለመሆንና ከፍ ያለ ዋጋ እንዲያወጣ ለማድረግ ቡናውን በጥራት ማዘጋጀት እንዳለ ሆኖ በሀገር ውስጥ የሚገዛበት ዋጋና ኤክስፖርት የሚደረግበት የተመጣጠነ መሆን እንዳለበት ገልጻለች።

ከዓለም ገበያ ጋር እኩል መወዳደር እንዲቻል ምርትና ምርታማነትን ከማሳደግ በተጨማሪ ጥራትና ዋጋ ላይ መሰራት እንዳለበት የምታስገነዝበው ወይዘሮ ቅድስት፣ ምርቱን በሁለት መንገድ ለገበያ እንደምታቀርብም ነው የምትገልጸው። አንደኛው አቅርቦት ነው፤ ይህም ማለት ቡናውን በማዘጋጀት ለላኪዎች ማቅረብ ነው። ሁለተኛው ዝግጅቱን የጨረሰ ቡና በቀጥታ ወደ ውጭ ገበያ መላክ ሲሆን፣ ይህንንም ማድረግ መቻሏን አስረድታለች።

እሷ እንዳለችው ፤ የቡና ማጠቢያና ማዘጋጃው ያለው በደቡብ ክልል አማሮና ይርጋጨፌ ነው። ቡናውን ከአካባቢው አርሶ አደሮች በቀጥታ ታገኛለች። አማሮ፣ ይርጋጨፌና ወናጎ በሚባሉ አካባቢዎች ከሚገኙ 86 ቡና አምራች አርሶ አደሮች ጋር ትስስር መፍጠርም ችላለች። እነዚህ አርሶ አደሮች በቋሚነት ያመረቱትን ቡና ለእሷ ያቀርባሉ። በተጨማሪም ሌሎች አርሶ አደሮች በወቅቱ ባለውና በተተመነው ዋጋ መሰረት ተገቢውን ክፍያ ፈጽመው ቡና በመረከብ ከአርሶ አደሩ የሰበሰቡትን ቡና በአካባቢው በሚገኘው የቡና ማጠቢያና ማበጠሪያ ማሽን አጥበው አድርቀውና ለቅመው ካዘጋጁ በኋላም እንደወቅቱ ገበያ በሚያዋጣት መንገድ ቡናውን ለገበያ ታቀርባለች።

የዓለም የቡና ዋጋ እነሱ ገዝተው ካዘጋጁበት ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ከሆነ በቀጥታ ኤክስፖርት እንደሚልኩ የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ 70 በመቶ የሚሆነው ገበያ አውሮፓ ሀገራት ቤልጅየም፣ ጀርመንና ፈረንሳይ መሆኑን ነው የገለጸችው። አሁን አሁን ደግሞ ወደ ኤዥያ ሀገራት ጭምር ገበያዋን እያሰፋች ትገኛለች። ጡዊ አማሮ ቡና ላኪ በዓመት በአማካኝ ከ1000 እስከ 1500 ቶን ቡና የማዘጋጀትና የማቅረብ አቅም እንዳለው የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ ከ300 እስከ 350 ቶን ያህል ቡና ደግሞ ለውጭ ገበያ እያቀረበች መሆኑን አጫውታናለች።

ወደፊትም አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን ለማግኘት በሀገር ደረጃ የተለያዩ ጥረቶች እንደሚደረጉ ያመላከተችው ወይዘሮ ቅድስት፣ አዳዲስ የገበያ ዕድሎችን ለማግኘት ዓለም አቀፍ በሆኑ ኤክስፖዎች ላይ መሳተፍ አንደኛው አማራጭ እንደሆነ ነው ያስረዳችው።

ለዚህም በቡና ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢትዮጵያውያን ሴቶችን ብቻ ያቀፈው ማህበር “**women in coffee Ethiopia**” ትልቅ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጻለች። እሷ እንዳለችው ማህበሩ፣ የማህበሩ አባል የሆኑ ሴቶች ዓለም አቀፍ በሆኑ ኤክስፖዎች ላይ ተሳትፈው ቡናቸውን መሸጥና ማስተዋወቅ እንዲችሉ በሚያደርገው እገዛ በቡና ሥራ የተሰማሩና አባል የሆኑ ሴቶች የኢትዮጵያን ቡና በተለያዩ የዓለም ሀገራት ተንቀሳቅሰው እየሸጡና እያስተዋወቁ ይገኛሉ።

በተለየ መንገድ ከሴት ቡና አልሚዎችና አቅራቢዎች ብቻ የመግዛት ፍላጎት ያላቸው ዓለም አቀፍ ቡና ገዢዎች ስለመኖራቸው የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ ለዚህም ማኅበሩ መኖሩ ጠቃሚ እንደሆነ ነው ያስረዳችው። ሴት ቡና አልሚዎችን ላኪዎችንና አቅራቢዎችን ብቻ ፈልገው የሚመጡ ዓለም አቀፍ ቡና ገዢዎች በማኅበሩ አማካኝነት በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶችን በቀላሉ ማግኘት እየቻሉ እንደሆነ ጠቅሳ፣ በዚህም ተጠቃሚ እንደሆነች ነው የገለጸችው። ከሴት ቡና ላኪ መግዛት ፈልጎ ከጀርመን ለመጣ ቡና ገዢ መሸጥ የቻለችበትን ሁኔታም ጠቅሳለች።

ወይዘሮ ቅድስት እንዳብራራችው፣ ማኅበሩ በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶች ዓለም አቀፍ በሆኑ ኤክስፖዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ብርቱ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል። አሁን ላይ ደግሞ በአፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፍ የቡና ኤክስፖ አዲስ አበባ ላይ ማዘጋጀቱ ይዞን ከሚመጣው የገበያ ዕድል በተጨማሪ በርካታ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል። ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የተወጣጡ ቡና ገዢዎች ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ኢትዮጵያ የቡና መገኛ ብቻ ሳትሆን የቡና መዳረሻ እንደሆነች ጭምር የሚረዱበትና ቡናውን ከምርቱ ጀምረው በመረዳት መግዛት የሚችሉበትን እድልም ይፈጥራል።

ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ቡና ገዢዎች ከሴት ቡና አምራችና ላኪዎች ጋር በቀላሉ መቀራረብ የሚችሉ በመሆኑ በቡና ሥራ ላይ የተሰማሩ ሴቶች ንግዳቸውን ለማሳደግ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ከዚህ ቀደም በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶች በተለያዩ ዓለም ሀገራት ተዘዋውረው ቡና የሚሸጡበትና የሚያስተዋውቁበት መንገድ ረዥምና ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ ነበር፤ አሁን ላይ ግን ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽን በቡና መገኛ ሀገር ኢትዮጵያ ላይ መካሄዱ ለዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል። ወይዘሮ ቅድስት እንደ ሀገርም ሆነ በግሏ ከኢግዚቢሽኑ ትልቅ ውጤት ትጠብቃለች።

ለአንድ ሳምንት በሚቆየው ዓለም አቀፍ የቡና ኤግዚቢሽንና ኮንፍረንስ ቡናን መሸጥ፣ ማስተዋወቅና አዳዲስ ገበያን ማግኘት እንደሚቻል የጠቀሰችው ወይዘሮ ቅድስት፣ ቡና የኢትዮጵያውያን ሀብት መሆኑን ለሚመጡት እንግዶች የሚያሳዩበት እንደሆነ ተናግራለች። በተለይም በቡና ሥራ የተሰማሩ ሴቶች እንዲሁም ሀገሪቷም ከኤክስፖው ተጠቃሚ እንደሚሆኑና ትልቅ ዕድል እንደሆነ ጠቁማለች።

ሴቶች በማንኛውም መስክ ውጤታማ ሥራ ይሠራሉ የምትለው ወይዘሮ ቅድስት፣ በተለይም በቡና ሥራ ሴቶች ትልቅ ድርሻ አላቸው ነው የምትለው። ሴቶች ከእርሻ ሥራው ጀምሮ በለቀማ፣ በማጠብና በማቀነባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውና ለቡና ሥራ የጀርባ አጥንት እንደሆኑ ነው የገለጸችው። እሷ እንዳለችው፣ ሴቶች በቡና ሥራ ከ80 በመቶ በላይ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፣ በተለይም በለቀማ ወቅት ቀይ ቀዩን ቡና ለይቶ በጥንቃቄ ለቅሞ በማቅረብ በኩል ሴቶች ይመረጣሉ።

ቡናን በማዘጋጀትና በመላክም እንዲሁ ሴቶች ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው የምትገልጸው ወይዘሮ ቅድስት፣ ይሁንና የልፋታቸውን ያህል ግን ተጠቃሚ አይደሉም ትላለች። ሴቶች በቡና ሥራ እያበረከቱ ባለው አስተዋጽኦ ልክ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊና ተገቢ እንደሆነም ታመለክታለች። ለዚህም በዘርፉ የተሰማሩ ሴቶች በአንድነት ተጠናክረው መሥራት እንዳለባቸው ነው የገለጸችው።

በዘርፉ የተሰማሩ ሴቶች እንዲበራከቱ ከቅጥር ጀምሮ ዕድሉን ለሴቶች መስጠት በዘርፉ የተሰማሩትን ወደ ማኅበሩ በማምጣት ማኅበሩ በሚያዘጋጃቸው የተለያዩ ስልጠናዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ መረጃ መስጠት እንደሚገባም ነው ያስገነዘበችው። መረጃ ሀብት ነው የምትለው ወይዘሮ ቅድስት፣ ሴቶች መረጃ ካገኙና ዕድል ከተሰጣቸው በማንኛውም መስክ መሥራት የሚጠበቅባቸው እንደሆነ ነው ያመላከተችው።

የነብስ ጥሪዬ የምትለውን የነርሲንግ ሙያ ወደ ጎን በመተው በቡና ሥራ የተሰማራችው ወይዘሮ ቅድስት፣ ዛሬም ድረስ ለሕክምና ሙያ ልቧ ክፍት እንደሆነና በቀጣይም የሕክምና ሥራዋን ጎን ለጎን የማስኬድ ዕቅድ እንዳላት አጫውታናለች። የሕክምና ሙያ ሰዎችን መርዳት ማገዝ በመሆን በእጅጉ የሚያስደስታት መሆኑን ጠቅሳ፣ ማኅበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት ረገድም ንቁ ተሳትፎ ያላት መሆኑን ገልጻለች። እሷ እንዳለችው ምርቱን በምታገኝበት አካባቢ የሚገኙ ነዋሪዎችን በተለያየ መንገድ የምታግዝ ሲሆን፣ በተለይም ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት እንዲሁም መንግሥት ለሚያደርገው ጥሪ ምላሽ በመስጠት ማኅበራዊ ኃላፊነቷን እየተወጣች ትገኛለች።



ወይዘሮ ቅድስት ብሩ

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## ዘንድሮ እንደሚጠናቀቅ የሚጠበቀው

# የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል ግንባታ ፕሮጀክት



**በኃይሉ አበራ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረተሰቡን መሠረታዊ ችግሮች የሚቀርፉና ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን እየገነባ ለአገልግሎት ክፍት እያደረገ ይገኛል። ፕሮጀክቶቹ የመዲናዋን ውበት የሚጠብቁ፣ ለኑሮ፣ ለመዝናኛ፣ ለአገልግሎት ምቹ እንዲሆኑ ተደርገው የሚገነቡም ናቸው።

ከተማ አስተዳደሩ ፕሮጀክቶቹን እያስገነባ ያለው የግዙፍ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት በማቋቋም እንዲሁም በከተማዋ ኮንስትራክሽን ቢሮ በኩል ነው። ሜጋ ፕሮጀክቶች ጽሕፈት ቤቱ ከሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች መካከልም አቃቂ አካባቢ የሚገነባው የሴቶች ተሐድሶ እና የክህሎት ማበልጸጊያ ማዕከል እና የኢንዱስትሪ ክላስተር፣ አይሲቲ አካባቢ የሚገነባው የሥራ አመራር አካዳሚ፣ በመዲናዋ መውጫ በሮች ተገንብተው ወደ ሥራ የገቡና እየተገነቡ የሚገኙ የግብርና ምርቶች የገበያ ማዕከላት ይገኙበታል።

ግንባታቸው በጥሩ አፈጻጸም ላይ የሚገኙት መገናኛ ሾላ አካባቢ የሚገነባው የየካ ፓርኪንግ ሁለት እና እዚያው መገናኛ አካባቢ እየተገነባ የሚገኘው የተለያዩ የትራንስፖርት ተቋማት መሥሪያ ቤቶች ህንጻ ግንባታ ሌሎች ከተማ አስተዳደሩ እያስገነባቸው የሚገኙ መሠረተ ልማቶች መካከል ተጠቃሾች ናቸው።

በከተማዋ እምብርት በርካታ አገልግሎቶችን እንዲሰጥ ታስቦ ግንባታው እየተጠናቀቀ ያለው የዓድዋ ሙዚየም ግንባታ፣ ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ የገባው የጎተራ ጎፋ ማዞሪያ ሣር ቤት መንገድ ማሳለጫ እንዲሁም አብዛኛው ግንባታው ተጠናቆ ወደ ሥራ የገባው የቃሊቲ ቱሉ ዲምቱ መንገድ ግንባታም እንዲሁ በከተማ አስተዳደሩ የተገነቡ ፕሮጀክቶች ናቸው።

ከተማ አስተዳደሩ የከተማዋን የተጠራቀሙ የመሠረተ ልማት ችግሮች ለመፍታት የሚያካሂደውን ግንባታ ቀጥሏል። በዚህም የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ለማስፋት የሚያግዙ የሆስፒታል ማስፋፊያዎችን ከማድረግ በተጓዳኝ በከተማዋ ማስፋፊያ አካባቢዎች አዳዲስ ሆስፒታሎችን እየገነባም ይገኛል። ሆስፒታሎቹ የሚገነቡት በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ጀሞ አካባቢ እና በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቤቴል አካባቢ ነው።

የሆስፒታሎቹ መገንባት ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥሩ እየጨመረ ለመጣው በማስፋፊያ አካባቢ ለሚኖረው የመዲናዋ ሕዝብ የጤና አገልግሎት ፍላጎትን ለመመለስ ፋይዳቸው ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል። በእነዚህ አካባቢዎች የመዲናዋ ሕዝብ የሕክምና አገልግሎት ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ እንግልት ሲደርስበት ኖሯል። ወረፋ ጥበቃው፣ የሆስፒታሎች ርቀት፣ አልጋ ለማግኘት ያለው ፈተናና የመሳሰሉት የከተማዋን ሕዝብ በእጅጉ ሲገዳደሩት የቆዩ ችግሮች መሆናቸው ሲነገር ይደመጣል።

የከተማ አስተዳደሩም ይህንን በመመልከት ሆስፒታል በሌለባቸው የከተማዋ ክፍለ ከተሞች የአዳዲስ አጠቃላይ ሆስፒታሎች ግንባታ በአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ በኩል እያካሄደ ይገኛል። የዛሬው መሠረተ ልማት አምዳችን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ እየተገነባ የሚገኘውን ሆስፒታል የግንባታ ሂደት ያስቃኘናል፡፡

የአዲስ አበባ ዲዛይንና ግንባታ ሥራዎች ቢሮ የኮንትራት አስተዳደር ባለሙያ ወይዘሮ ፈትሃ ነስሩ እንዳብራሩት፤ የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል የከተማ አስተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚያስገነባቸው ፕሮጀክቶች አንዱ ነው። በከተማዋ የጤና አገልግሎት ፍላጎት ከፍተኛ በመሆኑ እና ሆስፒታሎች በየክፍለ ከተሞቹ ባለመኖራቸው የተነሳም ህብረተሰቡ ራቅ ወዳሉ አካባቢዎች በመሄድ አገልግሎቱን ለማግኘት ሲገደድ ቆይቷል። በአካባቢው የመንግሥት ሆስፒታል የሌለ በመሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ የሆስፒታል አገልግሎት እያገኘ ያለው ረጅም ርቀት በመሄድ እና ከፍተኛ ወጪ በማውጣት መሆኑን ወይዘሮ ፈትሃ ተናግረዋል። የሆስፒታሉ ግንባታ መጠናቀቅ ህብረተሰቡ በጉጉት እየተጠባበቀ እንደሚገኝም ነው ያመለከቱት።

በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሰባት ቤቴል አካባቢ የሚገነባው ይህ አጠቃላይ ሆስፒታል ግንባታው መንግሥታዊ በሆነው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን (ኢኮስኮ) የግንባታ ሥራ ተቋራጭነት እየተካሄደ መሆኑን የኮንትራት አስተዳደር ባለሙያዋ ጠቅሰው፣ ተቋራጩ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የሚገነባውን ሆስፒታል ጨምሮ ሌሎች ሰፊ ሀገር አቀፍ መሠረተ ልማቶችን እየሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። ከተማ አስተዳደሩ በጀት በሌለበት ሁኔታ ላይ ሆኖ የጤና መሠረተ ልማቱ ለህብረተሰቡ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ከፍተኛ በጀት ይዞ በልዩ ትኩረት የሚያስገነባው መሆኑንም ይናገራሉ።

የኮልፌ ጠቅላላ ሆስፒታል ግንባታ ተጠናቅቆ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የአካባቢው ማህበረሰብ የሆስፒታል አገልግሎት ለማግኘት በሚያደርገው ጥረት የሚደርስበትን እንግልት ያቃልላል የሚል እምነት እንደተጣለበትም ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የዚህ ሆስፒታል ግንባታ አብዛኛዎቹ የስትራክቸር ሥራዎች ተጠናቅቀዋል፤ በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ የግንባታው አፈጻጸም 55 ነጥብ 24 በመቶ ላይ ይገኛል።

ሆስፒታሉ በ33 ሺ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ሲሆን፣ ከዚህም ውስጥ 11 ሺ 300 ካሬ ሜትሩ ሕንፃዎች ያረፉበት ቦታ ነው። አጠቃላይ በጀቱም ከሶስት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ነው።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሆስፒታሉ ግንባታ በፈጠረው የሥራ እድልም (በቋሚና እና ኮንትራት ቅጥር ከ70 በላይ እንዲሁም በጊዜያዊ የሥራ እድል ከ500 በላይ ሰዎች ) ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ግንባታው ለሆስፒታል አስፈላጊ የሆኑ እንደ ጋራዥ፣ መጋዘን፣ የተሟላ የመኪና መቆሚያ፣ የውሃ እና የመብራት አገልግሎት መስጫ፣ የቆሻሻ ማስወገጃ፣ የተሟላ መታጠቢያና መጸዳጃ ቤት፣ የኤክስ-ሬይ(x-ray)፣ እና ለሕክምና አስፈላጊ የሆኑ ክፍሎች ይኖሩታል።

የኮልፌ ቀራንዮ ጠቅላላ ሆስፒታል የሎት አንድ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር በዕውቀት መራ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ የግንባታ ፕሮጀክቱ 14 ሕንጻዎች ያሉት ሲሆን፣ ግንባታውም በሎት ተከፋፍሎ እየተካሄደ ይገኛል። በሆስፒታሉ ሎት አንድ፤ ሕንፃ አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ዘጠኝ፣ አስር፣ አስራ ሁለትና ሕንፃ አስራ አራት ይገኙበታል። በሎት ሁለት ሥር ደግሞ ሕንፃ አምስት፣ አስራ አንድ፣ አስራ ሶስት እና ሕንፃ ስምንት የሚባሉ በሎኮች ይገኙበታል። ሎት አንድ 323 አልጋዎች፤ ሎት ሁለት አጠቃላይ 100 አልጋዎች በጠቅላላው 423 ያህል አልጋዎች ይኖሩታል።

ግንባታው በግንባታ ቴክኖሎጂዎች በተዘጋጀ የአርማታ ሙሌት የሚያከናወን ነው። በመሆኑም የኮንክሪት ሙሌት ሳይት ላይ የሚዘጋጅ ሳይሆን ተዘጋጅቶ በሚቀርብ አርማታ በፓምፕ የሚሞላ ነው። የሥራ ተቋራጩ በቂ ልምድ ያለው እና ብዙ የመንግሥት እና የግል ፕሮጀክቶችን በወቅቱ አጠናቆ ያስረከበ ተቋራጭ መሆኑንም ገልጸዋል። የሆስፒታሉ ግንባታ እ.ኤ.አ ሐምሌ 2 ቀን 2021 የተጀመረ መሆኑን ጠቅሰው፣ ግንባታውን በተያዘው 2016 በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ እየተሰራ መሆኑንም ተናግረዋል።

የሆስፒታሉ ግንባታ የአእምሮ ሕክምና፣ የእናቶች እና የሕፃናት ሕክምና፣ የካንሰር ሕክምና መስጫ እና ማዋለጃ፣ የድንገተኛ ክፍል፣ ላብራቶሪ ፣ አክስ-ሬይ/ X-ray/፣ የጨረር ሕክምና (Nuclear medicine)፣ የሥነ-ልቦና ሕክምና መስጫ፣ የቀዶ ጥገና ሕክምና መስጫ፣ ማቀዝቀዣ ክፍል፣ ቤተመጻሕፍት፣ ካፍቴሪያ እና



**በአሁኑ ወቅት አጠቃላይ የግንባታው አፈጻጸም 55 ነጥብ 24 በመቶ ላይ ይገኛል።**

መሰብሰቢያ አዳራሽ የያዘ ነው።

የአእምሮ ሕሙማን፣ የእናቶች እና ሕጻናት፣ የኤክስ-ሬይ እና የተለያዩ ምርመራዎች እንዲሁም የካንሰር ሕክምናን ጨምሮ ህብረተሰቡ የተቸገረባቸውንና ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳረግባቸውን ሕክምናዎች አቅፎ የሚይዝ ሆስፒታል እንዲሆን ተደርጎ እየተገነባ ይገኛል። ከአንዳንድ ትላልቅ ሆስፒታሎችም በበለጠ በተሟላ ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጥ ታስቦ የሚገነባ ትልቅ ሆስፒታል ነው ብለዋል።

የግንባታ ሂደቱ እንደተጀመረ በቁፋሮ ሂደቱ ላይ ባጋጠመው ጠንካራ አለት እንዲሁም ፤ አንዳንድ የዲዛይን ጉዳዮች የተወሰነ መዘግየት መታየቱን ጠቅሰው፣ አሁን ግንባታው በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

**የሎት አንድ ግንባታ በሕንፃ ሁለት እና ሕንፃ ሶስት፡-** ለአእምሮ ጤና ክሊኒክ፤ ለኦብስቴሪክና ጂኒዮሎጂ ሕክምና፤ ለውስጥ ደዌ ሕክምና አገልግሎት የሚውሉ ከምድር በታች ወለሎች፣ በመጀመሪያ ወለል እና በሁለተኛ ወለል በአጠቃላይ 66 አልጋዎች ይኖሩታል።

**ሕንፃ አራት፡-** ግራውንድ ወለል ጨምሮ በጠቅላላው አራት ወለሎች ሲኖሩት የእናቶች ሕክምናን ጨምሮ ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ አጠቃላይ 71 አልጋዎች የማስተናገድ አቅም ያለው ነው።

**ሕንፃ ስድስት እና ሕንፃ ሰባት፡-** በግራውንድ ወለሉ ስድስት ክፍሎቸ ይኖሩታል። የመጀመሪያ ወለል፣ ሁለተኛ ወለል እና ሶስተኛ ወለልን ጨምሮ ለተለያዩ የሕክምና አገልግሎቶች የሚያገለግሉ 81 አልጋዎች የማስተናገድ አቅም አለው።

**ሕንፃ ዘጠኝ እና ሕንፃ 12፡-** ሕንጻዎቹ በተመሳሳይ ግራውንድ ወለልን ጨምሮ በጠቅላላው አራት ወለሎች ሲኖሯቸው፣ በግራወንድ ወለሉ ላይ የፔዲያትሪክ እና የሳይካትሪክ ድንገተኛ አገልግሎቶች የሚሰጡባቸውን ክፍሎች ጨምሮ በመጀመሪያ ወለል፣ በሁለተኛ ወለል እና በሶስተኛ ወለል ላይ ለሌሎች የሕክምና አገልግሎቶች የሚውሉ በጠቅላላው 51 አልጋዎችን ይይዛል።

**ሕንፃ 10፡-** የሕንጻው የመጀመሪያው ቤዝመንት ለላብራቶሪ አገልግሎት የሚውል ሲሆን፣ የግራውንድ ወለሉ መጋዘን እና የምግብ ማዘጋጃ ቤትን ጨምሮ ለካፍቴሪያ አገልግሎት የሚውል ግንባታ ተካተውበታል። የዚህ ሕንፃ የመጀመሪያው ወለል ደግሞ የማገገሚያ፣ የቅድመ ኦፕሬሽን ክፍልንና የስቴራላይዜሽን ክፍሎች አሉት።

**ሕንፃ 14፡-** ከምድር በታች በሁለተኛው (ሰከንድ ቤዝመንት) ወለሉ ላይ ዘጠኝ የሕሙማን አልጋዎችና ሁለት የፕሮሲጀር ክፍሎች ይኖሩታል። ከምድር በታች የመጀመሪያው (ፈርስት ቤዝመንት) ወለል ሕክምናቸውን ጨርሰው ለሚወጡ ታማሚዎች የሚሆኑ 20 የምርመራ ክፍሎች አሉት። በምድር (ግራውንድ) ወለሉ ላይም ለድንገተኛ እና የወጪ ታካሚዎች የሚያገለገሉ 17 የምርመራ ክፍሎች እንዲሁም ለውጭ ታማሚዎች የሚውል መድኃኒት ቤትን ያካተተ ነው።

በሕንጻ 14 የመጀመሪያው ወለል ለጥርስ ሕክምና ክሊኒክ፣ ለላቦራቶሪ እና ለኦርቶዴንቲክስ፣ ለፕሮስቶዶንቲክስ፣ ለኤክስ-ሬይ ክፍሎች እንዲሁም ሁለት ለምርመራ ክፍሎች፣ ለስቴራላይዜሽን ክፍሎች እና ለመድኃኒት ቤቶች የሚውሉ ግንባታዎች ተካተውበታል። አራት ለጂንኮሎጂ (Gnnecology) የሚውሉ ክፍሎች፣ ሁለት የአልትራሳውንድ ክፍሎች እና ስድስት የምርመራ ክፍሎችንም የያዘ ግንባታ ነው።

የሄሞዲያለሲስ ክፍሎቹም ለሶሻል አገልግሎቶች መስጫ የሚውሉ ስምንት አልጋዎችም እንዲኖሩት ተደርጎ እየተገነባ ይገኛል። በዚሁ ሕንጻ 14 ሁለተኛ ወለል ላይ የዴይ ኬር፣ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት እድሜ ያላቸው ሕፃናት መዋያ ክፍሎች፣ የአስተዳደር ቢሮዎችንና የስብሰባ አዳራሾችን ያካተተ መሆኑም አብራርተዋል።

ኢንጂነር በዕውቀት እንዳብራሩት፤ ግንባታው በአንድ ጊዜ 130 መኪናዎችን ማስተናገድ የሚችል የመኪና ማቆሚያ ይኖሩታል። በቀን ለ500 ሕሙማን አገልግሎት መስጠትም ይችላል።

በሎት ሁለት ግንባታው የሕንፃ አምስት፣ አስራ አንድ፣ አስራ ሶስት እና ሕንፃ ስምንት ግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

**ሕንፃ አምስት፡-** በጠቅላላ 68 አልጋዎች ያሉት ሲሆን በግራውንድ ወለል ላይ የራዲዮኒውክላር እና ራዲዮ ፋርማርሲ ክፍሎች ይኖሩታል። በመጀመሪያው ወለሉም የሰርጂካል አይሲዩ ሰባት የአልጋ ክፍሎች ይኖሩታል። በሁለተኛው ወለል ላይ ፔዲያትሪክስ አምስት የአልጋ ክፍሎች፣ የአይሶሌሽን ክፍሎች አሉት። እንዲሁም በሶስተኛ ወለሉ የውስጥ ሕክምና ስድስት የአልጋ ክፍሎች፣ የአይሶሌሽን እና ፕሮሲጀር ክፍሎች አሉት። ሕንፃ 11፣ 13 እና 8 አጠቃላይ 32 አልጋዎች አሉት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢሬቻ የሰላም፣ የአንድነትና ወንድማማችነት ማጽኛ!

በኢትዮጵያ በተያዘው መስከረም ወር በርካታ በዓላት ተከብረዋል። የአዲስ ዓመት፣ የመስቀል ደመራና የመውሊድ በዓላት በተከታታይ በደማቅ ሥነ ሥርዓትና ፍጹም ሰላም በሆነ መንገድ ተከብረዋል፣ የበርካታ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ማንነት መገለጫ የሆኑ አዲስ ዓመት በዓላትም በደማቅ ሥነ ሥርዓት ሲከበሩ ሰንብተዋል።

ሁሉም በዓላት የበዓላቱ ባለቤቶች፣ የፌዴራል መንግሥቱና የክልል መንግሥታትና የተለያዩ የአስተዳደር እርከኖቻቸውና በዓላቱ የሚመለከታቸው የተለያዩ ተቋማት በተለይም ሕዝቡ ባደረጉት ሰፊ ዝግጅትና ርብርብ በደማቅ ሥነ ሥርዓት በሰላም ተከበረዋል። በእዚህ ስኬት ውስጥ የጸጥታ ኃይሉ ተጠቃሽ ተግባር ያከናወነ ሲሆን፣ የሰላሙ ባለቤት የሆነው መላው ሕዝብ ያበረከተው አስተዋጽኦም ከፍተኛ እንደሆነ ይታመናል።

ኢትዮጵያውያን አሁን ደግሞ በሌላ ደማቅ የበዓል አውድ ውስጥ እየገቡ ናቸው። ይህ በዓል በኦሮሞ ብሔር ዘንድ በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚከበረው የኢሬቻ በዓል ነው። በዓሉ ዛሬ በአዲስ አበባ ሆራ ፊንፊኔ፣ በማግስቱ እሁድ ደግሞ በቢሾፍቱ ሆራ አርሰዴ በሚሊየኖች የሚቆጠሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች፣ ሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም ዲያስፖራዎችና የውጭ ሀገር ዜጎች በተገኙበት ይከበራል። በበዓሉ ለመሳተፍ በብዙ ሚሊየኖች የሚቆጠር ሕዝብ ከሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች እንዲሁም ከውጭ ሀገሮች ወደ አዲስ አበባና ኦሮሚያ ክልሎች እንደሚተሙም ይጠበቃል።

ለበዓል አከባበሩ በኦሮሚያ ክልልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በኩል ዝግጅት ተደርጓል። ለእንግዶች አቀባበል በማድረግ፣ በጸጥታና ደህንነት፣ አደባባዮችን፣ ጎዳናዎችን፣ ወዘተ በማስዋብ በኩል ለሚከናወኑ ተግባሮች አስፈላጊዎቹ ዝግጅቶች ተደርገው ወደ ትግበራ ተገብቷል። በዚህም መሠረት ሆራ ፊንፊኔ የሚከበርባት የአዲስ አበባ ከተማ ጎዳናዎችና አደባባዮች በአባገዳ ባንዲራ እና በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተንቆጥቁጠዋል። በቢሾፍቱና በመላ የኦሮሚያ ክልልም ተመሳሳይ ዝግጅት እንደሚደረግ ይጠበቃል።

የኢሬቻ በዓል በክረምቱ መውጣትና ብራ መሆን አዲስ ተስፋ በሚሰነቅበትና፣ ምድር አረንጓዴ በምትለብስበት፣ ቡቃያው በሚያብብበት በእዚህ የመስከረም ወቅት ላይ የሚከበርና የኦሮሞ ሕዝብ ለእዚህ የፈጣሪ ጸጋ ምስጋና ለማቅረብ ርጥብ ሣር ይዞ ወደ ውሃ አካላት የሚወጣበት ነው፤ ይህ ብቻም አይደለም፤ ተቀያይመው የቆዩ ሰዎች ይቅርታ የሚጠያየቁበት፣ ያለፈውን ትተው ፈጣሪያቸውን በጋራ የሚያመሰግኑበትም ነው።

የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የተለያየ እምነት ተከታዮች የየራሳቸው በዓል ቢኖራቸውም፣ አንዱ የአንዱን በዓል በማክበር በእጅጉ ይታወቃሉ። በኦሮሚያ ክልል ሕዝብ ዘንድ በደማቅ ሥነ ሥርዓት የሚያከብረው የኢሬቻ በዓልም እንዲሁ፣ በመላ ኢትዮጵያውያን ዘንድ በተለያየ መልኩ የሚገለጽ እሴት እንደመሆኑ የመላ ኢትዮጵያውያንም የጋራ በዓል ነው።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ የአንዱ ቤት በዓል ለሌላውም ቤት በዓል ነው፤ በዓል በር ተዘግቶ አይከበርም፤ ቤተሰብን ብቻ ሳይሆን ጎረቤትን ማኅበረሰብንም ታሳቢ ይደረጋል። አንዱ አንዱን እንኳን አደረሰህ ይላል፤ ለዚያውም መልካም ምኞት መግለጫውን ይዞ። ይህ ብቻ አይደለም፤ ቤት ያፈራውንም ያቋድሳል፤ አንድ ላይ ይዘፈናል፤ ይጨፈራል፤ ይመረቃል።

የኢሬቻ እሴት በእያንዳንዱ ቤት ያለና ሊኖር የሚገባም ነው። ሰላም፣ አንድነት፣ ወንድማማችነትና ምስጋና ሁሉም ቤት ይኖራሉ፤ ምረቃው ለቤተሰብ፣ ለአንድ ቡድን ተብሎ አይደለም የሚደረገው፤ ለመላ ኢትዮጵያውያንም ለሀገርም ነው። ይህም የበዓሉን ማህበራዊ እሴትነት በሚገባ ያመለክታል። ይህ ማኅበራዊ እሴት እንዲጠበቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኃላፊነት እንደመሆኑ ለበዓሉ በድምቀትና በሰላም መከበር አስተዋጽኦ ማድረግ ከበዓሉ ባለቤት ብቻ የሚጠበቅ ሳይሆን፣ የኢሬቻ እሴት በውስጡ ካለው እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊም ይጠበቃል።

ኢሬቻ በሰዎች መካከል ማኅበራዊ ትስስርንና አንድነትን የሚያጎለብት የሰላም፣ የወንድማማችነት አርማ ነው። ይህ ደግሞ እነዚህን እሴቶች አጥብቆ ለሚያቀነቅነው፣ ለሰላም ከፍተኛ ዋጋ ሰጥቶ እየሰራ ላለው የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲሁም የሰላሙ ባለቤት ለሆነው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቅ ትርጉም ይኖረዋል።

መንግሥት የሰሜን ኢትዮጵያን ጦርነት በሰላም ስምምነት በመቋጨት ሰላምን ለማጽናት እየሰራ እንደመሆኑ ለሰላም የሚጠቅሙ የትኛቸውንም እሴቶች ይጠብቃል። ባለፉት በዓላት ወቅትም በዓላቱ በሰላም እንዲከበሩ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ አጥብቆ ሰርቷል፤ በዚህም ውጤታማ መሆን ተችሏል።

የኢሬቻ በዓልም በደማቅ ሥነ ሥርዓትና በሰላም እንዲከበር የኢትዮጵያ መንግሥት፣ የኦሮሚያ ክልል መንግሥት ከሕዝብ ጋር በመሆን በትኩረት መሥራት ከጀመሩ ቆይተዋል። በዓሉን የሰላም ማጽኛ፣ አንድነት ይበልጥ የሚሰርጽበት፣ ወንድማማችነት የሚጎለብትበት ለማድረግ መሥራት ከመላው ሕዝብ እንዲሁም የሰላም፣ አንድነትና ወንድማማችነት እሴቶችን ከሚያቀነቅን ማንኛውም ወገን ይጠበቃል። በዓሉን የሰላም፣ አንድነትና ወንድማማችነት ማጽኛ ማድረግም ይገባል!


አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ኢሬቻ

### የፍቅር ፣ የወንድማማችነት እና የአንድነት በዓል

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ኢሬቻ ኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ ጥንታዊና ነባራዊ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የበዓል አከባበር ሥርዓት ሆኖ የዘለቀ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከበር በዓል ነው። ክረምት ሲገባና መስከረም ሲጠባ (ቢራ) የሚከበር ነው። መስረም ሲጠባ የሚከበረው በዓል በሐይቆች በወንዞች ዳር ሆኖ አደይ አበባ፣ ለምለም የወይራ ቀንበጥ፣ እርጥብ ሣር (በአፋን ኦሮሞ ጂደ ይባላል) ተይዞ የሚከበር ባህላዊ ኩነት ነው።

በይበልጥ መስከረም ሲጠባ የሚከበረው ከመስቀል ደመራ በኋላ ባሉት እሁድ መካከል ነው። በቢሾፍቱ በሆራ አርሰዲ ማለትም በአርሰዲ ሐይቅ የአዲሱ ዘመን ኢሬቻ ሚሊዮኖች በተገኙበት በድምቀት ይከበራል። ይህም በብዛት ከጨለማው ክረምት ወደ ቢራ (ሲነቡብ ይጠብቃል ) ፀደይ ላሸጋገረ ዋቃን (ፈጣሪን) ምስጋና የሚቀርብበት ነው።

በዝናቡ ምክንያት በወንዞች ሙሌት የተለያዩ ሰዎች፣ ወዳጅ ዘመዶች እንዲሁም በእርሻ ተወጥረው ዘመድ ለመጠየቅ ላልቻሉ ፋታ የሚያገኙበት እና የሚገናኙበትና የሚጠያየቁበት ወቅት በመሆኑ ፈረንጆች የምስጋና ቀን እንደሚሉት ዓይነት Galataa Waqaa (thankfulness of God) ይቆጠራል።

ሲያከብሩም ከላይ እንደጠቀስነው አበባውን እርጥብ ሣሩን የወይራ ቀንበጡን ይዘው ምስጋና በማቅረብ ነው። በዚሁ ኢሬቻ አካባበር ከየአካባቢው የመጡ ኦሮሞዎች ምስጋናቸውን በደስታ በባህላዊ ዘፈኖች፣ ጭፈራዎች በውዝወዜ በግጥሞች በምሳሌያዊ አባባሎች ይገልፃሉ።

አፈንዲ ሙተቂ ባወጡት አንድ የምርምር ጽሑፍ ፤ ኢሬቻ በሐረርጌ ኦሮሞዎች እሬሳ በመባል እንደሚታወቅ ይገልፃሉ። በሁለቱ በዓላት የሚከበሩባቸውን ወቅቶች፣ የየበዓላቱን ዓላማ እና በዓላቱ የሚከበሩባቸውን ዐውዶች ያጠኑ ምሁራን በዓላቱ በጥንት ግብጻዊያንም ይከበሩ እንደነበረ ይናገራሉ።

ይሁንና ተመራማሪዎቹ ‹‹የበዓላቱ ምንጭ ጥንታዊት ግብጽ ነች ወይንስ ከግብጽ በታች የሚኖሩት የኩሽ (ኑቢያ) ሕዝቦች?›› የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተቸግረዋል። ጥያቄውን አስቸጋሪ ያደረገው የግብጻዊያኑ እምነት ብዝሀ አማልክት (Polytheism) የተቀላቀለበት መሆኑ ነው። በአፋን ኦሮሞ ዋቃ ቶኪቻ ሲባል አንድ አምላክ ማለት ነው። ኩሻዊያኑ ግን “ዋቃ”፣ “ዋቅ፣ “ዋቆ” እያሉ በተቀራራቢ ቃላት ከሚጠሩት አንድ አምላክ በስተቀር ሌሎች አማልክት የሏቸውም።

የእሬሳ እና የደራራ በዓላት በጥንቱ ዘመን ከኦሮሞ ሕዝብ በተጨማሪ የምሥራቅ ኩሻዊያን (Eastern Cushitic People) በሚባሉት የቤጃ፣ የሳሆ እና የሶማሊ ሕዝቦችም ይከበሩ እንደነበረ ተረጋግጧል። እነዚህ ሕዝቦች ቀደም ብለው የእስልምናን እምነት በመቀበላቸው በዓላቱን ማክበሩን ትተውታል። ይሁንና እንደነርሱ የኩሻዊ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው የአፋር ሕዝብ እስከ ቅርብ ዘመን ድረስ የኢሬሳን በዓል ያከብር እንደነበረ ልዩ ልዩ ጥናቶች ያስረዳሉ።

በኢሬቻ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ የተለያዩ ምሁራን፤ የኦሮሞ ሕዝብ ምድር እና ሰማይን ለፈጠረው ፈጣሪው ዋቃ ምስጋናውን ለማድረስ የኢሬቻ በዓልን እንደሚያከብር በዚህ ላይ አባ ገዳዎች፣ ሃደ ሲንቄዎች እና የማኅበረሰቡ ባህላዊ መሪዎች እንደሚታደሙ ይጠቅሳሉ። በአጠቃላይ ኢሬቻ የኦሮሞ ሕዝብ ከክረምት ወደ ፀደይ በሰላም ላሸጋገረው አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል እንደሆነ ይናገራሉ ።

የኦሮሞ ታሪክ ምሁሩ ዲሪቢ ደምሴን አነጋግሮ ቢቢሲ ባሰራጨው ዘገባ ፤ ‹‹ኢሬቻ ማለት ዋቃ (ፈጣሪ) ማለት ሲሆን በዓሉም ፈጣሪን ማመስገን ነው፤ በዓሉም ማኅበራዊ ደረጃ እና የእድሜ ልዩነት ሳይፈጠር በኦሮሞ ሕዝብ ለዘመናት በጋራ ሲያከበር ቆይቷል።

ኢሬቻ የዘመን መለወጫ በዓልም እንደሆነ፤ የኦሮሞ ሕዝብ ክረምቱን በማለፉ በኢሬቻ ቀን ምስጋናውን ለፈጣሪ እንደሚያቀርቡ፤ በክረምት ወራት ተራርቆ ሳይገናኝ የቆየ ዘመድ አዝማድ መስከረም ላይ ይገናኛል። ሕዝቡም ክረምቱን በፈጣሪ ፍቃድ የሞላው ውሃ ጎድሎ ከዘመድ አዝማድ አገናኝን ብሎ ምስጋና ያቀርባል።

የአንትሮፖሎጂ ባለሙያው ገመቹ መገርሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው ፤ ‹‹ክረምት ሌሊት ነው። ሌሊት ደግሞ ጨለማ ነው። ጨለማ ለአውሬ እንጂ ለሰው ልጅ አይሆንም። ጨለማው ሲነጋ ደግሞ ብርሃን ነው፤ ብርሃን ሲሆን ሃሳብ የለም ደስታ እንጂ። ‹‹መስከረም ጠባ ማለት ይህ ነው ›› በማለት የኦሮሞ ሕዝብ ከክረምት መገባደድ በኋላ የኢሬቻ በዓልን የሚያከብርበትን ምክንያት ያስረዳሉ።

የኦሮሞ ሕዝብ የኢሬቻ በዓልን ለማክበር ሲወጣ እንደ ሣር ወይም አበባ ያሉ እርጥብ ነገሮችን በእጁ ይዞ ይወጣል። ባለሙያው እንዳሉትና ቢሾፍቱ በተለያዩ ዓመታት በዓሉን ሲከበር በግሌ እንደታደምኩትም ‹‹ ቢራን በሪኤ አበቦን ደራሬ ›› እያሉ ሲዘፍኑ አይቻለሁ። በእኔ ግርድፍ ትርጉም ‹‹መስከረም ጠባ ኢዮሃ አበባ›› እንደ ማለት ነው።

ኢሬቻ ሲከበር ዋቄፈናን ጨምሮ ሁሉም የእምነት ተከታዮች ክርስቲያኑም ሙስሊሙም ኦሮሞዎች ይገኛሉ፤ በበዓሉ የሚገኙ የሌሎች ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቁጥርም ሰፊ ነው። ኢሬቻ ጥላቻና ሸኩቻ አልባ የፍቅርና የሰላም በዓል ነው። መቃቃርና መናቆር በኢሬቻ አከባበር ቦታ የላቸውም። የብሔሩ አባላት ኢሬቻ ሲያከብሩ እርቅ ፈጽመው ሰላም ወርዶ ጠብ ተወግዶ ነው።

የኦሮሞ አባ ገዳዎች በሄደበት ሁሉ ሕዝቡን እያቀፉ እና እየደገፉ ባህሉን እያስተማሩ በሞጋሳና በጉዲፈቻ ሥርዓት የብሔሩ አባል ያደረጉት ቤት ቆጥሮ አይጨርሳቸውም። የብሔሩም ቁጥር የበዛው በዚሁ መንገድ መሆኑን የታሪክ ሰነዶች ይመሰክራሉ።

መስከረም ሲጠባ በምስጋና የሚከበረው ኢሬቻ ክረምት ከመግባቱ በፊት ልምላሜ በመማፀን ዋቃን ለመለመን በተራራ ላይ በመውጣት በቱለማ ኦሮሞዎች የሚከበር ኢሬቻ በሚል ሳሙኤል ለይኩን ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ ያወጡት አንድ ጥናት ያሳያል። ጥሩነህ ረቡማ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሶሻል አንትሮፖሎጂ ዲፓርትመንት ለድኅረ ምረቃ ያወጡት አንድ ጥናትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው።

ሰፊ ተቀባይነት ያለው የኢሬቻ አከባበር በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ነው። ኢሬቻን በተመድ የትምህርት የሳይንስና ባህል ድርጅት ዩኔስኮ ለማስመዝገብ ጥረት ሲደረግ ነበር። ጥረቱ እንዲሰምር የፌዴራል የቱሪዝምና የባህል ተቋማት እንዲሁም የከፍተኛ ትምህርት ምርምር ተቋማት ትኩረት ሰጥተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ጽሑፋችንን የምናጠቃልለው በኢሬቻ ምርቃት ይሆናል።

Biyyi biyya nagaa nuuf godhi..........godhi Waaq

ሀገሩን የሰላም ሀገር ያድርግልን ......አድርግልን ፈጣሪ

Xinnaa keenya nuguddisi............guddisi Waaq

ሕፃናቱን ያሳድግልን .............. አሳድግልን ፈጣሪ

Guddaan Keenya nuuf haabulu .....bulchi Waaq

ታላቆችን ይደርግልን .............አድርግልን ፈጣሪ

Barri bara nagaa nuu ta'a................godhi Waaq

ዘመኑ የሰላም ዘመን ይሁንልን ..............አድርግልን ፈጣሪ

Barri kan quufaa fi gabbinaa nuuf haa ta'u .........

godhi Waaq

ዘመኑ የጥጋብና የፀጥታ ይሁንልን ፡፡ አድርግልን ፈጣሪ !

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብሰው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ስመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤^አስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ስመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ስድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

# የለመለመው ተስፋ …

## የተሁለደሬዋ ወይዘሮ …

መልካምሥራ አፈወርቅ

ፋጡማ ዓሊ ስለነገ ብዙ ታልማለች። የአንድ ልጇ ዓለም፣ የባለቤቷ ነገ የተሰራው በዛሬው ማንነቷ ነው። ይህ ህልሟ ዕውን እንዲሆን አታስበው የለም። ጠንክራ ብትሰራ፣ ጉልበቷን ብትከፍል ያቀደችውን አታጣም። ነገ ለእሷ የዛሬው ላብ ድካሟ ነው። ይህ ድካም ዋጋ የሚያገኘው ልቧ ሲቆርጥ፣ እግሯ ርቆ ሲሄድ መሆኑ አልጠፋትም።

ፋጡማ ይህ እውነት ከገባት ወዲህ ባለችበት መቆየት አላሻትም። ቀዬዋን ርቃ ባህር ተሻግራ ለመሄድ ወስናለች። አዎ! ትዳሯ እንዲሰፋ ቤት ጎጆዋ እንዲቀና ያላት ምርጫ ይህ ሆኗል። ለነገው መልካም ሕይወት ዛሬን ዋጋ መክፈል።

አሁን ፋጡማ ዓሊ አንድ ልጇን ስማ፣ ባለቤቷን ተሰናብታ ዓረብ ሀገር ተጉዛለች። የዓረብ ሀገር ሥራ እንደ ሀገር ቤት አይደለም። የበዛ ዋጋ የሚከፍሉበት፣ ጉልበት ከሕይወት የሚገብሩበት ነው። ወይዘሮዋ ይህ ሁሉ አልጠፋትም። ልጇን ለማሳደግ በእሾህ መንገድ መራመድ ካለባት ታደርገዋለች።

ትንሹ ዑስማን ከፍ ብሎ ቁምነገር እስኪደርስ የሰው ሀገር ልፋቷ አይቆምም። ፋጡማ የሰራችበትን ይዛ ሀገሯ ስትመለስ ጎጆ ትዳሯ ይሞላል፣ ቤቷን ሰርታ ልጇን ወግ ታደርሳለች፣ አከባሪ ባሏን ታኮራለች። ይህን ሕይወት በህይቅ በተሁለደሬ እንዳሰበችው ይሞላል።

### ትንሹ ዑስማን

አሁን ዑስማን የአጸደ ሕጻናት ተማሪ ነው ። ይህ ዕድሜ



ለነገው የዩኒቨርሲቲ ትምህርት መንደርደሪያ ይሆናል። ይህን ስታስብ ፋጡማ ደስ ይላታል። ዛሬን እንዲበረታ እጇ አይታጠፍም። የሚሻውን ጠይቃ፣ የጎደለውን ትሞላለች።

እነሆ ! ዓረብ ሀገርና ፋጡማ ከተገናኙ ከሁለት ዓመት በላይ ተቆጥሯል። ፋጤ ዘወትር ባሏ ይናፍቃታል፣ ሀገር ቀዬው ትዝ ይላታል። አንድ ልጇ በዓይኗ እየዞረ ይፈትናታል። ዓላማ ይዛለችና ለዚህ ስሜት አትሸነፍም፣ በሥራ አትለግምም ‹‹አቤት ወዴት›› ብላ ትታዘዛለች። ለቤት ጓዳዋ ሙላት ለልጇ ፍላጎት ትሮጣለች። በምትልከው ገንዘብ የምትሻውን ቤት የመሥራት ሃሳብ አላት። ይህ እንዲሆን ባለቤቷ ከጎኗ ነው።

አንዳንዴ ፋጤ ስለወደፊት ኑሮዋ ከቤተሰብ ማውጋቷ አይቀርም። ወንድሟ በስልክ ባገኛት ጊዜ ጠንክራ እንድትሰራ ይመክራታል። ባለቤቷ ልጇን አይታ እንድትመለስ ይጠይቃታል። የእሷ ሃሳብ ግን ከአንድ ረግቷል። ጨከን ብላ ነገዋን መሥራት አለባት። በእሷ ነገ ውስጥ የልጇ፣ የባለቤቷ ሕይወት አለ። ይህን ቀን በብርታቷ ማንጋት፣ ማየትን ትሻለች።

### የስልክ ጥሪው…

አንድ ቀን ፋጡማ ከቤተሰቦቿ የደረሳት የስልክ ጥሪ ለውሳኔ አበቃት። ሁሉም እየደጋገሙ ልጇ መናፈቁን ይነግሯት ይዘዋል። እስከዛሬ ይህን ቃል ስትሰማው ቆይታለች። የልጇ ናፍቆት በተነገራት ቁጥር ሆዷ ይባባል፣ ዓይኗ ያነባል። እንዲህ በሆነች ጊዜ መልሳ ለመጠንከር አትዘገይም። አሁን ግን ይህ ስሜት ከእሷ ርቋል። የዘመዶቿን ቃል ሰምታ የልጇን ዓይን ማየት ጓጉታለች።

ፋጡማ ፈጥና አሰሪዋቿን ፈቃድ ጠየቀች። ለሁለት ወር ሀገሯ ቆይታ እንድትመለስ ይሁንታ ተሰጣት ። ጓዟን ሸክፋ ጉዞ ስትጀምር ትንሹ ዑስማን ይበልጥ ናፈቃት። ዓይኖቹን እያየች አንገቱ ስር ገብታ እስክትስመው ቸኮለች።

አዲስ አበባ ስትደርስ እህቷ ተቀበለቻት። ጥቂት ቆይቶ ልጇና ባለቤቷ በቅርብ መኖራቸውን አወቀች። እሷ እንዳሰበችው ትንሹ ዑስማን ትምህርት ቤት አልዋለም።ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ገብቶ መታከም ጀምሯል። ፋጤ የሰማችውን ማመን አልቻለችም። በድንገጤ ልቧ እየመታ የሆነውን ጠየቀች።

ልጇ ከታመመ አንድ ዓመት ከአራት ወር እንደሆነው ተነገራት። ፋጤ አባትና ልጅ ካሉበት ፈጥና ደረሰች። ባለቤቷ ተጎሳቁሏል። ትንሹ ዑስማን እንዳሰበችው አላደገም። ዕንባ አነቃት ፣ ላብ አጠመቃት። ልጇን እየሳመች፣ ፀጉሩን እያሻሸች ስለ ሕመሙ ጠየቀች ። ችግሩ ከአንገቱ የወጣች ትንሽ ዕባጭ ስለመሆኗ ቀለል አድርገው ነገሯት ።

ፋጡማ በእጇ ያለውን ገንዘብ መንዝራ ልጇን ለማሳከም ተነሳች። ይሄኔ ባለቤቷ ቀስ እያለ ያረጋጋት ያዘ። የልጃቸው ሕመም እንደተነገራት ሆኖ ቀላል አልነበረም። የባሏን የመጨረሻ ቃል በጭንቀት ጠበቀች። የሰማችውን አምኖ መቀበል ተሳናት ። አንድ ልጇ የደም ካንሰር በሚሉት ሕመም ስለመያዙ ሰማች።

ፋጡማ ከዚህ ቃል በኋላ ራሷን በዱላ እንደመቷት አቅሏን ሳተች። ካንሰር ከባድና የማይድን ሕመም መሆኑን ደጋግማ ሰምታለች። ዙሪያው ጨለመባት፣ የት እንዳለች ጠፋት፣ ወዴት እንደምትሄድ ግራ ገባት። በውሰጧ ያለው ሃሳብ አንድ ልጇ እንደማይድን ሹክ እያላት ነው። ልቧ ፈራ ፣ ክፉኛ ተጨነቀች።

ውሎ አድሮ ፋጡማ ለሰዎች ምክር ጆሮ ሰጠች። የዑስማን ዓይነት ሕመም ያላቸው ልጆች በርካታ መሆናቸው ተነገራት። ችግሩ ቀድሞ ከተለየ ሕክምናው እንዳለ ባወቀች ጊዜ ተስፋዋ ለመለመ። ተረጋግታ ጥቂት ቀናት ከልጇ አሳለፈች። አባት ዑስማንን ይዞ ሕክምናውን ሲቀጥል እሷ ሀገሯ ደርሳ መምጣት አሰበች።

… ወደ ገጽ 17 ዞሯል

# የለመለመው ...

ከገጽ 16 የዞረ

## የነበረው እንዳልነበረ

ፋጡማ ከሀገር ቤት ስትወጣ ብዙ ውጥን ይዛ ነው ለባሏ በምትልከው ገንዘብ ቤት እንደሚሰራ ታውቃለች። ከትናንት በተሻለ ነገን ለመድረስ በዓረብ ሀገር ጉልበት መከፈሏ ግድ ሆኗል። ይህን እያሰበች ወሎ ሀይቅ የገባችው ፋጤ ከመኪና ወርዳ ወደ ሰፈሯ አቀናች።

ፋጤ ከቤቷ ስትደርስ፣ በዕልልታ የተቀበላት፣ በደስታ አቅፎ የሳማት የለም። ጓዳ ሳሎኗ «ኦና» ሆኗል። የትናንት ጥሪቷ ደብዛው የለም። ንብረቷ ተበትኗል። የጓሮ ሰብሏ ጠፍቷል። ላሞቹ አይታዩም። የእርሻ በሬዋ ተሸጧል። ይህን ስታይ ሆድ ባሳት፣ ባዶነት ተሰማት።

ፋጡማ እንደከፋት ዙሪያ ገባውን ቃኘች። ስትለፋለት የነበረው ቤት አልተሰራም። እንዲህ የሆነው በልጇ መታመም ነው። አምርራ አለቀሰች። ሁኔታዋን ያዩ ከቤቷ ገብታ እንድታርፍ አግባቧት። እሷ ሕይወት አልባውን ጎጆ አልመረጠችም። ሁሉን ትታ ከወንድሟ ዘንድ ከረመች።

ፋጡማ ተመልሳ ሳትሄድ አባትና ልጅ ከአዲስ አበባ ተመለሱ። ዑስማን ቀጠሮ ተሰጥቶት መድኃኒት ታዞለታል። አባወራው መንደሩ ሲገባ ሚስቱን ከቤት አላገኛም። በሁኔታዋ ቢከፋም አላዘነባትም። ካለችበት ሄዶ ከቤቱ መለሳት።

ፋጡማ እንደ አዲስ ባለትዳር ጎጆዋን ቀለሰች። ባዶ ጓዳዋን ልትሞላም የእጇን ሰነዘረች። ያለ ሰው የከረመው ቤት ጸድቶ፣ ተጠርጎ እንደምንም አንሰራራ። ከእናቷ ማጀት የመጣው እህል ተጋግሮ ቤተሰቡ ለገበታ በቃ። አሁን በነፋጡማ ቤት ስለነገ ማሰብ ቀርቷል። የሁሉም ዓይን ከዑስማን ውሎ ተስፋ እየጠበቀ ነው።

ከአስራ አምስት ቀን በኋላ ዑስማን ለቀጠሮው አዲስ አበባ ተመለሰ። ይሄኔ ፋጡማ ተመልሶ መሄዱን ትታ ባሏን መደገፍ፣ ልጇን ማገዝ ፈለገች። ይህ ፍላጎቷ ከአባወራዋ አነጋገራት። እሱ ወደ እርሻው እንዲመለስ ነገረችው። ባል ይህን ቢያደርግ፣ የጎደለ ማሳውን ቢመልስ ፈቃዱ ነው። እንደ ሀሳቧ ለመሆን ግን ጥርጣሬ ገባው። ከእሱ በላይ ለዑስማን የሚደርስ የሚያውቅለት እንደሌለ ቢሰማው ኃላፊነቱን ለመስጠት «እምቢኝ» አለ። ፋጡማ ባሏ ያለፈበትን የመከራ መንገድ ልትጓዝበት አልዘገየችም።

ሁለቱም ስለአንድዬ ልጃቸው ዋጋ ሊከፍሉ ተሽቀዳደሙ። ባልና ሚስት ስለ አንድዬ ልጃቸው መከሩ። ኋላ ኋላ አባወራው ተሸነፈ። ለአሁኑ ልጁን እናት ተቀብላ እንድታሳክም ተወስኖ በምርቃት ተለያዩ።

አሁን ፋጤ ከእጇ የቀረውን ስምንት ሺህ ብር ለበሬ መግዣ ሰጥታለች። አባወራው ከሌሎች አቀናጅቶ እርሻውን ጀምሯል። በብድር የተገዙት በጎች ከሜዳ ይውላሉ። ሕይወት በአዲስ ሊጀመር መውተርተር ተይዟል። ዑስማን ቀጠሮ ባለው ጊዜ አዲስ አበባ እየቆየ መመለስ ግድ እያለው ነው። እንዲህ መሆኑ ለቤተሰቡ ኑሮን አላቀለለም።

## ከዓመታት በፊት የአባወራው ፈተና

አባወራው ባለቤቱ ዓረብ ሀገር ሄዳለች። ሁለቱም ስለነገ ብዙ ወጥነዋል። ከምንም በላይ የአንድ ልጃቸው ሕይወት ያሳስባቸዋል። የዑስማን አባት የልጁን መታመም ያወቀው በአጋጣሚ ነበር። ዑስማን ከትምህርት ውሎ ሲገባ ድካሙን ያያል። ርቦት ይሆናል ብሎ ምግብ ይሰጠዋል። ልጁ የእህል ዘር ማየት አይሻም። አንዳንዴ ለመብላት ልቡ ቢፈቅድ ካፉ ሲደርስ አይጥመውም። እሱን ትቶ መረር ፣ ጎምዛዛውን ይፈልጋል። በየምክንያት ሰበቡ መበሳጨት ልማዱ ነው።

ዑስማን ከቤት በወጣ ጊዜ መንገድ ይርቀዋል። ከእኩዮቹ እኩል አይራመድም። ከኋላ ቀርቶ አዝግሞ ይገባል። ውሃ ሲጠጣ ጥሙን አይቆርጥም። ይህ ስሜቱ ከደስታ አርቆታል። አባት ችግሩ ሲገባው ሆስፒታል መውሰዱ አልቀረም። የሐኪም ውጤት ችግሩ ታይፎይድና ወባ መሆኑን ጠቁሟል።

ሁሌም የሚሰጠው መድኃኒት ለውጥ አላመጣም። «ተሽሎታል» ሲባል ያገረሽዋል። «ዳነ» ሲባል ካልጋ ይውላል። አባት ሁኔታው እያሳሰበው ነው። አሁንም ዝም አላለም። ደሴ ከሚገኝ የግል ሆስፒታል ወስዶ አስመረመረው። በጊዜው የተገኘው ውጤት የዑስማን ችግር የደም ማነስ መሆኑን አመለከተ። ከሆስፒታሉ ለቀናት ተኝቶ የሌላ ሰው ደም እንዲሰጠው ሆነ። እናት ፋጡማ ከሰው ሀገር ላቧ ያላትን እየላከች ነው። እሷ አዲስ ቤት መስራቷን እንጂ ልጇ መታመሙን አታውቅም። አባት ስለልጁ ጤና እየዋተተ ነው። ድካሙ አልያዘለትም። ዑስማን ልጁ በጎ አልሆነም። አልተሻለውም።

ውሎ አድሮ ከሐኪሞች ምክር ተገኘ። የዑስማን ሕመም ከባድ በመሆኑ አዲስ አበባ እንዲወስደው ተነገረው። አባወራው ከደሴ አልፎ አያውቅም። አዲስ አበባ «የኔ» የሚለው፣ መጠጊያ ዘመድ የለውም። እንዲያም ሆኖ ምርጫ አልነበረም። ትንሹ ልጁ ይድን ዘንድ ጉዞውን ከታሰበው መንገድ ጀመረ።

## ግራ መጋባት- በአዲስ አበባ

አባትና ልጅ አዲስ አበባ ካደረሳቸው መኪና ሲወርዱ መገኛቸው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሆነ። የያዙት ማስረጃ አግዟቸው ዑስማን አልጋ ይዞ እንዲታከም ተፈቀደለት። ሁለት ወራትን ያስቆጠረው ሕክምና ያለዘመድ ጉብኝት በብቸኝነት አለፈ።

ሂደቱ እንዳበቃ ዑስማን ከሆስፒታል ወጥቶ በክትትል መታከም ነበረበት። ይህ እውነት የተነገረው አባወራ ልጁን ይዞ ለመውጣት ተቸገረ። ባለበት ቦታ «እከሌ» ብሎ የሚጠራው ሰው የለም። አባት በትካዜ አንገቱን ደፋ። ዑስማንን ይዞ ይሄድ፣ ይደርስበት መንገድ ጠፋው። በብቸኝነት ግራ ተጋባ።

ችግሩን ያስተዋሉ ባይተዋርነቱን ያወቁ ዕንባውን ሊያብሱለት አልዘገዩም። ዑስማንን የመሰሉ የካንሰር ሕሙማን የሚያርፉባቸው ማዕከላት ስለመኖራቸው ጠቆሙት። አባወራው ልጁን ይዞ ወደተባለው ሥፍራ አመራ። በዚህ ሥፍራ እግሩ ከደረሰ ወዲህ የት ልግባ ብሎ አልተጨነቀም። ጥቂት የማይባል የመከራ ዓመታትን ግን መግፋት ያዘ።

ቀጠሮው ሳብ ሲል ሀገር ቤት ሊሄድ እግሩ ይቀናል። ጊዜው ሲደርስ ደግሞ ከማዕከሉ ይመለሳል። አባወራው የነጻ ሕክምናው እስኪገኝ ስለልጁ ጤና ያልሞከረው የለም። የፋጡማ ገንዘብ ሳይበቃው የአባቱን በሬ ሸጧል። ሀብት ንብረቱን ጨርሶ ጥሪቱን አሟጧል።

## እናት ፋጡማ ስልጇ

ፋጡማ ዓሊ ዛሬን ወንዱ ኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ ማዕከል ውስጥ ትገኛለች። አንደበተ ሸጋ ነች። ያሳለፈችውን ስትናገር ለአፍታ አትሰለችም። ቃሏ ይጣፍጣል። ከገጽታዋ የሚታየው ጥንካሬ ግን ከዚህ የዘለለ ነው። ያለፉ የማይመስሉ መከራዎች፣ የተሸነፉ የማይመስሉ የመከራ ቀናትን ድል ነስታለች። ፋጤ በሥፍራው ለመገኘቷ ሚስጥሩ የልጇ ዑስማን ጤንነት ነው። በዚህ ተቋም ብዙ አግኝታለች። ምስጋናዋ የበዛ፣ አክብሮቷ የተለየ ነው።

ዑስማን ለእሷና ለባለቤቷ አንድ ልጃቸው ነው። ገና ከሰባት ዓመቱ ጀምሮ በተገኘበት የደም ካንሰር ብዙ ዋጋ ከፍሏል። ይህ ክፍያ ግን የእሱ ብቻ አይደለም። እናቱ ስለእሱ ያልሆነችው የለም። ኑሯቸው ግብርና ነውና ሕይወታቸው ከገጠር ነው። እንዲያም ሆኖ ፋጤ ዝም አላለችም። ቤት ጓዳዋን ዘግታ፣ ዓለም ትዳሯን ትታ ስለ ዑስማን ታግላለች። አዲስ አበባ እያመላለሰች ጤናውን ልትመልስ ተስፋ ጥላለች።

ፋጤ አዲስ አበባ ስትመጣ ከቤት የሚቀረው አባወራ ሴት የምትሞላው ሙያ ይቸግረዋል። ቆሞ ለመሄድ፣ በልቶ ለማደር የሚያግዘው የለም። ይሄኔ ቂጣ እስከ መጋገር ይደርሳል። ፋጤም ብትሆን ባሏ ከሌለ ጎዶሎዋ ይበዛል። የወንዱ ሥራ ይቸግራታል።

እህል ሲታጨድና ሲወቃ ብቻዋን ናት። ባልና ሚስት በአንድ የሚሰሩት ሁሉ በእሷ ትከሻ ብቻ መውደቁ ብርቅ አይደለም። ይህ ሁሉ ዋጋ ስለ አንዱ ልጅ ዑስማን ሲባል ነው። በእሱ ጥንዶቹ ነገን አሻግረው ያያሉ። መዳኑን ተስፋ አድርገው መልካም ቀንን ይመኛሉ።፡

## ሌሎች ስለእነሱ


የባልና ሚስቱን ብርታት ያዩ ሁሉ ገረሜታቸው የተለየ ነው። ሁሌም የሚከፍሉት ዋጋ የበዛ ሲመስላቸው ያልተገባውን ይመክሯቸዋል። እሱን ትተው ሌላ እንዲወልዱ፣ በእሱ ተስፋ እንዳይጥሉ ይነግሯቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ የእነሱን አዲስ አበባ መመላለስ ከምኞት ቆጥረው ብዙ ይላቸዋል። ሌሎች ጠጋ ብለው እንደሱ ዓይነት ልጅ ቢኖራቸው ትተውት እንደሚመጡ እየነገሩ ውስጣቸውን ያደሙታል። እነሱ ግን ሁሌም ስለ ዑስማን ያላቸው አቋም የፀና ነው። ዛሬን አድነውት ነገን በተስፋ ማየት።

## ዑስማን ዛሬ

ዛሬ ዑስማን የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት ሆኗል። ከታመመ አስር ዓመታት ቢያስቆጥርም አሁን በደሙ የደም ካንሰር አይታይም። ከጊዜ በኋላ ያጋጠመው የነርቭ ሕመም ግን ጤናውን እየፈተነው ነው። እንዲያም ሆኖ ከትምህርቱ አልቦዘነም። ያቋረጠውን ትምህርት ቀጥሎ ስድስተኛ ክፍል ደርሷል። አንባቢና ፀሐፊ ነው። ዶክተር የመሆን ህልሙ ብሩህ ሆኖ ይታየዋል።

ጎበዝና የደረጃ ተማሪ የሆነው ዑስማን አንዳንዴ መቼ ነው የምድነው ሲል ራሱን ይጠይቃል። መርሳትና መበሳጨት ቢታይበትም ባህርይው አያስቸግርም። ፋጤ ትናንት ከልጇ ጋር የነበሩ መሰል ልጆች ዛሬ በሕይወት እንደሌሉ ታውቃለች። የዛኔ በመጀመሪያ ሕመሙ የታየበት የእሷ ልጅ ነበር። ይህን ስታስብ ዑስማንን «ጌጤ ወርቄ፣ ተስፋ አስትንፋሴ » ትለዋለች። እንደብረት የጠነከረችው፣ እንደ እዮብ የጸናችው ብርቱዋ እናት ፋጡማ ዓሊ።

# ስፖርት




## ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች የሚጠበቁበት የቺካጎ ማራቶን ነገ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ ከተሰጣቸው የማራቶን ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው የቺካጎ ማራቶን ነገ ለ45ኛ ጊዜ ይካሄዳል። 45ሺ ተሳታፊዎች በሚካፈሉበት በዚህ ውድድር የአትሌቲክሱ ዓለም ከዋክብትም ለአሸናፊነት የሚፋለሙ ይሆናል። አምና በዚህ ውድድር በሁለቱም ጾታ አሸናፊ የነበሩት የኬንያ አትሌቶች በድጋሚ በቦታው መሮጣቸውን ያረጋገጡ ሲሆን፤ ከኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ጠንካራ ፉክክር እንደሚገጥማቸው ይጠበቃል።

በወንዶች በኩል አምና የቺካጎ ማራቶን አሸናፊው ኬንያዊ አትሌት ቤንሰን ኪፕሩቶ እና ሁለተኛ ሆኖ ውድድሩን የፈጸመው ኢትዮጵያዊው ሰይፉ ቱራ በድጋሚ የቦታውን ክብር ለመቀዳጀት የሚፋለሙ ይሆናል። ኬንያዊው አትሌት ለሁለተኛ ጊዜ በዚህ ማራቶን ተሳትፎ የበላይነቱን መቆጣጠር ይፈልጋል። በአንጻሩ እአአ በ2021 የቺካጎ ማራቶን አሸናፊ የነበረው ሰይፉ ለሶስተኛ ጊዜ በመድረኩ በሚኖረው ተከታታይ ተሳትፎ አሸናፊ ለመሆን ተዘጋጅቷል። አትሌቱ ያለፈው ዓመት ለአሸናፊነት ብርቱ ጥረት ያደረገ ቢሆንም በ25 ሰከንዶች ብቻ ብልጫ ተወስዶበት ነበር የአሸናፊነት ዕድሉን የተነጠቀው። በመሆኑም ይህንኑ ለማስመለስና በውድድሩ አሸናፊ ለመሆን የሚያደርገው ጠንካራ ፉክክር በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ከወዲሁ በጉጉት እንዲጠበቅ አድርጓል።

እአአ ከ2017 አንስቶ ከመካከለኛ ርቀት ውድድር ወደ ጎዳና ላይ ፉክክሮች የተሸጋገረው አትሌት ሰይፉ በሴኡል ማራቶን የመጀመሪያ ተሳትፎው ሁለተኛ ደረጃን ይዞ




ሁለቱ የመካከለኛ ርቀት ኮከቦች በማራቶን የሚያደርጉት ፉክክር ትኩረት ስቧል፣

በማጠናቀቅ ነበር በርቀቱ ውጤታማነቱን ያረጋገጠው። አትሌቱ በቀጣይም በዱባይ፣ ሚላኖ እና ሻንጋይ ማራቶኖች በመሳተፍ ልምድ ማካበት ችሏል። በርቀቱ 2:04:29 የሆነ ሰዓት ያለውም ሲሆን፤ ይህም በኦሪጎኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሀገሩን እንዲወክል አስችሎት ስድስተኛ ደረጃን ይዞ ነበር ያጠናቀቀው። ከወር በኋላ ቺካጎ ማራቶንን በመሮጥም ፈታኝ ፉክክር በማድረግ ሁለተኛ ሆኖ ነበር ውድድሩን የፈፀመው። በነገው ውድድርም ኬንያዊያንን አትሌት በመርታትም የቦታውን ክብር በድጋሚ ለመቀዳጀት ይፋለማል።

ከሰይፉ ቱራ በሁለት ሰከንዶች የተሻለ የርቀቱ ሰዓት ያለው ኢትዮጵያዊው አትሌት ዳዊት ወልዴም በውድድሩ ከጠንካራ ተፎካካሪዎች መካከል አንዱ ነው። እአአ የ2019ኙ የቫሌንሲያ ማራቶን አሸናፊ እንዲሁም በ2022 በለንደን ማራቶንን አራተኛ በመሆን ያጠናቀቀው አትሌት ክንዴ አጣናው በዚህ ውድድር ይካፈላል። በቶኪዮ ማራቶን ለጥቂት አሸናፊ መሆን ያልቻለው አትሌት ሁሰዲን ሞሃመድ እንዲሁም የዚህ ዓመት የዴጉ ማራቶን አሸናፊው ሚልኬሳ መንገሻም በኢትዮጵያ በውድድሩ ተፎካካሪ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ናቸው።

በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድር የ2022 ቺካጎ ማራቶን አሸናፊዋ ኬንያዊት አትሌት ሩት ቺፕጌቲች የምትካፈል ቢሆንም በርካታ ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ተሳትፎ መረጋገጡ ለአትሌቷ አሸናፊነት ስጋት ሆኖባታል። 2:17:36 የሆነ ፈጣን ሰዓት ያላት ወጣቷ ኢትዮጵያዊት አትሌት ታዱ ተሾመ ኬንያዊቷን ተከትላ የተቀመጠች ሲሆን፤ ጠንካራ የአሸናፊነት ፍልሚያ እንደምታደርግ ይጠበቃል። ይሁንና ለአሸናፊነት ከሚደረገው ጥረት ባለፈ በመም ውድድሮች ከፍተኛ ፉክክር የነበራቸው ሁለት አትሌቶች በጎዳና ውድድር በድጋሚ መገናኘታቸው ፉክክሩን እንዲጠበቅ አድርጎታል። ይህም በመካከለኛ ርቀት ክብረወሰኖችን እንዲሁም ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ የምትታወቀው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ገንዘቤ ዲባባ እና አሁንም ድረስ በመም መካከለኛና ረጅም ርቀቶች ተጽእኖ ፈጣሪ አትሌት በሆነችው ኔዘርላንዳዊቷ ሲፈን ሃሰን መካከል የሚደረግ ነው።

ከ2020 ወዲህ በጎዳና ላይ ሩጫዎች እየተካፈለች የምትገኘው ገንዘቤ የመጀመሪያ ተሳትፎዋ በሆነው የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን አሸናፊ ነበረች። ባለፈው ዓመት ደግሞ በአምስተርዳም ማራቶን ሮጣ የሀገሯን ልጅ አልማዝ አያናን ተከትላ በመግባት ሁለተኛ ደረጃን ይዛ አጠናቃ ነበር። በዚያ ውድድር ያስመዘገበችው 2:18:05 የሆነው ሰዓቷም በቺካጎ ማራቶን ተሳታፊ ከሆኑ ምርጥ አትሌቶች አራተኛው ፈጣን ሰዓት ነው። ይኸውም አትሌቷ በተካነችበት ፈጣን አሯሯጧ ታግዛ ድሉን እጇ ታስገባለች የሚል ግምት ከወዲሁ እንድታገኝ አድርጓታል።

በአንጻሩ በ1ሺ500ሜትር የገንዘቤ ተፎካካሪ የነበረችውና በቅርቡ በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና በሶስት ርቀቶች ተካፋይ የነበረችው ሲፋን ሃሰን ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ በቺካጎ ትሮጣለች። ይኸው የሁለቱ አትሌቶች ብርቱ ፉክክርም በማራቶንም ይደገም ይሆናል የሚለው የብዙዎችን ትኩረት ስቧል። ሲፈን ከወራት በፊት በተካሄደው የለንደን ማራቶን በመሮጥ በርቀቱ ያላትን ተስፋ አሳይታለች። አትሌቷ የገባችበት 2:18:33 የሆነ ሰዓትም በቺካጎ ተካፋይ ከሚሆኑት አትሌቶች ሰባተኛው ፈጣን ነው።

በማራቶን ሰፊ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ሱቱሜ ከበደ፣ ትዕግስት ግርማ እና አባበል የሻነህ ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አትሌቶች አይደሉም።